ምዕራፍ ዘጠኝ

ተግተን እንድንፀልይ የሚያስገድዱን ወቅታዊ ተግዳሮቶች

ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅ ፊትም ለመቆም እንድትችሉ ስትፀልዩ ሁል ጊዜ ትጉ (ሉቃ. 21፡36) ።

ከዚህ ከፍ ብለው ባሉ ከፍሎች የምንፀልይባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶችን ተመልከተናል። ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት መፍጠር ስለሚገባን ብሉይና አዲስ ኪዳን በፀለዩ ለዎችና በፀሎታቸው ውጤቶች የተሞላ በመሆኑ የመፀለይን አስፋላጊነት አይተናል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ነባራዊ የሆኑ በአሁኑ ዘመን እየተከሰቱ ያሉ ካልፀለይን በቀር ማምለጥ የማንችላቸዉ ነገር ግን በመፀለይ ብቻ ለማምለጥና ሌሎችንም ለማስመለጥ የምንችላቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም እንኳሮቹን ብቻ ከዚህ ቀጥለው ባሉ ገጾች ለመግለጽ እወዳለሁ። እዚህ ላይ ለማስገንዘብ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር የነገሮቹ ግዝፈት እስደንግጠን ተሰፋ እንድንቆርጥ ሳይሆን ከእነዚህ ሁሉ በላይ የሆነና እነዚህን በሙሉ ድል በማድረግ የፀሎታችንን ምላሽ ለመለጠት የሚችለውን እምላካችንን፣ እባታችንንና ጌታችንን በማመን መፀለይ ነዉ።

፩. የዓለም ሕዝብ እየበዛ መሄድና ወንጌል ያልደረሳቸዉ ሕዝቦች ብዛት

በዚህ ወቅት ያለው የአለም ህዝብ ፈጠን እድገትና ወንጌል ያልዳረሳቸው ሕዝቦች ብዛት እጅግ እንድንፀልይ ያስገድዳናል።

- የዓለም ሕዝብ በመለከረም 2006 ዓ.ም 7.135 ቢልየን (7,135,000,000) ደርሷል።
- ደህንነት በክርስቶስ በማመን ብቻ ነዉ የሚለዉ የክርስተያን ብዛት 10%ቱ ወይንም 703 ሚለየን ብቻ ሲሆን የቀራዉ ደግሞ 90% ያህል ይሆናል። በቁጥር ሲለላ ደግሞ 6.33 ቢልየን ነዉ።
- የካቶሊክ እምነት ተከታይ 18% ይሆናል። በቁጥር 1.27 ቢልየን ይሆናል ማለት ነዉ። የኦርቶዶክስ ተከታይደግሞ 4% ይሆናል። በቁጥር 282,ሚልየን ይሆናል ማለት ነዉ።
- የእስልምና ተከታይ 21% ይሆናል። በቁጥር 1. 48 ቢሊየን ይሆናል ማለት ነዉ።

- ሃይማኖት የለሾች ወደ 1 ቢለየን ይደርሳሉ።
- የህንዱ እምነት ተከታዮች ቁጥር ብዛት ወደ 1 ቢልየን ይደርሳሉ።
- የቀሩ ደግሞ የተለያዩ (ቡዲዚም፣ ሲክ፣ ጣዖትት እምላኪ) 1.35 ቢልየን ይሆናሉ።

በማቴ. 9፡35-38 ባለዉ ከፍል ላይ ጌታ መከሩ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸዉ ሲል የተናገረው ቃል ዛሬ እውነታው ከፍ እያለ ነው ያለዉ ። በዓለም ካለው ከ7.135 ቢልዮን ሕዝብ መከከል 713 ሚልዮን ብቻ በትከክል እማኝ ሲሆን 6.33 ቢልዮን ዳግሞ ገና ወንጌል የሚያስፈልው ሕዝብ እንደሆነ እላይ አይተናል። ይህም ብቻ ሳይሆን ከዳነውም ህዝብ መከከል በትከከል ሚስዮናውያንን በመላከ ወንጌልን እየሰሩ ያሉት እጅግ ጥቂቶች ናቸው። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በየዕለቱ ከሚሞቱ ከ163,000 ሠዎች መካከል በትንሹ ጌታን ሳይቀበል በየዕለቱ የሚሞተው ህዝብ 146,000 አያንስም፤ ይበልጣል እንጂ። በዓመት ታዲያ ከ53,000,000 (ከ53 ሚልዮን) በላይ ሰው በእነስተኛው አየሞተ ገሃነም እየገባ ይገኛል። ታዲያ ይህ እየሆነ እያለ ለእኛ ለእማኞች ደስ ብሎን ቃሉን እየሰማን ቤተክርስቲያን እየሄድን እየተመለስን፤ እየበላን፤ እየጣጣን፤ ቤት እየሠራን፣ ትዳር እየመሠረትን ለሚጠፉት ግድ የማይለን ከሆነ በጣም አሳዛኝ ነዉ። ጌታ ግን ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ሰፍጥረት ሁሉ ስበኩ ብሎናል። ብዙ የአለም ሕዝብ ወደ ሞት ጎዳና እየነጎደ ነው። እግዚአብሔር ይሙን ከእኛችን እንደሚፈልግብን ተናግሮናል። እጥፈ ጦርነት ከመጣ ሰው ባለው ሁሉ ወደ ጦርነት እውድማ ይገባል። ይህን ሁሉ ጥፋት እያየን፣ እግዚአብሔርም እያለቀሰ እኛ ደግሞ ጀሮ ዳበ ልበስ ብንል የጌታ ልብ ያዝናል። እየሆነ ስላለው ነገር በምድር ባንጠየቅም በሰማይ እንደምንጠየቅ በሚገባ ማወቅ አለብን። መንፈስ ስእብያተ ከርስቲያናት የሚለውን ጀሮ ያለው ይስማ በማለት ጌታ የደጋገመዉ እደራችንንም እንድንገነዘብ ጭምር ነዉ። ከሁሉም በላይ ግን የመከሩ ጌታ ለመከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑ በማለት ጌታ ስለሚጠፉ ነፍሳትና ሕዝቦች ስላዘዘን፡- የሚያለቅሱ ሰዎችን ወይንም የፀሎት ቡድኖችን በየቤተ እምነቱና በየእጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒያናቱ ማደራጀት አለብን።

ፀሎት፣ የሕንፃ ሥራ፣ የሳውንድ ሲስተም፣ ኮንፍራንሱና ክሩሴዳ እንዲሁም የተለያየ የገንዘብ ወጪ፣ ለዳነው ሕዝብ ብቻ ከሆነ ኢየሱሪ ከሰማይ መጥቶ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ሞቶ የተቀበረበትንና የተነሳበትን እንዲሁም ቤተ ክርስተያን በምድር ላይ የተቀመጠችበትን ዋና ዓላማ ረስተናል ማለት ነዉ። እግዚአብሔር እንቂ ደወል እየደወለልን ስለሆነ ቢያንስ በዓመት አቅዳችን ዉስጣ ለወንጌል ስርጭት የሚያስፈልግ በጀት መመደብ አለብን። ዛሬ ቤተክርስቲያን ዋናዉን ነገር ረስታ ዋና ባልሆነ ነገር ላይ ስትረባረብ የጌታ ልብ ለአብያተ ክርስቲያናት እያለቀሰ ነው። እጅግ አሳዛኝ ነገር ቢኖር ራዕይ አለኝ የሚል ሁሉ ካናዳ፣ አሜሪካ፣ አውሮፓና ደቡብ አፍሪካ ልሂድ የሚል እንጂ ለዚህ ወንጌል ሕይወቴን ልሰዋ የሚሬ እጅግ ጥቂት ነዉ። የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት ስው ወንጌሬ ሳይሰማ በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር ሰዉ እየሞተ ገሃነም እየወረደ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር በወንጌል ስም በተለያ ነገሮች ላይ እያፈሰሰን በእዉነት እግዚአብሔርን ምን ያህል እያሳዘነው እንደሆ ግንዛቤ ቢኖረን የተሻለ ነዉ። እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሰጣትን የሰው፣ የገንዘብ፣ የዕውቀትና የፀጋ ስጦታ (resourece) በእግዚአብሔር ዋና እጅንዳ ላይ እያዋለች ናትን?

ደግሞም ወንጌል በሚል ስያሜ የተሰየሙ ብዙ ሚኒስትሪዎች ስማቸው ወንጌል ነው ሥራቸው ግን ከወንጀል ያላነሰ ነው። በወንጌል ስም ይሰብኩና የሚገዙት ምቾት የሚሰጥ መኪና ነው። የሚሠሩት የሚያማምሩ የግል ቤቶችን ነው። ጌታ ምህረቱን ያብዛልን፤ ወደርሱም ሀሳብ ልባችንን ይመልሰዉ። ከላይ እንዳየነዉ የሕዝብ ቁጥር እጅግ እያደገ ነው። ደግሞም ወንጌል ያልሰሙ ሰዎች ቁጥርም በዚያዉ ልክ በብዙ እያደገ ነው። ጌታ የሰጠንን የአገልግሎት ቦታ ተጠቅመን ወንጌልን ለሚጠፉት ነፍሳት ለማድረስ እንነሣ። ባለን ምዕመን ብዛት እንርካ። ከኢየሱስ በረት ውጪ የሆኑ በጎችን ዋጋ ከፍለን እንፈልጋቸው። እግዚአብሔር የሰጠንን ይህንን ወርቃማ ዘመንና አጋጣሚዎችን ተጠቅመን ያልዳኑ ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር ቤት ይጉረፉ። ይህ ትውልድ የወንጌል ባለ እደራ እንደሆነ እንንገረው። የእቅማችንን ብናደርግ ከተጠያቂነት እንድናለን። ከሁሉም በላይ ግን በነኛ ቆሮ 9፡ 22-23 መሠረት በማናቸውም መንገድ ወንጌልን ለማድረስና በወንጌል ማህበርተኛ ለመሆን ጥረት አናድርግ። እኛ ቆርጠን ብንነሣ ጌታ ሊረዳን የተዘጋጀና የታመነ እምለከ ነው። ለዕውቀትና ለፀሎት እንዲረዳን ከዚህ ቀጥሎ ያለዉን ልብ እንበል፡-

- በዓለም ለይ 16,352 ብሄር ብሄረሰቦች አሉ ይባላል።
- ከእነዚህ ውስጥ ከ2% በላይ ወንጌል የደረሳቸው 9,600 ሲሆን
- ከ2% በታች ክርስቲያን ወይንም ምንም ወንጌል ያልዳረሳቸው ደግሞ 6,700 በላይ ይሆናሉ።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ከ2001 ዓ/ም ሕዝብ ቆጠራ መሠረት
  - ኦርቶዶክስ 43.5%
  - ሙስሊም 33.9%
  - ፕሮቴስታንት 18.7%
  - ካቶሊክና 0.7%
  - ሌሎች 3.2% ናቸው።

ጸሎታችንም ደግሞ ሰዎች ወደ ወንጊላዉያን አማኞች ቤተክርስቲያናት እንዲመጡ ሳይሆን የትም ሆነዉ የጌታን ማንነት እንዲረዱ መሆን አለበት።

2. የተጠናከሩ የጠላት አንቅስቃሴዎች አንድንጸልይ ያስገድዱናል

2.1 የተለያዩ ሃይማኖቶች አንቅስቃሴ

ሙስሊሞች ለሃይማኖታቸዉ በጣም ይቀናሉ። ስለ ሃይማኖታቸዉ ራሳቸዉን እንኳ አሳልፈዉ ከመስጠት ወደ ኋላ አይመለሱም። እኛ ክርስቲያኖች የእነርሱን ያህል ብንቀሳቀስ ኖሮ ዛሬ እጅግ ብዙ ፕርሰንት ክርስቲያን በሆነን ነበር። የዓላማቸው ጽናት ከእነርሱ ብዙ እንድንማር ያደርገናል። እነርሱ በቁራናቸው ውስጥ ያለው እውነት በርቶላቸው ወደ ኢየሱስ እንዲመጡ ፀሎት ያስፈልገናል። ነገር ግን ለሚለፉ እግዚአብሔር የልፋቱን ዋጋ መስጠቱ የእርሱ መለኮታዊ ባህርዩ ነውና እነርሱ በየእጭር ኪሎ ሜትር ርቀት መስጊድ የመሥራት ዓላማቸዉም እተሳካላቸዉ ነዉ። እለምን በእስልምና የመጠቅለል ዓላማቸዉም እየተጠናከረ ነዉ። ነገር ግን የምንጸልየዉን ስለምናገኝ እጥብቀን ብንጸልይና ተባብረን ብንሰራ ብዙ ሙስሊሞች ወደ ጌታ መምጣት ብቻ ሳይሆን ወንጌል በመካከላቸዉ በነጻነት የምሰበክብት ዘመንን ጌታ ያመጣል። በአሁን ሰዓት እንኳ በመካካላቸዉ ብዙዎች ጌታን ለመቀበል ይፈልጋሉ። ነገር ግን የሰደቱን እስከፊነት ስለሚፈሩ ዝም ብለዉ ቀናቸዉን የሚጠብቁ ብዙዎች ናቸዉ። ሆኖም ግን በራዕይ ፣ በህልም፣ በቁራናቸዉ፤ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፣ በዘመኑ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ... ብዙዎች ጌታን እየተቀበሉ ቢሆንም የበለጠ ጌታን እያመስገንን ስለ እጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው

የተጠናከረ የጸሎት ኃይል ያስፈልገናል። ለእስልምና የሚቀኑ ለኢየሱስ እንዲቀኑ፣ አሳዳጆች ወንጌል ሰባኪዎች እንዲሆኑ አብዙተን መጸለይ ይጠበቅብናል። የእስልምና፣ የቡዲዚምና የሀንዱዚም መዲናዎች በሙሉ የከርስትና መዲናዎች እንዲሆኑ ጥብቅ ጸሎት ማድረግ አለብን።

2.2.1. በቤተክርስቲያን ዉስጥ ያሉ ተግዳሮቶች ጥብቅ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል

ቤተክርስቲያን የነበረችባቸዉ የመከራ ዘመናት ለእድገቷ ትልቅ አስተዋዕጽዖ ሲያደርጉ፣ በእንፃሩ ግን የነፃነት ዘመን ደግሞ የቤተክርስቲያንን ዉድቀት ሲያፈጥን እንደነበረ ከታሪክ እንማራለን። ጄ. ኤል. ዊልያምስ (J. L Williams) የሚባሉ ሰዉ እንዲህ ብዋል፡- "History proves that persecution and poverty had *never been* enemies of the Church of Christ, but prosperity and freedom had *ever been* enemieis of the Church of Christ." ማለትም «ስደትና አጦት የቤተክርስቲያን ጠላት ሆነዉ አያዉቁም። ነገር ግን ብልጽግናና ነፃነት ዘወትር የቤተክርስቲያን ጠላቶች እንደነበሩ ታሪክ ያረጋግጣል» ብሰዋል። በእርግጥ ይህ አዉነት መሆኑን ምዕራባዉያን ቤተክርስቲያናት አሁን ካሉበት ሁኔታ ለማረጋገጥ እንችላለን። በእኛም አገር የነበረዉ ስደት ቤተክርስቲያንን አጠራት እንጂ አላጠፋትም። ነገር ግን በአሁን ሰዓት ያለዉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እዝማሚያዋ አደገኛ ነዉ ለማለት ያስችላል። በመከራ ዘመን ሰዉ አትጸልይም ሲባል፣ እንዳያመልክ ቤተ ክርስቲያን ሲዘጋበት በሌሊት እየተነሳ በግለሰብ ቤቶች ይጸልይና ያመልክ ነበር። ነገር ግን ዛሬ የፈልግነዉን ያህል ለመጸለይ ቤተክርስቲያን ክፍት ናት። ሆኖም ግን የክርስቲያኑ የጸሎት ፍቅር እየሞተ ይገኛል። ከሁሉም ጉባኤ በጣም አነስተኛ የሚባለዉ ለጸሎት በሚደረግ ጥሪ የሚመጣ ጉባኤ ነዉ። ከዚህም የተነሳ በዚህ ዘመን ብዙ ባዕድ ነገሮች እየሾለኩም ሆነ በቀጥታም ወደ ቤተክርስቲያን እየገቡ ናቸዉ። በእዉነትና በመንፈስ አግዚአብሔርን ለማምለክ የሚፈልጉ ሁሉ ልባቸዉ እየቆዘመ ነዉ። እትኩረን ጸሎት እንድናደርግ የሚገቡን የዘመናችን ቤተክርስቲያን ተግዳሮቶች ምንድር ናቸዉ? ከዚህ ቀጥለዉ ያሉትን ልብ አንበልና ለአሁኗ ዘመን ቤተክርስቲያን የጸሎታችንን መጠን አብዝተን መጨመር እንዳለብን ማሰብ አወዳለሁ።

ከዘመኗ ቤተ ክርስቲያን ዉስጣዊ ተግዳሮቶች እንዳንዱን እንመልከት

- በመሪ፤ በአገልጋይና በምዕመን መካካል መንፈሳዊነት የጎደለዉ ሥጋዊ ዉድድር፣
- ለመጸለይ ጊዜ የለኝም በሚል ራስን በማሳመን ላለመጸለይ ምክንያት ማብዛት፣
- ሰዉ የአግዚአብሔርን ገንዘብ (በተሰይ አሥራትን) ቅር ሳይለዉ መሥረቅ፣
- ትልቅ የቅድስና ችግር በአግዚአብሔር ቤት (ልጆች) መካካል መታየት፣
- የዘረኝነት በሽታ ቤተክርስቲያንን የዉጥረት ቤት ማድረግ፣
- የዘመኑ ትዉልድ ምኞት ወዳጅ፤ ስለ ወንጌል መከራ ከመቀበል የሚሸሽ፤ ዋጋ ከፍሎ ከማገልግል ይልቅ ዋጋ እየተከፈለለት ለማገልገል የሚፈልግ መሆንና መሰል ችግሮች፣
- የሐሽሽ፣ የአልኮል፣ የጫት መሰል ንግዶች መጧጧፍና አግዚአብሔር በማይከብርበት መንገድ ሀብታም ለመሆን መጣርና የብዙዎች ለአጉል ልማዶች ሱሰኝነት ሰለባ መሆን፣
- ከርስቲያን ባለበት አካባቢና መሥሪያ ቤት ምሳሌያዊ (ክርስቶስን የመምሰል) ኑሮ ካለመኖር የተነሳ ወንጌልና ከርስትና በጎ ተጽዕኖ ለመፍጠር አቅም ማጣት፣
- በቤተ ከርስቲያን ዉስጥ ያሉ ምዕመን እጋፕ ፍቅር ያጣ መሆን፣
- አግዚአብሔርን መፈለግና ከአግዚአብሔር ጋር ጊዜ ከማጥፋት ይልቅ ፋሽን በማሳደድና በቁሳቁስ ለመርካት መጣር፣
- የዉሸት ነቢያት ምድሪቱን መሙላትና አዉነትን የሚሰብኩና ለአዉነት የሚቀኑ በቤተክርስቲያን እንኳ ሳይቀር መገፋት፣
- ለአገልጋይ በቂ ቀለብ ለለማይሰፈርለት የከበረዉ የወንጌል አገልግሎት አቅምና ያጣ መሆን፣
- ቤተክርስቲያን ነፍሳትን ለማዳን ከመረባረብ ይልቅ በሚታይ ነገር ጉልበቷንና፤ ገንዘቧንና ጊዜዋን መስዋዕት በማድረግ ዋና ነገርዋን መጣል፣
- የአግዚአብሔር ቤት በእርሱ መገኘትና በከብሩ ሙላት በዉስጥ ባሉትና ከዉጪ በሚመለከቱት መፈራት ሲገባዉ እንደ ተራ ቤት መቆጠር፣
- ብዙ አማኞች ለሀብት ፍለጋ ወደ ጥንቆላ ቤቶች መመላለስና ወዘተ ናቸዉ።

ታዲያ እነዚህና ሌሎች እጅግ ብዙ ተግዳሮቶች ቤተክርስቲያንን እያጣደፏት በሚገኙበት በዚህ ዘመን ከመቼውም ይልቅ በርትተን በመፀለይ ተግዳሮቶቹን ለመቋቋም እንድንችል ጌታ ይርዳን::

ምዕራፍ አሥር

እንዴት እንፀልይ?

አርሱ በአንድ ሥፍራ ይፀልይ ነበር:: በጨረሰም ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ጌታ ሆይ ዮሐንስ ደቀመዛሙርቱን እንዳስተማራ እንፀልይ ዘንድ አስተምረን አለው» (ሉቃ ፲፡፩)::

በየዘመኑ የተነሡ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ደቀ መዛሙርቶቻቸውን እንዴት መፀለይ እንደሚገባቸዉ ያስተምሯቸው ነበር:: ከእነዚያም አንዱ ዮሐንስ ነበር:: ኢየሱስ ሰደቀመዛሙርቱ በቃላት ስለ ፀሎት ከማስተማሩ አስቀድሞ በመፀለይ ሰለፀሎት እንዳስተማረ ከላይ የተጠቀሰዉ ከፍል ግልጽ ያደርግልናል:: በተሰያዩ ጊዜያት ኢየሱስ ስብቻው ሲፀልይ ያዩ ስሰነበር ሰለ ፀሎት አስፈላጊነትና ጥቅም የልባቸውን መነሣሣት ካየ በኋሳ እንዴት መፀለይ እንደሚገባቸው አስተማራቸው (ሉቃ ፲፡1-13, 18፡1-7)::

ይህም በየዘመኑ የሚነሡ መንፈሳዊ መሪዎች ደቀመዛሙርቶቻቸውን ስሰፀሎት ማስተማር እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው፡:: ለምሳሌ ያህል ከታሪክ ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል ጆን ኖክስ (John Knox) የሚባል የእስኮትላንድ ተሃድሶ መሪ የነበረ ሰው «እግዚአብሔር ሆይ እስኮትንድን ስጠኝ ወይንም ግደለኝ» እያለ ይፀልይ ነበር:: የጆን ኖክስን ልጅ ያገባ ጆን ዌልች (John Welch) የሚባል ሰው ደግሞ የእስተማሪውን ማለትም የአማቹን የፀሎት ህይወት .በጣም ይመኝ ነበርና እርሱ ደግሞ እግዚአብሔር የአማቹን ብዙ እጥፍ ጊዜ ስመፀለይ እንዲችል ተማጸነ:: በእግዚአብሔር ፊትም በየቀኑ ከ7-8 ሰዓታት ለመጸለይ ቃል ኪዳን በማድረግ ጸሎቱን ቀጠለ ይባሳል:: ከዚህም የተነሳ በአማቹ በጆን ኖክስ የተጀመረውን የእስኮትላንዱ የተሃድሶ ንቅናቄን ወደ ግቡ ያደርሰ ሰው ጆን ዌልች እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይናገራል::

በእንግሊዝ አገር የተነሣው ታላቅ የፀሎት ሰው ጆን ዊከለፍ እንዲሁ ሎላርድስ የሚባሉ የፀሎት እርበኞች እንደነበሩትና ከእርሱ የተማሩትን የተሃድሶ ንቅናቄ በየደረሱበት ያቀጣጥሉ እንደነበርና በእነርሱ የተጀመረዉ የተሃድሶ ንቅናቄ እርሾ ቆይቶ ተሃድሶን እንደወለደ ይነገርላቸዋል::

በጀርመን አገር ከተሃድሶ አንቅስቃሴና መነቃቃት በኋላ የቤተክርስቲያን መቀዝቀዝ ጀምሮ ነበር። እግዚአብሔር ለተሰየ ዓላማ በወቅቱ ያስነሣው ዚንዘንዶርፍ የሚባል ሰው ከሀብታም ወላጆቹ የወረስውን ጎንዘብና ርስት በወንጌል ምክንያት ለተሰደዱ ሞራቪያኖች በነፃ ከሰጠና በኋላ ስለ 24 ሰዓት የፀሎት ሰንሰለት እንዳስተማራቸዉ ጠቅሻለሁ። አርሱም መስዋዕትነትን ከፍሎ ያስተማራቸው የፀሎት ስልት ለ100 ዓመታት በታማኝነት አንደተካሄደና ያ ደግሞ ዓለምን ሁሉ ያካለለ የሞራቪያኖች የጸሎትና የወንጌል ንቅናቄን እንደወለደ የቤተክርስቲያንና የሚስየሎጂ ታሪክ ያረጋግጣል። ከዚያም በላይ እነዚህ የወንጌል ተልዕኮው እንቅስቃሴ አራማጆች ወደ አውሮፓ፣ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ፣ ኢስያ፣ አፍሪካና እውስትራሊያ እንዲሁም ወደ ካሪቪያንና ፓስፊክ ደሴቶች ሁሉ ሳይቀር በታላቅ መስዋዕትነት የወንጌል ንቅናቄን እንደፈጠሩ ታሪክ ዘግበላቸዋል። መሥራቹ ዜንዘንዶርፍ ቢሞትም ተከታዩ ትውልድ የአርሱን መርሆዎች በመከተል ለ100 ዓመታት ያልተቋረጠ የፀሎት ሰንሰለትን አንደቀጠሉና ያ ፀሎት ደግሞ የወንጌል ተልዕኮውን አሳት ሳይበርድ እንዲቀጣጠል አድርጎ ነበር።

ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ ያስተማረው የፀሎትና የወንጌል ተልዕኮ አንቅስቃሴ ትምህርት የጥንቷን ቤተክርስቲያን የነጠረች፣ የጠራችና ተልዕኮዋን በትክክል የተወጣች እንድትሆን አድርጓታል። እኛም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ወደ 30 የሚጠጉ የጸሎት እካሄዶችን በትክልል በማጤንና ተግባራዊ ብናደርጋቸዉ ውጤታማ የፀሎት አገልጋዮችና በፀሎት ተገልጋዮች አንሆናለን። ደግሞም በእገራችንም ታላቅ የጸሎት ንቅናቄ ይነሳል የሚል ትልቅ እምነት ይኖረኛል።

፩. እግባባዊ በሆነ የፀሎት ቅደም ተከተል መፀለይ

ፀሎት ማለት ስጠኝና አምጣ ላይ የተመሠረተ መጠይቅ ሳይሆን ማዕከላዊ ጉዳዩ እምልኮ ነው። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ግንኙነትን መፍጠር ነው። ለዚህም ጤናማ የፀሎት ሕይወት የሚከተሉ ቅደም ተከተላዊ የፀሎት ሂደቶች ያስፈልጉናል።

፩.፩ የአምልኮና የውዳሴ ፀሎት

ይህ ቀዳሚው የፀሎታችን ክፍል ነው። ይህ ማለት ብዙ ነገሮችን ያካትታል። የዚህ ፀሎት ዋናው ክፍል በእግዚብሔር ማንነት ላይ በማተኮር መፀለይ ማለት ነው። ስለ ታላቅነቱ፤ ክብሩ፣ ኃይሉ፣ ችሎታው

ማለትም የርሱ የሆነውን ሁሉ በተግባርም በቃልም ሰርሱ መስጠትና መናገር ማለት ነው (ኢሳ 40፡1-31) ። በተግባር ስንል ሁለት ነገሮችን መረዳት ያስፈልገናል እላለሁ።

የመጀመሪያዉ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ማንነት በትክክል በመረዳት በታላቅ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ በፊቱ መሆን ነዉ፡- «የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁ እርሱ የሠራዊት ጌታ እግዚብሔር ይሁን ... » ይላልና (ኢሳ 8፡12)፤ ከማንም ከምንም ይልቅ የእግዚአብሔርን በላይነት ማንዘቢ ውስጥ በማስገባት ሰእርሱ ከውጪ ሳይሆን ከውስጥ የሆነ አምልኮ መስጠት ነው። ስለዚህም በውጫዊ አካላችን የእርሱን አስፈሪነት፣ አስደንጋጭነትንና ታላቅነትን በውል በመረዳት በፊቱ ተንበርከክን፣ ወድቀንና ተደፍተን የምንፀልየው ፀሎት ነው። ነቢዩ ዳንኤል በዳን 10፡5-9 ባለው ክፍል የጌታ ኢየሱስን መለኮታዊ ክብር ባየ ጊዜ ኃይል ከድቶት *በግምባሩ እንደተደፋ* እናያለን። ጳውሎስ ደግሞ በሐዋ 9፡1-9 የጌታ ክብር ከላይ ባንፀባረቀበት ጊዜ *በምድር ላይ ወድቆ እንደተንቀጠቀጠ* እናያለን። አንዲሁም ሐዋርያት ኢየሱስ ከርስቶስን በተራራ ላይ ሲፀልይ የፈቱ መልክ ተለውጦ ልብሱም ተብለጭልጮ ባዩና እርሱን ሰሙት የሚል ድምጽ ከሰማይ በስሙ ጊዜ «በግምባራቸዉ ወደቁ እጅግም ፈሩ» ይላል (ማቴ 17፡1-8)። ሐዋሪያው ዮሐንስም በፍጥሞ ደሴት እያስ በጌታ ቀን በመንፈስ ሆኖ ጌታ ኢየሱስን በታላቅ ክብሩ በራዕይ ባየ ጊዜ እንደሞተ ሰው ሆኖ ወደቀ (ራዕይ 1፡10-20)። ስለዚህ ይህ ዓይነት የጌታ መገለጥ ካለ በእግዚአብሔር ፊት መዉደቅ፤ መንበርከክና መደፋት ፈጽሞ ጥያቄ ሊሆን የሚችል ጉዳይ እይደለም። ከላይ የተጠቀሱ የእግዚአብሔር ስዎች በሚያስፈራዉ በእግዚአብሔር ፊት የቀረቡት እቀራረብ ትክክለኛ አምልኮ እንዳቀረቡ የሚያሳይ ነው። በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ውስጥ ሆነን የእግዚብሔርን ትክክለኛ ማንነት በመረዳት በፊቱ በመፍራት (በአምልኮ) የምንሆንበት አቀራረብ በዚህ መልክ ነው።

ሁለተኛዉ ስለማንነቱ በክንፈራችን ወይንም በምላሳችን በመናገር የምናደርገዉ አምልኮ ነዉ፡- እግዚአብሔር እርሱን የምንወድበትንና እርሱን የምናመልክበትን አምልኮ በቃላቶቻችን መግለጽ በጣም አስፈላጊ ነው። እርሱም ይወደዋል። በተለይም የእግዚአብሔርን ምህረትና ፍቅር በመረዳት የምንፀልየው ፀሎት ጌታን ለኛ ማን መሆኑን የበለጠ ያሳየናል ማለት ነዉ።

1.2 የንስሃ ፀሎት

በኢሳ 6:5-7 መሠረት አምልኮ አግዚአብሔርን ያሳየናል፤ ንስሃ ግን እኛን ያሳየናል:: ስለዚህ የንስሃ ጸሎት ከአምልኮ ጸሎታችን ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ መፀለይ ያለብን የፀሎት ዓይነት ነው:: ከላይ አንዳየነዉ ሁሉ አግዚአብሔርን በትክክል የሚያይ ሰው የራሱን ማንነት ለማየት ጊዜ አይፈጅበትም ወይም አይቸገርም:: ዛሬ በትዳር መካካል፣ በቤተክርስቲያን፣ በመንፈሳዊ ድርጅቶችና በተለያዩ በሥራ ቦታዎች የሚታዩ የእርስ በእርስ መወነጃጀሎች ምክንያቱ አግዚአብሔርን በማንነቱ ያያና የተረዳ ትዉልድ እያነሰ በመሄዱ ይመስለኛል::

የንስሐ ፀሎት ማለት:-

- የራሳችንን ኃጢአት መናዘዝ
- ቤተሰብን ወክሎ የቤተሰብን ኃጢአት መናዘዝ
- ቤተክርስቲያንን ወክሎ የቤተክርስቲያንን ኃጢአት መናዘዝ
- ያለንበትን ከተማ /ዞን/ቀበሌ/ ወክለን የከተማችንን/የቀበሌችንን ኃጢአት መናዘዝ
- አገርን ወክለን የአገራችንን ኃጢአት መናዘዝና
- በዓለም ያሉትን ቅዱሳንንም ሆነ ያለመኑትን ወክለን ስለነርሱ መናዘዝ ነዉ:: ስለዚህ በትክክል ስናመልከና ስንናዘዝ ከአግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ፍጹም ጤናማ ስለሚሆን ከዚያ ቀጥሎ የምንፀልየው ፀሎት በሙሉ ውጤታማ ይሆናል::
- በዳን 9:1-27 ላይ ዳንኤል በራሱና በሕዝቡ ኃጢአት ሲናዘዝ የአግዚአብሔር መልአክ መጣ:: ዳሰሰዉ:: አስተማረዉ:: ማስተዋልንም ሰጠዉ:: እጅግ የተወደደክ ሰዉ ዳንኤል ሆይ በሚል ሰም እግዚአብሔር ጠራዉ:: ታላቅ ምስጥርንም (አስክ ዛሬ ድረስ ያልተገለጠዉን) እሳየዉ:: 'ታዲያ ንስሃ በጸሎታችን ዉስጥ ያሰዉ ሚና እጅግ ታላቅ በመሆኑ ስለራሳችንና በሌሎችም ፋንታ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት በንስሃ ጸሎት መቆም ትልቅ በረከት ነዉ::

1.3 የምስጋና ፀሎት

ምስጋና እግዚአብሔር ስለ ሰጠን በጎ ስጦታዎች ሁሉ ማለትም በመንፈሳዊም ሆነ በተፈጥሮ፣ በግልና በጋራ አግዚአብሔር ላደረገልን ነገር ሁሉ አድናቆትን ማቅረብ ማለት ነዉ:: ፀልየን ጌታ ለመለሰልን

መልሶች በሙሉ ጌታን ማመስገን አለብን:: በመዝ 50:23 ላይ «ምስጋናን የሚሰዋ ያከብረኛል የእግዚአብሔርንም ማዳን የማሳይበት መንገድ በዚያ አለ» ይላል:: ጌታ ላደረገልን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ፀልየን ላልመለሰልንና መልስ ሳይመጣ ለዘገየባቸው ነገሮች በሙሉ አግዚአብሔርን ማመስገን አለብን:: ምክንያቱም የሚዘገይበት ምክንያት አግዚአብሔር ነገርን ሁሉ በጊዜው (ነገሮቹ መፈጸም በሚገባቸው ትክክለኛ ሰዓት) ውብ አድርጎ ስለሚመልስ ነው (መክ. 3:11):: ያግሞ አግዚብሔር ፀልየን የማይመልስልን ምክንያት ቢኖር አርሱ የማይከብርበትና ለአኛም ጥቅም ስለማይሆን ነዉ:: ስለዚህ ቶሎ ለተመለሰው መልስ አግዚአብሔር ይመስገን:: ሳይመለስ ለዘገየውና ለቀረውም አግዚአብሔር ይመስገን::

1.4 የምልጃ ፀሎት

ምልጃ ማለት ሌላውን ሰው ወይንም አገርን ወክሎ ወደ አግዚአብሔር በፀሎት መቅረብ ማለት ነው:: ጳውሎስ ... ምልጃም ... ለሰዎች ሁሉ ... እንዲያደርጉ ከሁሉ በፊት እመክራሰሁ ይላል (1ኛ ጢም 2:1-2)::

የምልጃ ፀሎት አገልግሎት በጣም ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል የፀሎት አገልግሎት ነው:: ስለቤተሰብ አባላት፣ ስለ ቤተክርስቲያን ምዕመናን፣ በሥራ ቦታ፣ ለምናገናኛቸው ሰዎች ስለ አገር መሪዎችና ስለ አገራችን፣ ስለ አህጉራችንና አለማችን አጠቃላይ ሁኔታ መጸለይ ማለት ነዉ:: ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለቤተክርስቲያን እገልጋዮችና ወጥተው በወንጌል ሥራ ላይ ስተሰማሩት፣ በቅርብም በሩቅም ላሉ ለምናወቃቸው ቅዱሳን፣ አየጠፉ ላሉ ሰዎች፣ ወንጌል ላልገባቸው ብሄረሰቦች፣ አካባቢዎችና አገሮች ወዘተ በአግዚአብሔር መንፈስ ሆነን መቃተት ማለት ነው:: የምልጃን ፀሎት ሊያካሄዱ የሚችሉት በህይወት ያሉ ቅዱሳን አንጂ የሞቱ ቅዱሳን ሆኑ መላዕክት አይደሉም:: የምልጃን ፀሎት ከሌላው ልዩ የሚያደርግ ነገር ቢኖር የፀሎት አገልግሎታችንን ወደ ጌታ ኢየሱስና ወደ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከፍ ማድረጉ ነው:: ምክንያቱም በሮሜ 8:26 ላይ «መንፈስ ቅዱስ ራሱ <u>በማይነገር መቃተት ይማልድልናል</u>» ይልና፤ ሮሜ 8:34 ላይ ደግሞ «... ከሙታን የተነሣው በአግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ <u>ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው</u>» ይላል:: ስለሆነም የብዙዎችን ሸክም ተሸክመው በምልጃ ፀሎት በዕምባ የሚቃትቱ በሙሉ በጸሎት አኳያ ጌታ ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ የሚሰሩትን ሥራ የሚሠሩ ናቸው ማለት ነው:: ስለዚህ የምልጃ ፀሎት ባለሸክም ያደርገናል፤ ህዘንተኛም ያደርጋል (ሮሜ 15:1):: አልቃሻ

ያደርጋል፣ በሃሌሉያ ፋንታ ወዬው ያሰብሰናል። ምክንያቱም በኃጢአተኞች ላይ የአግዚአብሔር ቁጣ አስከፈነቱና ሞተው ገሃነም የሚገቡ ሰዎች ብዛትና የዘላለም ሞት እስቃቂነቱ ይታያቸዋልና።

በዛሬ ጊዜ እጅግ አሳዛኝ የሆነው ጉዳይ ቢኖር የአንዳንዱ እጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚታይ የፀሎት ፕሮግራሞች ከጅማሬ አስከ ፈጻሜ ንግግርና ጩኸት ብቻ መሆኑ ነው። እንደሚመስለኝ ወደ ኢየሩሳሌም ሕዝቡ የዘንባባ ዝንጣፊና ልብስ እያነጠፉለት ሆሳዕና እያሉ ሲዘምሩ ኢየሱስ የኢየሩሳሌምን ከተማ እያየ ያለቅስ ነበር። እንዲሁም በአብዛኛው የምናካሄዳቸው እምልኮ ዝማሬዎችና የፀሎት ፕሮግራሞች የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሳትን ይመስላል። ለቅሶ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሃሌሉያ እያልን እንዘላለን። ሕዝብን የሚያባብል ሰብከት እየሰበክን እናስቃለን። ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የሚያስለቅስ ትልቅ ሸክም ይዘን በጌታ ፊት መቃተት ያሰብን ዘመን መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። እንድንጸልይ የሚያስገድዱን ተግዳሮቶች በሚል ምዕራፍ ሥር የተጠቀለሉን ሀሳብ በደምብ እንይ። ጨምሬ ሰመጥቀስ ያህልም በዓለም ካለው ህዝብ 90% ያህሉ ጌታን የማያውቅ ነዉ። በየቀኑ 163,000 ሰው ይሞታል። ከዚያ ህዝብ መካከል 90% ሰው ያላመነ ከሆነ በዓመት ሲሰለ 53,000,000 (አምሳ ሦስት ሚልየን) የሚያህል ሕዝብ በየዓመቱ ወደ ገሃነም እየገባ ነዉ። በጣም የሚገርመው አንድ ሰው በመኪና አደጋ ከሞተ አገር ሁሉ ያለቅሳል። ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ የሞቱ ጊዜ እገር አልቅሷል። አዎን ሞት ያን ያህል ከባድ ከሆነ በአንዱ ዓመት እግዚአብሔር የፈጠረው እስትንፋሱን የሰጠዉና ልጁ ኢየሱስ ከርስቶስ የሞተለት ከላይ የተጠቀሰውና ከዚያም በበለጠ እሃዝ ያለዉ ህዝብ እየሞተ ገሃነም ሲገባ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ሰቆቃ እንደሚሆንበት ብንረዳና ብናውቅ ኖሮ የምንበለው፣ የምንጠጣውና የምንለብሰው ባላረካን ነበር። እግዚአብሔር ባሰ ሸክም ትውልድንና በዓለም ላይ በየዕለቱ እየተከሰተ ላለው ሰቆቃና መከራ አልቃሾችን ይፈልጋል። እነዚያ ውስጥ እንዱ ያድርገን! ስለዚህ ዉጤታማ ጸሎተኞች ለመሆን በሚገባ የጸሎት ርዕሶችን የምንይዝበት ጥሩ ማስታወሻ በግልም በሕብረትም ያስፈልገናል። የጸሎት ርዕሶችን በመዘርዘር በሥርዓት ብንጸልይ የጸሎቱ መልስ እንደተመለሰ ደግሞ ጌታን እናመስግናለን ማለት ነዉ። የበለጠም ለመጸለይ ልባችን እየተነሳሳ ይሄዳል።

1.5 የልመና ፀሎት

ይህ ስለግል ጉዳዮቻችን የምንፀልየው ፀሎት ነው። አብላጫው ከርስቲያን አብዛኛው የፀሎት ሰዓቱን የሚጨርሰው በዚህ ፀሎት ላይ ነው። ምክንያቱም በባህሪያችን ራስ ወዳዶች ስለሆንን ነው። ለሰዎችም የምንሰጠው የፀሎት ርዕስ 99ኙ% ስለራሳችን ነዉ ቢባል ማጋነን አይመስለኝም። ይህ ጸሎት እስፈላጊ ቢሆንም ከ1.1-1.4 የተጠቀሱ በአምልኮ፣ በንስሃ፣ በምስጋናና በምልጃ ፀሎቶች ላይ አበዛኛዉን ጊዜ በጸሎት ማጥፋት አለብን። ያንን እድርገን ስለራሳችን ባንፀልይ እንኳ የእኛን ሥራ ጌታ ይሠራል። ትልቁ ትኩረታችን እግዚአብሔርን ማምለክ ይሁን። እንዲሁም ለሌሎች በመቃተት ስንፀልይ መንፈስ ቅዱስና ጌታ ኢየሱስ ስለእኛ ይማልዱልናል። ያጠን አንሆንም ጌታ ስለእኛ ያስባልና (ነጴጥ 5:7)

1.6 የግሳፄ (የተቃውሞ) ፀሎት

ይህ ፀሎት ጥቅሙ እሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ያለውን በግልጽም የሚዋጋንን፣ በተለያዩ ቦታዎች፣ ሰዎች ላይ እየታየ ያለውን የጠላትን አሠራር የምንቃውምበት ፀሎት ነው። አብዛኛውን የፀሎት ጊዜያችንን በዚህ ፀሎት ላይ ማጥፋት ባያስፈልገንም ጠላት ዲያብሎስን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አጥብቀን መቃወም አለብን። ምክንያቱም ዲያብሎስን እድንተን መቃወም እንዳለብን ቃሉ ያበረታታናል (ነጴጥ 5:8-9)። በዚህ ረገድ ከሁለቱም ጽንፈኝነት መጠንቀቅ አለብን። አንዳንድ ዬኖሚኔሽኖች በመቶና ከዚያ በላይ ዕድሜያቸዉ አንድ ቀን ዲያብሎስን ገስጸዉ እያዉቁም። ያሳዝናል። ሌሎቹ ደግሞ ከጸሎት ሰዓት ጅማሬያቸዉ እስከ መጨረሻ ድረስ በግሳጼ ጀምረዉ ጸሎቱን በግሳጼ ይጨርሳሉ። ሁለቱም ስህተት ነዉ። እግዚአብሔር በፀሎታችን ድል አንደሚያደርግ እያመንን በሚገባም መቃወም አለብን። ደግሞም ስንቃወም የዲያብሎስን ገናናነት እያደነቅን መሆን የለበትም።

ስለዚህ በእነዚህ የጸሎት ዓይነቶች በእግባቡ ለእያናዳንዱ በቂ ጊዜ ሰጥተን እንዲሁም በቅደም ተከተሉ ብንጸልይ እጅግ በጣም ዉጤታሞች እንደምንሆን ፍጹም እምንት ይኖረናል።

2. ተግቶ መፀለይ

የትጋት ፀሎት የሚለው ሁለት ዋና ሀሳቦችን የያዘ ነው:: የመጀመሪያው በፀሎት ሰዓት ሳንደክም ወይንም ጸሎትን ሳናቋርጥ በፅናት መፀለይ ማለት ነው:: የፀሎት ቦታ ማለት ከፍተኛ የሆነ የዲያብሎስ ጦርነት የሚካሄድበት ቦታ ነው:: ነገር ግን ኃጥያትን፣ ሞትንና ዲያብሎስን ያሸነፈ ጌታ ከእኛ ጋር አለ:: የሚያበረታን የእግዚአብሔር መንፈስም ከእኛ ጋር መሆኑን ከተገነዘብን በትጋት መፀለይ ቀላል ይሆንልናል:: ለምሳሌ:-

- የእስራኤል ልጆች ጎልያድንና ራሳቸውን ከጎልያድ ጋር አነጻጽረው ይህንን ፊልስጤማዊ መዋጋት ማን ይችላል አያሉ ባሉበት ሰዓት ላይ እግዚአብሔር በሰንቅ ለበብ ደዊትን ላከላቸው:: ዳዊት ግን ጉልያድንና ራሱን ላይሆን ያየው እግዚአብሔርንና ጎልያድን ነበር:: በዚያን ለዓት ጎልያድ በፊቱ ኢምንት ሆኖ ታየው (1ሳሙ 17)::
- አንዲሁም 12ቱ ሰላዮች ለሰለላ ወደ ከነዓን በገቡ ጊዜ የኤናቅ ለዎችንና የተመሸጉ ከተሞችን አዩ:: አሥሩ ሰላዮች መንገደኛ ከሆነው ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ሲያነፃፀሩ ራሳቸውን የአንበጣን ያህል አሳንሰው አዩ:: ነገር ግን ሁለቱ (ካሌብና ኢያሱ) በዚያ የነበሩትን ኃያላንና እግዚአብሔርን ነበር ያነፃፀሩት:: በዚያን ለዓት እግዚአብሔር ለሁለቱም (ለካሌብና ኢያሱ) የጠላቶቻቸዉን ጥላ አንደተገፈፈ አሳያቸው (ዘኁቁ 13 እና 14)::
- የኤልሳዕ አገልጋይ ግያዝ ተራራውን የሸፈነ የጠላት ሠራዊትንና ሁለት ለዎችን (ራሱንና ኤልሳዕን) ሲያነፃፀር ምድር ብትውጠኝ ይቀለኛል አስከማለት ነበር የተጨነቀዉ:: ነገር ግን ኤልሳዕ የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከሶሪያ አደጋ ጣዮች ጋር ሲያነፃፀር በእርሱ ዙሪያ ያለዉ የእግዚአብሔር ሠራዊት እጅግ አይሎ ተመለከተ:: ከዚያም በኋላ ኤልሳዕ ከብዙዎቹ የሶሪያ አደጋ ጣዮች ይልቅ እጅግ የሚበልጣውን የእግዚአብሔርን ሠራዊት የግያዝን አይኖች አንዲመለከቱ ፀለየለት:: ግያዝ አይኖቹ ተከፍተዉ የእግዚአብሔርን ሠራዊት ባየ ጊዜ እጅግ ተጽናና:: ስለዚህ የሥጋችንን ደካማነት ከጠላት የረቀቀ ጥበብና ብርታት ጋር ካነፃፀርን በቶሎ ተስፋ እንቆርጣለን:: ነገር ግን ከእኛ ጋር ያለውን ጌታ ካየን ዘወትር ትጉዎች እንሆናለን (ማር 13:32-37 ሉቃ ፲፡1-3፣18:1-8)::

ሁለተኛው የትጋት ዓይነት የሚያሳየን ፀሎት የያዝ ለቀቅ ሥራ መሆን እንደሌለበት ነዉ:: ነገር ግን የዘወትር ማለትም የሌትና የቀን፣ የከረምትና

የበጋ፣ የወጣትነትና የጉልምስና ዘመን ብሎም አለከ እርጅና መቀጠል ያለበት ታላቅ አገልግሎት ነው:: በየዘመኑ ፀሎት የአንድ ወቅት መነቃቃት ሆኖ ይታያል:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ሁሌ አንድንተጋ ነው:: በሉቃ 18:7 ላይ «ቀንና ሌሊት ወደ እግዚአብሔር ለሚጮሁ ለምርጦቹ እግዚአብሔር ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል» ይላልና:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ያለተማረንን በተግባሩም ያላየንን አውነት አጥብቀን በመያዝ ሁልጊዜ መትጋት አድል ፈንታችን ይሁንልን::

3. ረዥም ለዓት ፀሎት

ሰይጣን በመጀመሪያ ደረጃ የሚተጋዉ ማንም ከርስቲያን አንዳይፀልይ በማድረግ ነው:: ነገር ግን ከቃሉም በመረዳት ይሁን፣ መንፈስ ቅዱስ አሳሰቦትም ይሁን፣ ወይንም ከተማረው ትምህርት ይሁን፣ አንዲሁም ከሰልጠናና ኮንፍራንስ መልዕክት የተነሣ ይሁን ቃል በመግባት መፀለይ ከጀመርን ያንን ፀሎት አንድናቋርጥ ሰይጣን የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም:: አንዲያውም በዚያ ከርስቲያን ላይ የከተት ጦር አዋጅ ያዉጅበታል:: ከዚህ የተነሣ ነው ብዙ ከርስቲያኖች በጀመሩት የፀሎት ልምምድ መቀጠል ሲያዳግታቸው የምናየዉ::

ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የቆይታ ፀሎት አሰፈላጊና ውጤታማ ያደርገናል:: ለምሳሌ መዝሙረኛው ዳዊት ሲናገር «ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት፤ አርሱም ዘንበል አለልኝ፤ ጩኸቴንም ሰማኝ፤ ከጥፋትም ጉድጓድ፣ ከረግረግም ጭቃ አወጣኝ፤ አግሮቼን በድንጋይ ላይ አቆማቸው፤ አረማመዴንም አፀና፤ አዲስ ዝማሬን ለአምላካችን ምሊጋና በአፌ ጨመረ፤ብዙዎች ያያሉ፤ ይፈሩማል፤ በእግዚአብሔርም ይታመናሉ» ይላል (መዝ 40:1-3) :: የቆይታን ፀሎት ምንነት በሚገባ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ጥቂት ምሳሌዎችን አስቲ ላንሳ:-

3.1 ንግግራችን ከአፍቃሪ አምላካችንና አባታችን ጋር ነዉና

መቼም ከሚያፈቅረው ጓደኛ ጋር የሚያወራ ለው ምንም ያወራ ላይመስለው ሰዓት ያልቅበታል:: ምክንያቱም የንግግሩ ረዥምነት ምክንያቱ የጠለቀ ፍቅር ስለሆነ ነው:: በትክክል እግዚአብሔርን አናፈቅራለን የምንል ከሆነ ከእርሱ ጋር ያለን ንግግራችን (ፀሎታችን) በፍጹም አጭር አይሆንም:: ሁለት የተፈቃቀሩ ጓደኛሞች ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፆታዎችም ቢሆኑ ንግግራቸው ሁልጊዜ ረዥም ነው::

ተፈቃሪዎቹ ሁሌ ንግግራቸዉ ትርጉም አለዉ። አግዚአብሔር ከአፍቃሪ ወላጆች ሁሉ ይልቅ አፍቃሪ በመሆኑ፣ ወላጅ ደግሞ ምንም ዓይነት ቢሆን የልጅ ንግግር ለለሚጣፍጠዉ በአግዚአብሔር ፊት ቃላትን ሳንመርጥ በፀሎት ሰዓት የምንናገረው ሁሉ ይገባዋል፤ ደስም ይለዋል። ስለሆነም ፀሎት የ10 ደቂቃ ንግግር ሳይሆን ከአምላካችን ጋር ስዓታትን የሚፈጅ መንፈሳዊ (መለኮታዊ) ጫዋታ መሆን አለበት።

3.2 በአግዚአብሔር መንፈስ ተጽዕኖ ዉስጥ ሆነን ስንጸልይ

የፀሎት መንፈስ በእኛ ላይ የሚንቀሳቀስ ከሆነ ረዥም ሰዓት መፀለይ በጣም ቀላል ይሆንልናል። ምክንያቱም ፀሎት የሚያለደስተን መቼ ነው ቢባል መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሆኖ ሲፀልይ ነው። አለበለዚያ ፀሎት ተራራን የመግፋት ያህል ይከብድብናል። ስለዚህ ነዉ ጳዉሎስ በሮሜ 8፡26 ላይ መንፈስ ቅዱስ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ያለዉ።

3.3 ለሚጠፉት ነፍሳትና በዓለም ላለው ችግር ስንፀልይ

ለሚጠፉት ነፍሳትና በዓለም ላለው ችግር ስንፀልይ የፀሎት ሰዓት በጣም ያንስብናል። በዓለም ላይ 6.3 ቢልየን ሕዝብ ጌታን ያልተቀበለ መሆኑ ቀርቶ ባስንበት ቤተሰብና ከተማ ብዙ ሰዓት ወስደን እንድንፀልይ የሚያደርግ አጅግ ብዙ የጠፉ ነፍሳት አሉ። ደግሞም ቃላት ሊገልጹ የማይችሉት ብዙ ችግርና በተለያዩ አገሮች አካባቢዎች በስደት ላይ ያሉ ቅዱሳን ብዙ ስለሆኑ የፀሎታችን ሰዓት ማጠር የለበትም።

3.4 የፀሎት ምንነት በትክክል ስንረዳ

የፀሎት ምንነት በትክክል ከገባን ፀሎት በእርግጥ ጣፋጭ ይሆናል። ከርስቲያን ከተንበረከከ በኋላ ስውነትን በማዛል ይሁን በማድከም ቶሎ ብሎ ከተንበረከከበት አንዲነሳና ፀሎቱንም አንዲያቋርጥ ሰይጣን የማያደርገው ጥረትና የማፈነቅለዉ ድንጋይ የለም። ብዙ ጊዜ ሰይጣን በሥጋችን በኩል አድርጎ ለሚመከረን ምክር በቀላሉ ታዛዦች እንሁን። ስለዚህ ጉልበታችን ቢደክምም የፀሎት ፈላጎት ባይኖረንም የቆይታ ጸሎት ለማድረግ ዉሳኔና አቋም ያስፈልገናል።

4. የአዳር ፀሎት

በ1800 ዓ.ም በአሜሪካና አገር ከንታኪይ በሚባል ግዛት ማግሬዲይ የሚባል ለው በቤተክርስቲያኑ ከቅዳሜ 12 ለዓት አለከ እሁድ አሥራ ሁለት ሰዓት በመፀለይ የቤተክርስቲያን ምዕመናን ለፀሎት ያንቀሳቅስ በነበረበት ወቅት አግዚብሔር ታላቅ መነቃቃትን አስነስቶ ነበር ይባላል። ከዚያ በኋላ በጥቂት ጊዜ ውስጥ አሥራ አንድ ሺህ ሰዎች ወደ ጌታ የመጡ ሲሆን የዚያው ያህል ሰዎች የጌታን አራት ይካፈሉ አንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ ደቀመዝሙርቱን ሐዋርያት የሚል ስያሜና ሹመት ከመስጠቱ በፊት ሌሊቱን ሙሉ አንደፀለየ በሉቃ 6፡12 ላይ ይገልጻል። አንዲሁም ጴጥሮስ በታሰረበት ወቅት ሐዋርያትና ሌሎች ቅዱሳን ሌሊቱን በምልጃ ሲጸልዩለት የጌታ ጣልቀገቢነት ሆነና ጴጥሮስ ከአስርቤት ወጣ (ሐዋ. 12፡5)

ከ1976-1983 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ከፈነዳው አብዮት ስደት የተነሳ ቤተክርስቲያናት የአሁድ አምልኮ ፕሮግራሞቻቸው ሳይቀር ሊዘጉባቸው አጠቃላይ ፕሮግራሞቻቸውን ወደ ሌሊት አዙረው ነበር። በዚያም አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች አዳር ፀሎት ይካሄድባቸው ነበር። አነዚያ የአዳር ፀሎቶች ቅዱሳን የመከራውን ዘመን አንዲሻገሩ አድርገዋቸዋል። እኔ ራሴ በዚያን ዘመን በተወለድኩበት አካባቢ በነበርኩበት ጊዜና በባሌ ሮቤ ከተማ በነበርኩባቸው ጊዜያቶች በየሳምንቱ አናደርግ የነበረው የአዳር ፀሎት አሁንም ትዝ ይለኛል። ዛሬ በባሌ አካባቢ ቤተክርስቲያናት አንዲወለዱ፣ አንዲያድጉና አንዲበዙ ያደረገው ያኔ ጥቂት ቅዱሳን በትጋት ያደረጉትን ፀሎት ጌታ ቆጥሮ ነዉ አላለሁ። ቤተክርስቲያናት የአዳር ፀሎቶች ያስፈልጓቸዋል። ተራራን የመውጣትን ያህል አንዲከብድብን አያስፈልግም። በአርግጥ ብዙ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ሆኖም ግን ችግር ሊከሰት ይችላል በሚል ለበብ የአዳር ፀሎትን መተው የለብንም። ለምሳሌ በቤተ ከርስቲያን ዉስጥ የአናት ሌቶች አዳር ፀሎት፣ የወንድ ወጣቶች አዳር ፀሎት፣ የሴት ወጣቶች አዳር ፀሎት፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች አዳር ፀሎት፣ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች አዳር ፀሎት፣ የአብያተክርስቲያናት አገልጋዮች አዳር ፀሎት፤ የቤተክርስቲያን የጸሎት ቡድኖች አዳር ጸሎት፤ የየአገልግሎት ዘርፎች አዳር ጸሎት አና... ያስፈልጉአታል። በዚህ መንገድ ቤተክርስቲያንን ከአደጋ አንታደጋታለን።

5. የፀሎት ቡድኖች ፀሎት

በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተጠናከረ (የተደራጀ) የፀሎት ቡድኖች እንዲኖሩት ያስፈልጋል። ይህ እንዱ እንዲያዉም ዋናው የቤተክርስቲያን እገልግሎት በመሆኑ ቤተክርስቲያን ትልቅ ትኩረት በመስጠት የፀሎት ሽክም ያላቸውን ሰዎች በመመልመል የፀሎት ቡድን በማድረግ የፀሎትን አገልግሎት ማጠናከር አለባት። ኤድዊን ኦር (Edwin Orr) የሚባሉ ሰው ሲጽፉ «በየትኛውም ሥፍራና አገር የተነሡ መነቃቃቶችና የተሃድሶ አንቅስቃሴዎች የጀመሩት በመንፈስ ቅዱስ ምረት ተቀናጅተው ልባቸውን አንድ አድርገው በፀለዩት <u>የቅዱሳን የፀሎት ሕብረት</u> ነው» ብለዋል። ይህን ሀሳብ ተቀብለው በተግባር ላይ ባዋሉ በጆናታን ኤድዋርድ (Jonathan Edward) ምክንያት ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት በአሜረካን አገር ተነስቶ እንደነበር ታሪክ ያወሳል።

6. የ24 ሰዓት የሰንሰለት ፀሎት

በዚህ ጽሑፍ ላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በ1722 ዓ.ም በጀርመን አገር የተነሣው የ24 ሰዓት የፀሎት አንቅስቃሴ ለ100 ዓመታት የዘለቀ የወንጌል ተልዕኮ ንቅናቄን ለመፍጠር ምክንያት ሆኖ እንደነበር ተመልከተናል። ከዚህ የምንመለከተው ለ24 ሰዓት በማይቋረጥ ፀሎት አማካኝነት የማያቋርጥ የእግዚአብሔር ጉበኝት ይሆናል ማለት ነዉ። በእንዲህ ሁኔታ ውስጥ ሰይጣን ተረጋግቶ ከፉ ሥራውን ለመሥራት ዕድል ያጣል። በዘፀ 17፡11 «ሙሴ እጆቹን ባነሣ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር። እጁን ባወረዳ ጊዜ ግን አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር» ይላል። ይህ የሚያላየን የማይቋረጥ የተጠናከረ ፀሎት በሚኖርበት ሰዓትና ዘመን የጠነከረና የበረታ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ይሆናል። ነገር ግን ፀሎት በተዳከመ ቁጥር ሰይጣን ሥራውን ለመሥራት ዕድል ይኖረዋል ማለት ነው። በአጠቃላይ የከርስቶስ ቤተክርስቲያን በተቻለ መጠን አጠቃላይ ምዕመኖችዋን 24ቱን ሰዓታት ለጸሎት ብትደለድልና በዚያው መልክ ብትሰራ ከአካባቢዋ አልፋ ለሌሎችም አሰገራሚ መንፈሳዊ ውጤቶችን በእርግጥ ታመጣለች ብዬ አምናለሁ። በአሁን ሰዓት በብዙ በታዎች አበረታች የሆኑ የ24 ሰዓታት እንቅስቃሴዎች በአገራችንና ከአገራችንም ዉጪ አየታዩ ስለሆነ ጌታን እናመሰግናለን። ነገር ግን በየአካባቢዉና በየአጥቢያዉ እንደሚገባ አጠናክረን ብንጀምርና ብንቀጥል ታላላቅ ታምራቶችን እናያለን።

7. የጉዞ ፀሎት

«እግሮችህ የሚረግጡበትን ሥፍራ ሁሉ ለአንተ አስጣለሁ» ብሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ እንደተናገረ (ኢያሱ 1፡3) በጌታ ሰም እየረገጥን የምንፀልይባቸውን በታዎችን በሙሉ ጌታ ይስጠናል። የስህተት ሃይማኖቶች፣ ዓመጸኛ መንግስታት፣ እግዚአብሔር የማይከብርባቸው የሰውም ሆነ የሰይጣን መዋቅሮች፣ ርግማንን መሠረት ያደረጉ ባህላዊ ልምምዶች፣ የጥፋት መልዕክት አስተላላፊ የሆኑ ተቋሟትና ድርጊቶች፣ የጥንቆላ ቤቶች ... ወዘተ በሙሉ የእግዚአብሔር ከብር እንዳይገለጥ፣ ቤተክርስቲያን እንዳታድግ፣ ወንጌል እንዳይሰራጭና እንዳይሰበክ፣ ቤተክርስቲያን እንዳትተከልና አገር በጤናማ ኢኮኖሚ እንዳያድግ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው። በመሆኑም በኤር 1፡9 «አነሆ ቃሌን በአፍህ አኑሬያለሁ፦ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ ታጠፋና ትጣሰጠ ዘንድ ትሰራና ትተከል ዘንድ በአህዛብና በመንግስታት ላይ ዛሬ አድርጌሃለሁ» የሚል መለኮታዊ ሥልጣን ተሰጥቶናል። ስለዚህ በኢየሱስ ሰም የማይገለበጥ የዲያብሎስ መንግሥትና ሥራ የለም። በአስቴር፣ በመርደክዮስና በእስራኤል ህዝብ የተባበረ ፀሎት የሐማ የተንኮል እቅድና ፕሮግራም ተገልብጧል። (አስቴር 1-10 ሙሉ ሀሳቡን ለማግኘት ምዕራፎቹን በሙሉ ብናነብ የተሸለ ነው)። ዛሬም በአግራችን እየተጓዝን የዓመጽ አሠራሮች ያሉባቸውን የሐሺሽ፣ የአልኮል፣ የቁማር፣ የዝሙት፣ የመተትና የጥንቆላ ቤቶች እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩ አካባቢዎችና በታዎች ላይ በመንቀሳቀስ ያለ መታከት ብንፀልይ የአመጽ ድርጅቶች በሙሉ ይፈርሳሉ። በፈንታው የእግዚአብሔርን የጽድቅ መንግስት እንተከላለን። በታሪክም ሆነ ዛሬ በግልጽ እንደምናየው እንደዚህ ዓይነት የበረቱ የአመጽ አሠራሮች ባሉበት አካባቢ ያሉ የማይፀልዩ ቤተክርስቲያናት ቢኖሩ እያደር ሸባ ይሆኑና በቆይታ መዘጋታቸው አይቀሬ ነው። ስለዚህ በመኪና፣ በብስክሌት፣ በእግር ... እየተጓዝን ወደ ሀብረተሰብ እጆቻችንን እየዘረጋን መባረክ አለብን። በዚያን ሰዓት የጥፋት ልጅ ዲያብሎስ የተቆጣጠራቸውን ይለቃቸዋል። ቀንበሮቹ ሁሉ ይሰበራሉ። ጽድቅ ያብባል፣ ይነግሳልም።

8. የፆም ፀሎት

«ይህ ወገን በፀሎትና በፆም ካልሆነ በቀር በሴላ በምንም ሊወጣ አይችልም በማለት በማር 9፡29 ላይ ጌታ ራሱ የረቀቀ፣ ኃይለኛና የበረታ የዲያብሎስ አሠራር በፆም ፀሎት ብቻ እንደሚሸነፍ አረጋግጦልናል።

አንዲሁም በማር 2፡18 ላይ ፈሪሳውያንና የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ይጾሙ ስለነበር አንድ ቀን ወደ ኢየሱስ መጥተው «የአንተ ደቀመዛሙርት የማይጾሙት ስለምንድር ነው ብለው በጠየቁት ጊዜ ጌታ ሲመልስ ሙሽራው ከአነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎች ሊጾሙ ይችሳሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከአነርሱ የሚወስድበት ወራት ይመጣል፤ በዚያን ወራት ይጠማሉ» በማለት የፆምን አስፈሳጊነት አረጋግጧል።

በሐዋ ሥራ 13፡1-4 የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የወንጌል ተልዕኮ ሥራ የተጀመረው በፆም ፀሎትና በአውነተኛ አምልኮ ቦታ አንደነበር ቃሉ ይናገራል። በማቴ 6፡16 ላይ *ስትፆሙ* ... አለ አንጂ *ብትፆሙ* እለማለቱ መፆም ጥያቄ የማያስፈልገው አንደሆነ አንመለከታለን። ደግሞም ኢየሱስ 40 ቀናትን በመፆም አገልግሎቱን ጀመረ፤ በአገልግሎቱም መጀመሪያ ላይ ዲያብሎስን ረታው (ማቴ 4፡1-11)። ዳንኤል ከለማይ አምላክ አስደናቂ ምስጥር የተገለጠለት 21 ቀናትን በመፆሙ አንደነበር አናያለን (ዳን 10)። በ3 ቀንና ሌሊት የፆም ፀሎት የአይሁድ ጠላት ሐማ የጥፋት አቅድ ተገልብጦበት የሞትን ጽዋ ተጎንጭቷል። የአስራኤል ህዝብ ጠሳቶች በያሉበት አገር ሁሉ አንዲጠፉ የወጣ የጥፋት ትዕዛዝና አዋጅ ተገልብጧል። ታዲያ ይህን ሁሉ ስናይ አግዚአብሔር የስጠንን ይህንን ታላቅ እድል አለመጠቀም ትልቅ ኪሣራና አለመታደል ነው። የነነዌም ሰዎች የሞት ቅጣት የተገለበጠው በ3 ቀናት ፀሎት ነበር። ያቺ ነነዌ ቢያንስ ብዙ ዓመታትን የምህረት ጊዜና እድል አንዳገኘች ከታሪክ አንረዳለን። አግዚአብሔር የአጭር ቀናትን ፆም ፀሎት በምናሳልፈው የረዥም ዓመታትን ምህረትና የብዙ ዓመታትን መፍትሔ ይስጠናል። የአገልግሎታችን ዘመን ይረዝማል። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በፆም ፀሎት የሚተጉ ግለሰቦችን ቤተክርስቲያናትንና አገሮችን ቃላት ሊገልጡ በማይችሉ ለማያዊና ምድራዊ በረከቶች ይባርካል።

በመሆኑም አንድ እማኝ በሳምንት ቢያንስ ቋሚ የሆነ ቢያንስ የአንድ ቀን ወይም የ2 ቀናት የፆም ፀሎት ልምድ ያስፈልገዋል። ይህንኑ ቤተክርስቲያን ልማድ ሊታደርግ ይገባታል። አልፎ አልፎ ደግሞ በግል፣ በቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያንና በአገር ደረጃ አሳሳቢ ጉዳዮች ሲኖሩ የ3 ቀናት፣የላምንት፣የሁለት ላምንት፣ የሶስት ላምንት፣ የወር፣ የ40 ቀናት የፆም ፀሎት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን የፆም ፀሎቱን ቀናት በሚመለከት አስከ 3 ቀናት ያለ አህል መፆም ይቻላል። ነገር ግን ከ3 ቀናት የሚበልጥ ከሆነ ቀላል ምግብና የተለያዩ ጨጓራን የማይጎዱ መጠጦች ማታ ማታ መጠቀም አስፈላጊ ነው። ዳንኤል በ21 ቀናት ፆም ፀሎት ጊዜያት ዉስጥ

ማለፊያ አንጀራ ወይን ጠጅ በእፌ አልገባም (ዳን. 10) ሲል ይናገራል አንጂ ምንም አንዳልበላ አይናገርም። ኢየሱስ፣ ሙሴና ኤልያስ 40 ቀናትን ያለ ውኃና ያለ ምግብ ቆይተዋል። ነገር ግን ያንን የቆዩት በአግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለነበረ ታላፊነቱን የወሰደው አግዚአብሔር ራሱ ነበር። አኛ ደግሞ አንደ አነርሱ እንሆናለን ብንል ከፍተኛ የሆነ የጤና ቀዉስ (ምናልባት አስከ ሞት የሚያደርስ ችግር) ስለሚፈጠርብን ከ3 ቀናት በላይ ያለ ምግብና ዉኃ ፆም ፀሎት መካሄድ አይመከርም። ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ስለ ጾም ፀሎት ያሉት በጥቂቱ አንደሚከተለዉ አንመልከት፡-

ስማቸዉ *ቢል ቢራይት (BILL BRIGHT)* ይባላል። አርሳቸዉ በአሁን ሰዓት ወደ ጌታ የሄዱ፤ ነገር ግን የታላቁ ተልዕኮ (Campus Crusade/Great Commission) መስራችና ለረዥም ዘመናት ፕሬዝዳንት የነበሩ ለዉ ናቸዉ። አርሳቸው የጀመሩት የወንጌል ስርጭት ሥራ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ አንዲንቀሳቀስ ፆም ፀሎት በቀጣይነት አንደሚያስፈልግ ጌታ አንደተናገራቸዉ ይናገራሉ። ከዚህም የተነሳ ኢ.አ.አ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ለ7 ዓመታት በየዓመቱ 40 ቀናትን በፆም አንደጸለዩ ተናግረዋል። መፆም አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ የአጠቃቀም ጥንቃቄ ደግሞ አስፈላጊ መሆኑን በሚገባ አስገንዝባዋል። የፆማቸውም አጠቃቀም በሚመለከት በሚጸሙበት ስዓት በየማታው ውሃ፣ ፍራፍሬና ጁስ ብቻ ይጠቀሙ እንደነበር ይገልጻሉ። ስለአጠቃላይ ስለ ፆም ፀሎት ልምምዳቸዉ አንደሚከተለዉ አስቀምጠዋል።

- በህገራችን በአሜሪካና በዓለም ላይ ታላቅ መነቃቃት አንዲመጣ የ40 ቀናት ፆም ፀሎት እንደሚያስፈልገኝ ጌታ ተናገረኝ። አኔም ጌታ ለተናገረኝ ቃል ታዛዥ ሆንኩ። ያ ስዓት የአግዚአብሔር ትከከለኛ ጊዜ ነበር። ከዚህም የተነላ ስለ ጸምና ፀሎት አስፈላጊነት በአሜሪካና በዓለም ዙሪያ ያሉ ቅዱላንን በፀሎት ለማነሳሳት ሰል መጽሐፍ ጸፍኩኝ።
- ያም ብቻ ሳይሆን ኢ.አ.አ 1994 ላይ መሪዎችን ከአኔ ጋር በፍሎሪዳ አርላንዶ አብራውኝ ለ40 ቀናት በፆም ፀሎት አንዲጸልዩ ጋበዝኳቸው። አነርሱም ፈቃደኛ ሆነዉ መጡ። ያ የዓለም አቀፉ የፆም ጸሎት ንቅናቄ ጅማሬ ነበር ብዬ አገምታለሁ። የኔም የዘዉትር ፀሎቴና ዋና ትኩረቴ በወቅቱ በምድሬ በአሜሪካ አሳዛኝ በሆነዉ የስነ-ምግባር (የቅድስና) ችግር ይታይ ነበርና። ይህ ችግር መኖሩን በመንፋሴ ሰለተረዳሁ ብቻ ላይሆን በዓይኔም እያያሁ ስለነበር ነዉ።

ከዚህ ፆም ጸሎት በኋላ መንፈሳዊ ለውጥ በብዙ ሰዎች ሕይወት ሲከሰት በዓይኔ አይቻለሁ፡፡ ለዚህም ውጤታማነት በዓለም ላይ ያሉ የሰነ መለኮት ምሩቃን፣መጋቢዎች፣ የቤተክርስቲያን እገልጋዮች በሙሉ በሕይወት ዘመናቸዉ ሁሉ ቢያንስ አንድ ጊዜ የ40 ቀናትን ጾም ፀሎት እንዲጸልዩ እበረታታለሁ ብለዋል፡፡ ስለጾም ፀሎት ጥቅምና እስፈላጊነት የሚቀጥሉ ዝርዝር ሐሳቦችን በመጽሃፋቸዉ አስፍረዋል፡፡ አንዲህ ሲሉ፤ ጾም ፀሎት፡-

- ለሰውነታችን (ለእካላችን) ጤንነት እንኳ በጣም ጠቃሚ መሆኑን፤
- ከእግዝአብሔር ጋር ያለንን መንፈሳዊ ግንኙነት ከመቼም የበለጠ የተጠናከረ እንደሚያደርግ፤
- በእገር እቀፍና በዓለም እቀፍ ያለውን የወንጌል ተልዕኮ እካሄድን በጣም የሚያጠናክርና በጣም የሚያፋጥን መሆኑን፤
- ከርስቲያኖች እርስ በርሳቸውና ከእግዝአብሔር ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በጣም እንደሚያጠናክር፤
- የባለትዳሮች እርስ በርስ የሚኖራቸውን ግንኙነትና ሕብረትን እጅግ በጣም የተጠነከራ እንደሚያደርግ፤
- የክርስቶስ እካል የሆነችው ቤ/ክ በቁጥርና በጥራት (ከ Quantity and Quality) ከማደጓም በላይ አንድነቷ በማንም በምንም የማይደፈር ጥንካሬ እንዲኖራት እንደሚያደርግ፤
- እግዝአብሔርን በመንፈስና በእዉነት ለማምለክ እንድንችል እንደሚረዳን፤
- በሕይወታችን የተለማመድናቸው መጥፎ ልማዶች ለመስበር ልዩ ጉልበት እንዳለዉ፤
- ራሳችንን ለመግዛት ማለትም ሥጋዊ ስሜታችንን፣ ቁጣንና የመሳሳሉት ለመቆጣጠር፤
- ወደ እግዝአብሔር የበለጠ እንድንጠጋና ነፍሳችን የበለጠ እግዚአብሔርን እንድትፈልግና
- በተለያ ችግር ዉስጥ ያሉትን ማለትም በእጦት በሕመም፤ በእርዛት የሚሰቃዩትን እንድናስብ ወይንም እንድናዝንላቸው ያለዉ በጎ ጎኑ እጅግ ታላቅ መሆኑን ዘርዝረዋል፡፡

ደግሞም ስለራሳቸውና ስለቤተሰባቸዉ የፆም ጸሎት ሕይወት ሲናገሩም እንዲህ ብለዋል፡

- "እኔና ባለቤቴ በፆም ስንፀልይ ከጌታ ጋር ያለን መንፈሳዊነትና የእኛም የልብ እንድነት በጣም የተጠናከረ ሲሆን እይቻለሁ።
- ፆም ፀሎት በጀመርኩ ጊዜ ነበር ለብዙ ዓመታት ሰሰቃይ የነበረውን በሽታዬን ጌታ የፈወሰኝ" ብለዋል፡፡

በዚህ እኳያ እኔም እግዚአብሔር በጓዳኛዬ ሕይወት ሳደረገው ድንቅ ሥራ በዓይኔ ያየሁትን ልመስከር፡፡ ስሙ ኤልያስ ይበላል፡፡ ይህ ወንድም በሶሻሊዝም ዘመን አብሮኝ የተሰደደና በመታሰርም ብዙ መከራም እብረን የቀመሰን ወንድም ነበር፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ሁለንተናዉን ለጌታ ጨርሶ የሰጠ ወንድም ነዉ፡፡ በተለይም ለእዉነትና ለቅድሰና በጣም ቀናተኛ ወንድም ነዉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ባለፉት 30 ዓመታት የእገልግሎት ቆይታዉ ብዙ ውጣ ውረዶችንም በሕይወቱ እሳልፎአል፡፡ ከዚህ ከኑሮና ከእገልግሎት ውጣ ውረድ የተነሳ የጫጓራ በሽተኛ ሆነ፡፡ ከዚያም እልፎ ጫጓራው በጣም ከመሳዳቱ የተነሳ ብዙ ጊዜ ሐሞት እስከሚያስታውከው ድረስ ሲያስጨንቀው አይቻለሁ፡፡ ስለዚህ ዉስን የምግብ ዓይነቶችን ብቻ ይመገብ ነበር፡፡ ይህ ወንድም በቅርቡ ከእንድ ፀሎት ቡድን ጋር ለሰባት ቀናት የፆም ጸሎት ምሽግ ገቡ፡፡ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የሦስተኛ የፆም ፀሎት ቀናት የጨጓረውን ሕመም ሊቋቋመዉ የማይችለው ዓይነት ነበር፡፡ ሆኖም የምሞት እንኳ ቢሆን ይህን ፆም ፀሎት እቀጥላለሁ በሚል ዉሳኔ ጸሎቱን ቀጠለ፡፡ ፆም ጸሎታቸዉን በጀመሩ በእራተኛዉ ቀን በሆዱ ውሰጥ በጨጓራዉ ምክንያት ይነድ የነበረዉ እሳት በድንገት ቀጥ አለ፡፡ እስከ ሰባተኛ ቀን ድረስ ጸጥታው ሰፈነ፡፡ በሰባትኛው ቀን ጾማቸዉን ጨርሰው ሲወጡ ድሮ የማይበሳቸውን ምግቦች (እንደ ምስርና ቀይ ወጥ ያሉትን) ሁሉ መብላት ጀመረ፡፡ ጨጓራዉ እንዳችን ችግር እንዳልፈጠረበት አይቶ ተደነቀ፡፡ እስከዛሬም ድረስ ሳለፈዉ ሁለት ዓመታት እንድም ቀን በዚህ በጨጓራ በሽታ ችግር አለመሰቃየቱን ብዙዎች ባለንበት መስክሮልናል፡፡

እንዲሁም ዲን (Dean) የሚባሉ ሰው ሲጽፉ እንዲህ ብለዋል፡- ፆም ፀሎት ሀ/ ትልቅ ደስታና ውስጣዊ ሰላምን ይሰጠናል (ዘካ 8፡18-19) ፣ ለ/ ሽልማት አለዉ (ማቴ፡6፡18) ፣ ሐ/ ለእግዝአብሔር መንፈስ ቅዱስ ድምጽ ንቁ እንድንሆንና ፈጣን ምላሽ እንድንሰጥ ያደርገናል (ሐዋ 13፡1-4) ፣ መ/

ታላቅ ትህትናን በሕይወታችን ያመጣል። ያ ትህትና ደግሞ ፀጋን አንድናገኝ ይረዳናል (1ኛ ጴጥ 5፡5) ብለዋል።

ይህን ሐሳብ ሳጠቃልል ለእግዚአብሔር ከብር፣ ለመንግስቱም መስፋፋት፣ ለሌሎችና ለእኛም ለግል ጉዳይ በጤናማ ተነሳሽነት ግብዝነት የሌለበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፆም ፀሎት ብንጸልይ በሕይወታችን ብቻ ሳይሆን በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን፣ በአገራችን፣ በአህጉርና በዓለም ደረጃ አለገራሚ ሥራዎችን አግዚአብሔር ይሠራል። ጌታ የግል እንቆቅልሾቻችንን ይፈታል፤ የዘመናት ቋጠሮ በመፍታት ይባርካል፤ ሰውነት ከኃጢያትና ከበደል ነፃ ለመሆን እድሉ ሰፊ ይሆንላታል። ብዙ የተደበቀ ከፉ የሆነ የሰዉና የአገር ሚስጥር ይጋለጣል፤ ሥፍራንም ይለቃል። የተኛ ፀጋችን መነቃቃት ይጀምራል። የዲያብሎስ ሥራ በየእቅጣጫ ይፈርሳል። መለኮታዊ ምሪት በተደጋጋሚ ይገለጣል። የአግዚአብሔር መገኘት ግልጽ ይሆናል። ሥጋ ቢደከምም ሥጋዊነትም ደግሞ ይደከማል። መንፈስ ቅዱስ ግን በእኛ ላይና በቤተክርስቲያን ለመሥራት ትልቅ ነፃነት ስለሚያገኝ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ትሆናለች፤ መነቀቃቃትም ዕድል ፋንታዋ ይሆናል።

ስለዚህ ፆም ጸሎት በእካላችን፣ በማህበራዊዉና በመንፈሳዊ ረገድ በጣም ጠቃሚ ሰለሆነ በሩቁ ፈርተን ዳርዳር አየዞርን ላንለማመደዉ ዘመናችንን አንጨርስ። ብዙዎች የማይጸሙት ዋናዉ ምከንያት እኔ ፈጽሞ አልችልም በሚል ለበብ ነዉ። ነገር ግን አንድ ማወቅ ያለብን አዉነት ቢኖር ሁሉም ሰዉ ተፈጥሮዉ እንድ መሆኑን ነዉ። ልዩነቱ በዉሳኔያችን ላይ ብቻ ነዉ። ወስነን ሰንጀምር ጌታ ሊረዳን ሁሌ ዝግጁ ነዉ። ደግሞም በብሉይ ኪዳን ዘመን ማከሰኞና ሐሙስ የፆም ጸሎት ቀናት ሲሆኑ በአዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ ረቡዕና ዓርብ የፆም ጸሎት ቀናት ሆነዉ ስለነበረ ነዉ አርቶዶከስና ካቶሊክ ቤተክርስቲያናት በታማኝነት ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ፆምን በታማኝነት እስከ ዛሬ ሲያካሄዱ የቆዩት። አኛ ፕሮቴስታንቶች ግን በጸጋ ላይ ስለምናተኩር ብዙ ጊዜ ማንኛዉን ዋጋ የሚያስከፍለዉን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድን እንኳ በማወቅም ባለማወቅም ቸል ብለን እናልፋለን፤እናሳልፋለንም። ስለዚህ ፆም ጸሎትን አተኩረን ማየትና መለማመድ እጅግ አስፈላጊያችን መሆኑን አንዘንጋ። ተግባራዊም ለማድረግ ዉሳኔ ዛሬውኑ እናድርግ። የተዉንም ካለን ንስሃ ገብተን እንቀጥል። ያላወቅንም ብንኖር ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈላዊ ተግባር ስለሆነ ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን አንኳ ቢሆን ቋሚ ልምዳችን እንድናደርግ ጌታ ይርዳን።

9. የማለዳ ፀሎት

ኢየሱስ አንዱ የፀሎት ልማዱ ገና ጨለማ ላለ ሳይነጋ ወጥቶ መፀለይ ነበር (ማር 1፡35) ። አንድሪው ሙሬይ የተባሉ ሰው «እኔ ማንንም ከማየቴ አለቀድሞ በማለዳ አግዚአብሔርን መገናኘት ከምንም ነገር በላይ አንደሆነ አምናለሁ» ብለዋል። ባለፈው የአንድ ምዕተ ዓመት ግማሹን የኮሪያ ቤተክርስቲያናት የ365 ቀናትን በየጧቱ ከአሥር ለዓት ጀምሮ ምዕመናን በሙሉ ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት የፀለዩት ፀሎት በአገሪቱ ይህ ነው የማይባል ታላቅ ለውጥን አምጥቷል።

በኢትዮጵያ አውድ ከሌሊቱ 7 ሰዓት ጀምሮ በተለይም ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ በጣም የረቀቀ የከፋት አሠራር የሚሠራበት ሰዓት ነው። ስለዚህ የአመጽ አሠራር ሥራውን ከጨረሰ በኋላ ተነስተን በፀሎት ከመታገል ይልቅ የአመጽ አሠራር አንዳይሠራ አስቀድመን ተነስተን በመጸለይ መከላከል፣ ሥራውንም ማፍረስና ማድከም አጅግ አስፈላጊ ነው። በተለይም የማለዳዉ ሰዓት የሰልከ ጥሪ የማያሰቸግረን፣ ሕፃናት የማይረብሹን፣ የሥራ ሰዓት ደርሷል ብለን አዕምሮአችን የማይታወከበት ጊዜ በመሆኑ ጊዜዉን ትኩረት ሰጥተን መጠቀም ትልቅ ማለተዋል ነው። በመሆኑም በማለዳ ቢያንስ ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ ተነስተን ከጠላት ጋር ፍልሚያ ገጥመን ከላሸነፍን የዕለቱን ሥራ በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ያዳግተናል። የማለዳን ፀሎት አስፈላጊነትና ጥቅም በሚገባ በመረዳት የዲያብሎስን ሥራ በጭካኔ ለማጥፋት የትኛውንም መስዋዕትነት መከፈል አጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ጥሩ ዘዴ በጊዜ መተኛት ነዉ። በሆነና ባልሆነ ነገር ምሽት ላይ ጊዜ ሳናጠፋ በጊዜ ተኝተን በጊዜ ከአንቅልፋችን እንነሳ።

10. ፀጥተኛ የፀሎት ቦታ

በማቴ 17፡1 ላይ ኢየሱስ ለመፀለይ *ወደ ተራራ* ሳይ ከ3ቱ ደቀመዛሙት ጋር ወጣ። በማር 1፡35 ላይ ደግሞ ኢየሱስ ለመፀለይ *ወደ ምድረባዳ* እንደሄደ እንመለከታለን። ቤሐዋ 1፡12-14 ሐዋሪያት ደግሞ *ወደ ሰገነት* ላይ እንደወጡ አናነባለን። እነዚህና ሌሎችም ማስረጃዎች ፀሎት ፀጥ ያለ ቦታና ለዓትን እንደሚፈልግ ጠቋሚዎች ናቸዉ። ለለዚህ ለመፀሰይ ምቹ ቦታ በማዘጋጀት መፀለይ በጣም ውጤታማ የሆነ ፀሎት ለመፀለይና የፀሎት እንቅስቃሴን ለማነሳሳት አንችላለን። አንዴት?

10.1 በየቤታችን የፀሎት ከፍል በማዘጋጀት

እያንዳዱ ሰው ለራሱ የሚፀልይበትን ቦታ ማዘጋጀት ማለትም እያንዳንዱ ሰው የጸሎት ቦታን ለራሱ መለየት አለበት። ለምሳሌ በከተማ የሚኖር ከሆነ በየራሱ መኝታ ከፍል መፀለይ ይችላል። ቢቻል ደግሞ ክቤቱ ከፍሎች እንዱን ክፍል ለፀሎት መለየት ይቻላል። ነገር ግን ገጠር የምንኖር ከሆነ በእንዱ ቤት ውሰጥ ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ ትንሽ ጎጆ ለፀሎት ለይቶ መስራት ይመረጣል።

10.2 በቤተክርሰቲያን ግቢ ውሰጥ የፀሎት ክፍል/ከፍሎችን ማዘጋጀት

በእነዚህ ክፍሎች ምዕመናን እየመጡ ለ24 ሰዓታት እንዲፀልዩ ማበረታታት አለብን። በእነዚህ የፀሎት ከፍሎች በተለይም የሰንሰለት ፀሎት ፕሮግራሞችን ለማካሄድ ይቻላል። የ24 ሰዓት የፀሎት ፕሮግራም በእንድ ክፍል የምናካሄድ ከሆነ ቀሳል የሆነ ዘዴ ቢኖር የቤተክርሰቲያን ምዕመናንን በየወሩ 6 ሰዓት ብቻ እንዲጸልዩ የሰንሰለት ፀሎት ዕድል ቢሰጣቸዉ ከዚህ ቀጥሎ ባለው መልከ እያንዳንዱን ቡድን ማቀናጀት ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ከዘዴዎቹ እንዱ፡-

- ከጧቱ 12-6 ሰዓት
- ከቀኑ 6-12 ሰዓት
- ከምሽቱ 12-6 ሰዓት
- ከሌሊቱ 6-12 ሰዓት በማካፈል እያንዳንዱ ቀን በ4 ቡድኖች መከፋፈል ነዉ።

በእንድ ቡድን ውሰጥ ለምሳሌ 5 ሰው ቢኖር በእንድ ቀን 20 ሰው መፀለይ ይችላል ማለት ነው። ያ ከሆነ በየወሩ በመቶዎችና በሺሆች የሚቆጠሩ ምዕመናን በየቤተክርሰቲያኑ የፀሎት ተካፋዮች ይሆናሉ ማለት ነዉ። ከዚህም የተነሣ፡- ሰውን ሁሉ የሰንሰለት ፀሎት ተሳታፊ ማድረግ ይቻላል። እንዲሁም ደግሞ በእያንዳንዱ ቀን የማይቋረጥ መዓዛ ሽታ ወደ እግዚአብሔር ይቀርባል። ከምሽቱ 12-ሌሊቱ 6 ሰዓት ለሚፀልዩ ቤተክርሰቲያን ፍራሽ ብታዘጋጅ ተጠቃሚ ትሆናለች። በዚህ ጉዳይ ቤተክርሰቲያን ብዙ የገንዘብ ወጪ ይጠይቀናል ብሳ ማሰብ የለባትም። እነዚህ ሁኔታዎች ያለተመቻቹለት ሰው ወደ ተራራ፣ ጫካ፣ ገደላማ ስፍራ፣ እህል ማሳ

... በመሄድ መፀለይ ይችላል። በዚህም ረገድ ጸጥ ያለ ቦታ መርጠ የሚፀልይ ሰው ሁሉ ከአምላኩ ጋር ጤናማና ጣፋጭ ግኙኝነት ማድረግ ስለሚችል ለፀሎት ቦታን መምረጥ ወይም መለየት በጣም ወሳኝ ነው።

፲፩. ጓደኞን መርጠ አብሮ መፀለይ

በማቴ 17፡1-8 ኢየሱስ 3 የፀሎት ጓደኞች ነበሩት። እነርሱም ዮሐንስ፣ ጴጥሮስና ያዕቆብ ነበሩ። በትንቢተ ዳንኤል 2፡17-19 ላይ ስናይ ደግሞ ዳንኤል 3 የፀሎት ጓደኞች (ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ) እንደ ነበሩት እናያለን። የፀሎት ጓደኝነት ታላቅ ውጤት አለው። ኢየሱስ ሲፀልይ ፊቱና ልብሱ ተለውጧል። ዳንኤልና ጓደኞቹ ሲፀልዩ የተቋጠረ እንቆቅልሽ ተፈቷል (ዳን 2፡19)። ከዚህ የምንማረው ዳንኤል የፀሎት ጓደኝነትን የያዘው በቅድስና ጉዳይ ከእርሱ ጋር እንድ አቋም ከነበራቸው ጓደኞቹን ጋር ነበር (ዳንኤል 1፡8)። የፀሎት ጓደኝነት አራት መሠረታዊ ነገሮችን ያካትታል።

- ተመሳሳይ ሸክም ያላቸው ሰዎች፣
- ተመሳሳይ አቋም ያለቸው ሰዎች፣
- የመንፈስና የልብ አንድነት ያላቸው ሰዎች፤
- ተመሳሳይ የፀሎት ትጋት ያላቸው፤
- ሁለት ብቻ የሚሆኑ ከሆነ ተመሳሳይ ዖታ ያላቸዉ። ምከንያቱም ባልና ሚስት ካልሆኑ በቀር ሁሰት ብቻ ከሆኑ ሰይጣን እንዳይፈትናቸዉና ለጥንቃቄና መልካም ምስክርነትን ለመጠበቅ ሲባል ሁለት ተቃራኒ ዖታ ያላቸዉ የፀሎት ጓደኞች ሆነው መፀለይ አይገባቸውም። ከሁለት በላይ ከሆኑ ግን ይችላሉ።

የፀሎት ጓደኞች ፀሎታቸው በጣም ውጤታማ ከመሆኑም በላይ ፈጣን የሆነ የፀሎት ምላሽ ያገኛሉ። በፀሎታቸው ስዓት የእግዚአብሔር መንፈስ በነፃነትና በሙላት ይሰራል።

12. የአዛውንቶች ፀሎት

አዛውንቶችን በፀሎት ተሳታፊ ማድረግ ትልቅ በረከት ነው:: አዛውንቶች ብዙ ለመሥራትና ለመሮጥ ሁኔታው ስለማይፈቅድላቸው ለመፀለይ ያላቸው ዕድል ሰፊ ነው:: ደግሞም እዘወትረው ስለሚፀልዩ ፀሎታቸው በጣም ውጤታማ ይሆናል:: ደግሞም በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉትን እንደየእድሜእቸው በማደራጀት በፀሎት ብናላትፍ በጣም ውጤታማ መሆን እንችላለን ማለት ነዉ::

13. ባለመኑ ለዎች መካከል (Community) የፀሎት ፕሮግራሞችን መጀመር

የአንድ ህብረተሰብ አባላት ወደ ክርስትና እምነት ዘወር እንዲሉ ካሰፈለገ በዚያ ህብረተሰብ መካከል የፀሎት ፕሮግራሞችን በለውር መጀመር ያስፈልጋል:: ያ የፀሎት ዓይነት "Light house prayer" ይባላል:: ይህም እንድ ያመነ ሰዉ ወይንም ቤተሰብ ካለ በእርሱ ቤት ጸሎቱን መጀመር እንችላለን:: ያለጊዜ ለደት እንዳይነሳ እጠቃቀሙ ትልቅ ጥንቃቄ ያሻዋል:: እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት በዚያ በጨለማው ሕብረተሰብ መካከል መለኮታዊ ብርሃን እንዲበራ ምክንያት ይሆንልናል ማለት ነዉ::

14. የተራራ ፀሎት

ሰይጣን ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በዓለም ላይ ያሉ ተራሮችን ሲቆጣጠራቸው እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን:: እግዚአብሔርም ደግሞ ተራሮችን ለራሱ ሲፈልግ እንመለከታለን:: በመሆኑም የእግዚአብሔር ህዝብ (ቤተክርስቲያን) ለተራሮች ትኩረትን በመስጠት የፀሎት ቦታ አድርጎ ለመቀየር የተለየ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል (ባታል)::

- ሙሴ ጥሪ የተቀበለው በተራራ ላይ ነበር (ዘፀ 3)::
- ጌታ ኢየሱስ ፊቱና ልብሱ የተለወጠው በተራራ ላይ እየፀለየ በነበረበት ጊዜ ነበር (ማቴ 17 እና ሉቃ 9)::
- የኮሪያን ቤተክርስቲያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣን እድገት ያላት ቤተክርስቲያን ካደረጓት ነገሮች መካከል እንዱ ለተራራ ፀሎት ትኩረት መስጠቷ ነበር::

ስለሆነም እኛ ለተራራ ጸሎት የተለየ ትኩረት ብንሰጥ እጅግ ታላቅ በረከት ለምድራችን ይሆናል:: ከኢትዮጵያ ተራሮችም አብዛኛዎቹን ብንመለከት፣ ታሪካቸውንም ብናጠና የጠንቋዮች መቀመጫዎች ናቸዉ:: ብዙዎቹ አለከዛፊም እንደዚያዉ ናቸው:: ይህንን እያየን የበቀል ሥራ ጌታ እንዲሠራ ተራሮችን የጸሎት ሥፍራ በማድረግ መልሰን ለእግዚአብሔር ክብር ማዋልና መቀደስ አለብን::

ተራሮች ባሉበት አካባቢ ያሉ አብያተክርስቲያናት ተባብረው ዓመታዊ የፀሎት ፕሮግራሞችን በቅንጅት ማድረግ ይችላሉ:: ለዚህም የፀሎት ፀጋና ሸክም ያላቸውን ወገኖች በመመልመል ኮሚቴ በማድረግ በየአካባቢው እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ማድረግ ይችላሉ:: ሌላው በተራሮች ላይ ለመፀለይ የሚያለችሉ መለስተኛ የፀሎት ቤቶችን መሥራት ብዙዎች በተለያየ ጊዜ ወደ ተራራው በመሄድ የፀጥታ የፀሎት ጊዜ እንዲያላልፉ ይረዳቸዋል:: ይህም ደግሞ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በረከት እንደሆነ ልብ ይሏል:: ከእገራቸዉ ውጪ እንኳ የሚኖሩ ኮሪያዉያን በሄዱበቸዉ አገሮች ተራሮች ላይ ትንንሽ ቤቶች ሠርተዉ የጸሎት ሥፍራ እያደረጉ እንዳለ እኔው ራሴ ለዚህ ምስክር ነኝ:: ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያዉያን ደግሞ ብዙ ተራሮች ባሉበት እገር ስለምንኖር በእካባቢያችን ያሉትን ተራሮች የጸሎት ተራሮች ማድረግ እለብን:: በኢትዮጵያ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ዱራሜ በምትባል ከተማ ጥግ ያለውና በደቡብ ክልል ትልቁ (ረዥሙ) ተራራ በሚባለው *በአምባሮ ተራራ* ላይ እየተካሄደ ያለዉን ተሞክሮ ለእብነት መውሰድ እንችላለን:: ከዚያ ልምድ ተነስተን እኛም በየእካባቢያችን ባሉ ተራሮች ላይ የጸሎት ንቅናቄ መጀመር እንችላለን:: በዚህ በእምባሮች ተራራ ላይ የተጀመረዉ የጸሎት እንቅስቃሴ ራሱን የቻለ የንቅናቄ ተሞክሮ በሚል ሥር በስፋት ስለተቀመጠ ያንብቡትና እርስዎም ተሞክሮዉን በእካባቢዎ ከሌሎች ጋር ይጀምሩ::

15. የተለየ የፀሎት ወቅት በመውሰድ መፀለይ

የምንኖርበት ዓለም መከራ የተሞለበት ዓለም ነው:: ኑሮአችንም በጣም የተወላለበ ነው:: ለይጣንም ያልተጠበቁ ታላላቅ ተግዳሮቶችን በሕይወታችንና በቤታችን ድንገት ብቅ እያደረገ ያጨናንቀናል:: በመሆኑም የተለያዩ ከስተቶች ሲፈጠሩም ይሁን በቋሚነት በእግዚአብሔር ፊት የተለየ የፀሎት ጊዜ በመውሰድ መፀለይ የመንፈሳዊ ሕይወታችንን፣ የእገልግሎታችንንና የትዳር ኑሮአችንን ሚዛን (Balance)

ከመጠበቁም በላይ ታላላቅና ድንቃድንቅ ድሎችን በጠላት ላይ ለመቀዳጀት ያለችለናል። ከላይ በሳምንት የሁለት ቀን የፆም ፀሎት የብሉይና የአዲሰ ከዳን አንዲሁም የቤተክርስቲያን ታሪከም ልማድ ነበር ብያለሁ። ነገር ግን በአሁን ዘመን የካቶሊክ፣ የኦርቶዶከስ፣ የሙስሊምና ሌሎችም ለያዙት የፆም ልምምድ ጠንካሮች ሲሆኑ የፕሮቴስታንት አምነት ተከታዮች በዚህ ልምምዳቸውና አቋማቸው በጣም ደካማ ናቸው የሚለዉንም ህሳብ ጠቅሻለሁ። ማጋነንም አይሆንም። የሥጋን ድካም ሰበብ በማድረግና ጸጋዉ ይበቃል በማለት ብዙ የተለያዩ ምከንያቶችን (excuses) አናበዛለን። ሌላው ደግሞ ብዙ አብያተክርስቲያናት የራሳቸው የሆነ የፕሮግራም ይዘት፤ አቋምና አመለካከት ለላለቸው ብዙ ባላውቅም በአብዛኛዎቹ አብያተክርስቲያናት ፆም ፀሎት አየታወጀ በቋምነት የሚደረጉ የፀሎት ፕሮግራሞች በአጅጉ የተዳከሙ ናቸው። ሆኖም አሸናፊ ጌታ ኢየሱለ አንጂ ሥጋ፣ ሁኔታና ሳይጣን አይደሉምና የሸንፈት አዋጅ በራሳችን ላይ እያወጅን በፀሎት ልፍስፍለ በመሆን የሰይጣን መሣቂያ መሆን የለብንም። ስለሆነም በዚህ ረገድ ትምህርት፤ ውይይት፤ ውሳኔና አቋም ያስፈልገናል። የተለየ የፀሎት ወቅትን በሚመለከት የሚከተሉ ልምምዶችን ለመጠቆም አወዳለሁ። ነገር ግን ፀልየን የተሻለውን መውሰድ የራሳችን ምርጫና ውሳኔ ነው።

15.1 በየወሩ ቢቻል የ3 ቀናት ተከታታይ የፆም ፀሎት ቀናትን ማካሄድ

ይህ በአንዳንዶች ዘንድ የአለቴር ፀሎት በመባል የሚታወቅ ሲሆን በተለይም በአሁኑ ዘመን አይኑን አፍጦ የመጣውንና የዘመናዊነትንና የኃጢአትን አንዲሁም ብዙ ቅጥ ያጡ (Abnormal) ተግዳሮቶችን ለመቋቋም የምንችለው ትልቅ ዋጋ በሚያለከፍል (abnormal) ፀሎት ነው። ኢየሱስ ሞቶ ነው ዓለምን ሁሉ ያዳነው። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት አሥራ አንዱ በለማዕትነት ሞተው ነው ዓለም ላይ ዛሬ ከ700,000,000 (ከሰባት መቶ ሚልየን) በላይ አማኝ ሊገኝ የቻለው። የዛሬንና የነገን ትውልድ ለመታደግ ሥጋን ለማዕት ለማድረግ የተዘጋጀ ትውልድ ያስፈልገናል። አለበለዚያ ግን ትልቅ አደጋ ተጋርጦብናል። ዋጋ በሚያለከፍል ፀሎት ይህን የአመጽ ጎርፍ ካለቆምን ወይንም ከልተቋቋምን ዓይናችን እያየ ይህ የጥፋት ጎርፍ ብዙዎችን ጠርጎ ይወለዳል። እኛንም አይምረንም። ጌታ በነገር ሁሉ ማለተዋልን ይስጠን። ለምሳሌ አውሮፓ በተለይ አንግሊዝ የዛሬ 100 ዓመታት ከ90% በላይ ማለት ይቻላል ሕዝቧ አማኝ ነበር። ነገር ግን መንፈሳዊነትና ፀሎት በመሞቱ ዛሬ አማኝ

የሆነዉ ህዝብ ወደ ከ10% በታች ሆኗል። የዛሬ 500 ዓመት የፕሮቴስታንት አምነት የጀመረበት የአዉሮፓ ከፍለዓለም ከርስትና ዛሬ ከዓለም ከርስትና ጋር ሊነፃፀር በጌታ ያመኑትን ክርስቲያኖችን የሚወከለዉ 3.3 ፐርሰንቱን ብቻ ነዉ።

15.2 ድንገተኛ የጸሎት ጥሪ

ብዙ ጊዜ ድንገት ለሚከሰቱ ከስተቶችና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለምንጸልየው ጸሎት ለሶስት ቀናት (ልከ አንደ አስቴር) ፣ ለላምንት፣ ለሁለት ሳምንት፣ ለሦለት ሳምንታት (ለ21 ቀናት) ልከ አንደ አንደ ዳንኤል፣ ለ40 ቀናት ልከ አንደ ኢየሱስ፣ ሙሴና ኤልያስ የምናደርጋቸዉ ጸሎቶች በአርግጥ የተአምራትን ኑሮን አንድንኖር ያደርጉናል። ከአግዚአብሔር ትከክለኛ ምሪት መቀበል የሚፈልጉ ሰዎችና ግለሰቦች ይህንን ፀሎት ሲያጠነክሩ አናያለን። ምከንያቱም ለግል ሕይወትና አገልግሎት ለመሥሪያ ቤትና ለቤተሰብ፣ ለቤተክርስቲያን አንዲሁም ለአገር ከአግዚአብሔር ዘንድ ትከክለኛ ራዕይ አንዲኖረንና መፍተሄ ሲያስፈልገን በዓመት አንድ ጊዜም ቢሆን ጸሎት ማድረግ ትልቅ በረከት ነው።

15.3 የህማማትን ላምንት

ይህ በአንዳንድ ቅዱሳንና አብያተክርስቲያናት ዘንድ አየተለመደ ለለመጣ ጌታ ይመስገን። ነገር ግን ልምምዱን በየአብያተ ከርስቲያናቱ ማጠናከር አለብን። በዚያ ሳምንት ያንን ማድረግ ብዙ ጌታን የማያውቁ ሰዎች ወደ ጌታ ልባቸውን አንዲያዘነብሉ ፀሎታችን ትልቅ ሚና ይኖረዋል ነው። ጊዜው ጌታ የተሰቃየበት ላምንት በመሆኑ ለለኛ ትልቅ ትርጉም አለዉ።

15.4 የጳጉሜ ወር ፀሎት

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አግዚአብሔር በመለኮታዊ ጥበቡ ብዙ ግለሰቦች፣ ሕብረቶችና ቤተክርስቲያናት የጳጉሜን ወር በፆም ፀሎት በማሳሰፍ ላይ ይገኛሉ። ከዚያም የተነሣ ብዙ መልካምና በጎ የሆኑ ተጽእኖዎች ፕሮግራሙን በሚያካሄዱ ወገኖችና አብያተክርስቲያናት ላይ አየተፈጠሩ ይገኛል። ስለዚህ የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናት ይህን የጸሎት ልምምድ በየዓመቱ ቢያደርጉ በአገር አቀፍ ደረጃ በጎ ተጽዕኖ መፍጠር ይቻላል አለሁ።

16. የስልክ ፀሎት

አግዚአብሔር የሰጠን ቴክኖሎጂን ወይንም የትኛውንም በረከት ስለግዚአብሔር ከብር ለመጠቀም አንችላለን:: እግዚአብሔር ደግሞ ደሰ ይሰኝበታል እንጂ ሀዘንተኛ አይሆንም:: ሰልክ ትልቅ አገልግሎትን ከሚሰጡ የዘመኑ ቴክኖሎጂዎች አንዱ ነው:: አንዱም እገልግሎቱ በእካል ልንደርስላቸው ለማንችላቸዉ ሰዎች ለመፀለይና በእነርሱም ለራሳችን ለማሰፀለይ እንችላለን:: በእግርም በመኪናም ሄደን ወይንም መጥተው ለማናገኛቸው ወገኖች የሰልክ እገልግሎት ልንሰጥና ከእነርሱም ልንቀበል እንችላለን:: ነገር ግን ሰይጣን የአግዚአብሔርን በጎ ሀሳብ ለመቀልበስ መጣር ልማዱ ሰለሆነ በሰልክ ላይ እንፀልያለን የሚሉ ብዙ አገልጋዮች በትንቢትና የመገለጥ መልዕክት እያሰተላለፍን ነው በሚል ስበብ ዋና ትኩረታቸው ብርን መሰብሰብ እየሆነ መጥቷል:: ይህን ማለቴ በሰልክ የትንቢት መልዕክት መተላለፍ የለበትም አያልሁ አይደለም:: ነገር ግን የብዙዎች ዉሰጣዊ ተነሳሽነታቸዉ (Motive) ጤናማ ስላልሆነ ጥንንቃቄ መደረግ አለበት እያልኩ ነው አንጂ:: በስልክ ጧትና ማታ ልፀልይልህ፣ ልፀልይልሽ እያሉ የሚያጣድፉትንና በየሴክንዱ ትንቢት የሚናገሩልንን በልዩ ጥንቃቄና ፍተሻ ብናዳምጣቸው ጥሩ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትን አትናቁ ግን ሁሉን ፈትኑ ስለሚል መልዕክቶችን በሙሉ እንደወረደ መቀበል የለብንም:: ነገር ግን በውስጣችን ያለዉ መንፈስና የአግዚአብሔር መንፈስ የሚያረጋግጥልንን መልዕክት በመጽሐፍ ቅዱስንና የበሰሉ እገልጋዮችን በማመከር መቀበል ተገቢ ነው:: ስለዚህ በስልክ ላይ ለተቸገሩ፣ ለታመሙና ለተጨነቁ ሰዎች መፀለይ ትልቅ በረከት መሆኑ አይጠያይቅም:: ዋናው ነገር ስልክ ወይንም ቀጥታ ፊት ለፊት ሆነን መፀለይ ሳይሆን በየትኛዉም ሁኔታና ስፍራ ሆነን የምንፀልየዉ ፀሎትና አግዚአብሔር ለፀሎቱ የሚመልሰዉ ምላሽ ነው::

ለምሳሌ ያህል አኔ ሁሊጊዜ የማደርገዉ ነገር ቢኖር ልጆቼ ዩንቨርሲቲ ሲማሩ በነበሩበት ወቅት (እሁን የጨረሱና እሁን ደግሞ በመማር ላይ ያሉ) ሁሌም ሁኔታዎች ሲከብዱባቸዉ አኔንና ባለቤቴን አንድንጸልይላቸዉ ይጠይቁናል:: እኔም ሞባይላቸዉን በጆሮአቸዉ ላይ እንዲያደርጉ ነግሬአቸዉ በኔ ሞባይል ሆኜ አጸልይላቸዋለሁ:: በቀኑ ወይንም በሁተኛዉ ቀን ክዚያ ጸሎት በኋላ የክበበኝ ጭንቀት ወይንም ሕመም ለቀቀኝ እኮ ብለዉ ሲመስክሩልኝ ሁሌም እስማለሁ:: ደግሞም በጥቅምት ወር ማለቂያ 2006 ዓ.ም ላይ ሚስዮናዊ ተመሰገን የሚባል

ሚስናዊ ሆኖ ወደ ባርማ ማለትም የዛሬዋ ማይናማር ሄደ:: መሄዱ ብቻ ሳይሆን ዓለም ገድ የሚያሰኝ አገልግሎትን አገለገለ:: ከዚያን ጊዜም ጀምሮ እጅግ ብዙ የሚሸን ድርጅቶች መቋቋም ጀመሩ:: ብዙ ወጣቶች ለወንጌል ተልዕኮ ተንቀሳቀሱ:: አዶኒራም ጃድሰን የፀሎት ሰው በመሆኑ ሚስዮናዊ ሆኖ በሄደበት አገር <u>በየቀኑ ሰባት ጊዜ ይፀልይ ነበር ይባላል</u>:: በሄደበት አለም ታላቅ አገልግሎት ሰጥቶ በአገሩም ላይ ታላቅ ተጽዕኖ አሳድሮ አልፎአል::

ጸሎቱን ክጸለዩ ከ48 ዓመት በኋላ ማለትም እ.ኤ.አ በ1854 በጸሎቱ ተሳታፊ የነበረዉ ቢሪያም ግሪን ትክክለኛውን የ1806 የሐይእስታክ የጸሎት አንቅስቅሲያቸው የነበረውን ሥፍራ ቁጥራቸው በርክት ላሉ ለሚፀልዩ ሴቶች ነገራቸው:: አነዚያም ሴቶች ከመሬቱ ባለቤት ያቺን ቦታ አንድ ዶላር በሚያወጣ ወርቅ ገዙ:: ያንንም ከገዙ በኋላ የአሜሪካን የሚስዮን ንቅናቄ በ1806 አዚህ ቦታ ተወለደ የሚል ጽሑፍ የያዘ ሐውልት ተተክሎ ዛሬም ሐዉልቱ እንደቆመ ይታያል:: ባለፈው አኤአ በ2006 ዓ.ም ላይ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰዎች ሐውልቱ ባለበት ተገኝተው አጅ ለእጅ ተያይዘው የአሜሪካን የሚስዮን ንቅናቄ በጸሎት የተጀመረበትን ሁለት መቶኛ ዓመት እከብረዋል::

የዚህ ታሪክ ጸሐፊም ሲናገር «የ1806 የገለባው ክምር ሥር የፀሎት ንቅናቄ የዓለም አቀፍን የወንጌል ተልዕኮ አንቅስቃሴ የወለደ በኩር ንቅናቄ ነበር» ብሏል :: አዎን አነዚህ ወጣቶች ተራ ወጣቶች ነበሩ:: ነገር ግን የአግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰማ ጆሮ ነበራቸው:: ለአግዚአብሔር መንፈስ ታዛዦች ሆኑ:: አግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎችን የሚሰራው ታናናሽ በሚባሉ ሰዎችና ራሳቸውን ዝቅ በሚያደርጉ ሰዎች ነው:: እንደዚህ ያሉትን ሰዎች በአርግጥ ጌታ ለክብሩ ይጠቀምባቸዋል!

3. በ1858-1859 ዓ.ም በአሜሪካን አገር የተከሰተው ታላቁ የፀሎት ንቅናቄ

ይህ አግዚአብሔር ለወቅቱ አስቦ ያመጣው ያልተጠበቀ የአግዚአብሔር አጅንዳ አንደነበረ ይነገራል:: ጊዜው አ.ኤ.አ ጁላይ ፣ ቀን 1957 ላይ ጃርማያህ (ኤርሚያስ) ላንስፊር የሚባል በንግድ ይተዳደር የነበረ ሰው ለኒውዮርክ ከተማ የከተማው ሚስዮናዊ እንዲሆን ተመረጠ:: ይህ ሰው በ1809 ተወልዶ በ1842 ዓ.ም ሮድዌይ በምትባል ቤተክርስቲያን ጌታን ተቀበለ:: ይህ ቤተክርስቲያን ከአሥር ዓመት በፊት ቻርለስ ፊኒ በሚባል ታላቅ ሰባኪ የተሠራ ሲሆን በቻርለስ ፊኒ ዘመን ታላቅ መነቃቃት

በአሜሪካ ተከሰቶ የነበረ ቢሆንም በዚህ ወቅት መንፈሳዊ ብርድ በአገሪቱ ጀምሮ ነበር ይባላል።

በዚያን ወቅት በኒውዮርክ ከተማ መኻከል ወይንም ፒያሳ በድህነት የተጉሳቆሉ ብዙ ሰዎች ይኖሩ ነበር። ሀብታሞች ግን ወደ ገጠሩ ወጣ ብለው ቤት ሠርተው አዚያው በገጠር አከባቢ ባሉ ቤተክርስቲያናት ይካፈሉ ነበር። ነገር ግን በከተማው መኻከል ያለውን ድሃ በፀሎትም ሆነ በሌላው ድጋፍ የሚያሰብ አልነበረም። በከተማው መኻከል ለሚኖሩ አጅግ የተጎሳቆሉ ሰዎችን ለማገልገል በጊዜዉ ጃርማያ ትልቅ ሽከም ተሰማው። ከዚህም ሽከም የተነሣ በየዕሮቡ ዕለት ልክ 6 ሰዓት ላይ ከርሱ ጋር አብረውት የሚፀልዩ ለዎችን ፍለጋ ማሰታወቂያ መለጠፍ ጀመረ።

ታሪኩን ዘጋቢ እንዲህ ሲል ያሰቀምጣል፡- አ.አ ሴፕተምበር 23 ቀን 1857 ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ጃርማያ ለፀሎት ሰዎችን ጋበዘ። በግብጥው መሠረት ቤተክርስቲያን ከፍቶ ቢጠብቅም 6፡30 አሰኪሆን ድረስ ለፀሎቱ ብቅ ያለ ማንም አልነበረም። ነገር ግን ልክ 6፡30 ላይ የአንድ ሰው ኮቴ በደረጃዉ ላይ ተሰማ። ማን ነዉ ብሎ ጃርማያ ሲመለከት ስለፀሎት የወጣውን ማሰተወቂያ ያነበበ ሰው ነበር የመጣዉ። ጃርማያ ደሰ አለዉ። ቀስ በቀሰ የተሳታፊዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ። በዚያ ዕለት 6 ሰዎች ከኤርሚያስ ጋር አብረው ፀልዩ። ከዚያን ቀን በኋላ በየዕሮቡ የሚሰበሰቡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ። የጥቅምት ወር ሲገባ በሳምንት አንድ ጊዜ ይደረግ የነበረው የፀሎት ፕሮግራም ተሳታፊዎቹ የፀሎት ፕሮግራሙ በየቀኑ በምሳ ሰዓት እንዲሆን ተሰማሙ። የፀሎት ፕሮግራሙ በተጀመረ በ6 ወሩ በከተማው መካከል ሱቅ ያላቸው ነጋዴዎች አብዛኛዎቹ በምሳ ሰዓት ለፀሎት መሰብሰብ ጀመሩ። በየቀኑ 10,000 የሚሆኑ ሰዎች የጸሎት ፕሮገራሙ ተሳታፊዎች ሆኑ። ያም ብቻ ላይሆን ፀሎቱ በተጀመረ በሁለት ዓመት ውስጥ በዚያን አካባቢ ከ10,000 ሰው በላይ ጌታን በመቀበል ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ተጨመሩ። በኒውዮርክ የተቀጣጠለው የፀሎት አሳት የአሜሪካንን አጠቃላይ ግዛቶች ያካለለ ሆነ።

ከዚህ ጸሎት የተነሳ በሰሜናዊዉና በደቡባዊዉ የአሜሪካ ግዛቶች መካከል በባሪያ ንግድ ምክንያት ብዙ ደም ያቃባው ጦርነት ቀዝቀዘ በሰዎች መካካል አርቀ ሰላም በየአቅጣጫ መዉረድ ጀመረ። ልክ የኒውዮርክን ሪቫይቫል ተከትሎ ትላልቅ በሚባሉ በአሜሪካ ከተሞች በሙሉ

መነቃቃት ጀመሩ። ከዚያ ቀጥሎ ትናንሽ ከተሞችንና በገጠር ባሉ መንደሮች ሁሉ ሳይቀር የፀሎት ንቅናቄና የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት በየቦታዉ ተቀጣጠለ። መነቃቃቱ ያልነካቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች በየቀኑ የሚያወሩት ይደረግ ሰለነበረዉ ጸሎት ብቻ ሆነ። ለዉ ሁሉ በጸሎት ፍቅር በመነደፉ ቤተክርስቲያናት፣ የቲያትር ቤቶችና አሉ የሚባሉ አደራሾች በሙሉ ፀሎት የሚካሄድባቸዉ ቦታዎች ሆኑ። ሲ.ፕ. ሚሰልቫይን የሚባሉ ፀሓፊ ጠቅለል አድርገው ለለዚህ የጸሎት እንቅሰቃሴ ሲጽፉ እንደሚከተለው አሰቀምጠዋል። "በየዕለቱ ይደረግ የነበረው ፕሮግራም ቀላል አልነበረም። መፀለይ፣ ቃሉን ማንበብ፣ መዘመር፣ በተረጋጋ መንፈስ ሆኖ በአግዚአብሔር መንፈስ መቃተት በየሰፍራው የዘወትር ተግባር ሆነ። አብረው የሚፀልዩ ሰዎች መካከል የነበረው ፍቅርና ደስታ ጉባኤውን መንግሰተ ሰማይ ማሰመሰሉና ሁሉም አንዱ በሌላው ላይ በጎ ተጽኖ ፈጣሪ መሆኑ ይገርም ነበር። ሕዝቡ በጸሎት መቀጣጠሉ በአንድ ቦታ ፣ በአንድ የዕድሜ ከልልና በአንድ የህብረተሰብ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ሁሉንም ለውያማከለ ነበር። በሰዎች ሁሉ ላይ የሕይወትና የማህበራዊ ለውጥ በግልጽ ይታይ ነበር" ብለዋል።

በወቅቱ የነበረዉ ሁኔታ እጅግ አሰከፊ ሰለነበር ከ5-6 ሰዓት የሚያህለውን ጊዜ በየቀኑ የምናሰልፈው በፀሎት ነበር። በወቅቱ ሰለ ፀሎት የተጻፉ መጻሕፍት ብዙ አልነበሩም። ነገር ግን ያገኘነዉን ሁሉ ከየአቅጣጫዉ አያደንን ማንበብና ያነበብነዉን ለመተግበር መጣርንም ዋና ሥራችን አደረግን። መጽሐፍ ቅዱሰን የአያንዳንዱን መጽሐፍ ምዕራፍ በምዕራፍ ለይተን እሰከምናውቅ ድረሰ በላነው። ደግሞም እግዚአብሔር ከፈታችን ያለቀመጣቸው የአኛ ምሳሌዎቻችን የነበሩትን አንደነ ተሰፋዬ ጋቢሶ (በሶሻሊዝም ዘመን ለ8 ዓመታት በአሰር ቤት ከሌሎቹም ጋር ታሰረዉ የወጡና በአሁን ሠዓት በአዋሰ ሙሉወንጌል ቤ/ክ መጋቢ ሆነው የሚያገለግሉ)፣ በአሁን ሠዓት ወደ ጌታ የሄዱና በኔ በኩል እሰከዛሬ ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው ታላቅ የእግዚአብሔር ቃል ለባኪ ናቸው የምላቸው ወ/ዊ ሰምያን ዳና፣ አንዲሁም በአሁን ሠዓት በወላይታ ሶዶ ስታዲያም ቃ/ሕ/ቤ/ክ ቤተክርስቲያን መጋቢ ሆነው የሚያገለግሉ መጋቢ ዮሐንስ ባለናና ሌሎችም ለወጣቶች ያሰተምሩን የነበረውን የእግዚአብሔርን ቃልና የሕይወት ምሳሌነታቸውን ጥቂቶቻችን ትምህርቶቻቸዉንና መንፈሳዊ ሕይወታቸዉን በታላቅ ጥንቃቄና ትኩረት እንከታተል ነበር። በግል ካለን ትጋትና ከእነዚህ ሞዴሎቻችን መንፈሳዊ አሰተዋዕጽዎ የተነሳ ሙሉ ሕይወታችን በመንፈሰ ቅዱሰ አሰት ይነድ ነበር። ከዚህም የተነሳ በቂ እንቅልፍ አግኝተን አርፈን ተኝተን ያደርን ዕለት ታጢአት የሠራን ያህል ይፀፅተን ነበር። በተለይም አዳር ፀሎቶችን ማዘወተርና በሌሎችም ቀናት ከእኩለ ሌሊት ሠዓት ጀምሮ አሰኪነጋ መጸለይ በጣም የተለመደ ተግባራችን ሆነ። በተለይም ከ1960ዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ አዋሰ ሕይወት ብርሃን ቤ/ክ ይደረግ የነበረውንና ሌሎች ኮንፍራንሶችን እኔና ጥቂት ጓደኞቼ መከታተላችን የሕይወታችንን አቅጣጫ የቀየረና የፀሎት ሕይወታችንን ይበልጥ የለወጠ ነበር። አነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ለዚያ ወቅት ያዘጋጀልን በተለይ ለኔ ትልቅ በረከቶች ነበሩ ማለት እችላለሁ።

በተሰይም በዚህን ወቅት ማለትም ከ1970-1971 ዓ.ም በፀሎት ህይወቴ ትልቅ ተፅዕኖ የፈጠረች አየለች ወዳጆ የምትባል እህት ማለትም የአቶ ተሰማ ሎዴቦ (የደቡብ አብያተ ክርስቲያናት ዋና ፀሃፊ የነበሩ) ባለቤት ናት። አርሷ በይርጋለምና ዲላ በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ የተነሳዉን ሪቫይቫል ቀምሳ የመጣችና ህይወቷን ለጌታ ጨርሳ የለጠች እህት ነበረች። የህይወትዋ መለወጥ፣ የጸሎት ትጋትዋ በጣም ያስቀናኝ ስለነበር እንደ አየለች አትጋኝ ሸያልኩ አጸልይ ነበር።

ደግሞም ጌታ በጣም አድርጎ የተጠቀመዉ የሚሸግዳ ከፍለ ማህበር ኳይር የሚባል ነበር። ይህንን ኳየር ያስጀመሩት ደግሞ የዛሬዉ የወንጌላዉያን አብያተክርስቲናት ዋና ጸሓፊ የሆኑ ቄለ ዓስሙ ሼጣ ነበሩ። አርሳቸዉ፣ አብርሃም ገበየሁ፣ በቀለ አባይና ሌሎችም ከኤለ አይ ኤም አስኮላርሽፕ ተለጥቷቸዉ ከዲላ በመምጣት እካዳሚክ ት/ት ይማሩ ነበር። እንዲሁም ተረፈ በዳዳ የሚባል ከወሊሶ፣ ይስሃቅ አልዳዳና ራሔል ባፋ ከዋካ በመምጣት በዱራሜ አስከ አሥረኛ ከፍል ባለዉ ኤ አይ ኤም ት/ቤት ተማሪ ሆነዉ ይማሩ ነበር። በወቅቱ ወጣት ዓለሙ ሼጣ በጣም ትጉና ታታሪ ወጣት ነበሩ። በተለይም ትልቅ የመረነት ጸጋ የነበራቸዉ ነበሩና እነዚህን የአስኮላርሽፕ ተማሪዎችን በማነሳሳትና በማስባስብ ለመጀመሪያ ጊዜ በከምባታና ሐዲያ ምድር ኳየር በመመሥረት የኳየርን ምንነት ያስተዋወቁት እሳቸዉና የአስኮላርሽፕ ተማሪዎች ነበሩ። እርሳቸዉም ዛሬ ይህን ትልቅ የአመራር ቦታ ይዘዉ ቢመሩ ብዙ አልደነቅም። ምከንያቱም ገና ያኔ ታላቅ የመሪነት ጸጋ ይታይባቸዉ እንደነበር አዉቃለሁና።

እኔም የኳየር ምንነትን በሚገባ ሳላዉቅ መዝሙር ስለምወድ ብቻ ገባሁና ማገልገል ጀመርኩ። ታዲያ ቆይቶ የኳየሩ ቦታ ጵጌል ሆነልኝ። በዚያ ኳየር ገብቼ ማገልገል የጀመርኩት የስደቱ ወላፈን የነበረበት ጊዜ ነበርና በዚያን ወቅት አብረዉኝ በኳየሩ ዉስጥ ሆነዉ ይተጉና ያተጉኝ የነበሩ ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡-ተከተል ማርቆስ፣ ከበቡሽ አጤቦ፣ ታደሰ ዮሐንስ፣ ተረፈ ደንታሞ፣ ኤልያስ ሓንዲስ፣ አበበች ሚቆሬ፣ አረጋሽ ባፋ፣ ሙሉ ያዕቆብ፣ በቀለች ግርማሞ፣ ተስፋነሽ ዮሐንስ፣ ደግሞም ባለቤቴ ወ/ሮ ዘነበች ኡሼና ሌሎችም ዉድ የሆኑ ወንድሞችና እህቶች ነበሩ። በዚያ ኳየር ከተዋወቅንበት ሰዓት አንለቶ ዕድሜዉን ሁሉ የጸሎት አጋሬ ሆኖ የጸለየልኝንና በጸሎቱ የተሸከመኝን በሪሶ ሎዴቦን አግዚአብሔር አብዝቶ ይባርከዉ እላለሁ። ከኳየራችን ዉጪ ደግሞ የጸሎት ወገቤንና ጉልበቴን ያጸኑ ሁልጊዜ የማልረሳቸዉ ወ/ሮ ብዙነሽ ሐደሮ፣ ዘነበች

ማርቆስና ደስታ ዋኖሬ ናቸዉ። ስለዚህ የአኔ ጸሎት ጉዞ በአጠቃላይ በብዙዎች መንፈሳዊ ባላ የተደገፈ ነበር ማለት ይቻላል። ሰዉ ነኝና ስለ አነዚህ አጅግ ዉድ ስለሆኑ ቅዱሳን ጌታን ሰማመስገን ፈጽሞ ቃላት ያጥሩኛል። ከዚህ የተነሳ ያንን የመከራ ዘመን አግዚአብሔር በድልና በድንቅ ታምራት አሻገረኝ። በአነዚያ የስደት ጊዚያት በሕይወታችን፣ በቤተክርስቲያናትና በአካባቢያችን በሚጸልዩ ወገኖች ሕይወትና አገልግሎት እግዚአብሔር አስገራሚ ተአምራቶችን ያደርግ ነበር።

ከርስቲያኖችን ያሳድዱና በአሳዳጆችም ይሰደዱ በነበሩ ከርስቲኖች መካከል ጌታ ያደረገዉን በጥቂቱ ቀንጨብ አድርጌ ላቅርብ።

ሾኔ በምትባል ከተማ የታሰሩ ከርስቲያን አስረኞን ስመረሽን ይመጣ የነበረ ባለሥልጣን ከመኪና ተገልብጦ ከወገቡ በታች ሽባ ሆኗል። ሌላ አንድ ባለሥልጣን በዚያው መኪና አደጋ ሕይወቱ አልፋለች። አብረዉ የነበሩ ወርቁ አሼቦና አየለች አሼቦ የሚባሉ ሁለት ከርስቲያን አህቶች አካላቸዉን ጭረት እንኳ ሳይነካ በሰላም ከመኪናዉ ወጡ።

ከርስቲያን አስረኞቹ ግን የነበሩበት ቤት ከአየር እጦት የተነሳ ታፍነው አጅግ ተጨንቀው በነበሩበት ስዓት ወደ አግዚአብሔር ሲጮሁ ድንገተኛ አውሎ ንፋስ መጥቶ የእስር ቤቱን ከዳን ነቅሎ በመውሰድ በረዥም ርቀት ወስዶ በመጣሉ በቂ አየር እግኝተዉ በመተንፈስ እፎይ አሉ። አንዲሁም እነዚህን ከርስቲያኖች በግፍ ያሳሰረ ካድሬ በአብደት መንፈስ ተመቶ በኋላ ሞተ።

በሌላዉ ከተማ አንዲትን እህት ለመደብደብና ለማስነወር የመጡ ወንድ ወጣቶች እርሷ ጋ ደርሰው አርስ በርሳቸው ቋንቋቸው ተደባላልቆ ተደባድበው ደም በደም ሆነው ምንም ሳያደርጓት ወደመጡበት አየተደባደቡና አየተጣሉ ተመለሱ።

አኔና ጓደኛዬ በፀሎት ውለን በታይለኛ ጭቃ ላይ ስንሄድ ሁለታችንም ተንሸራትተን ወድቀን በተደጋጋሚ ተንከባለናል። ነገር ግን አካላችን ሊጎዳ ቀርቶ ልብሳችንን ስናወልቅ እንድ የጭቃ ምልከት ስንኳ በልብሳችን ላይ ሳናገን መቅረታችን አንድ ያስደነቀን ትንግርት ነበር።

አንድ ቀን የእንድ ቤተከርስቲያን ኳየርን እየደበደቡ አስር ቤት ለመውሰድ የቀበሌ ወጣቶች በመጡ ጊዜ ከየት መጣ ሳይባል ነጭድጓድና ከፍተኛ የሆነ እውሎ ንፋስ አሳዳጆችን ሁላቸውንም በሚዳ ይዞ በታተናቸውና

ዝናብ ጠግበው ወደ መጡበት ሲመለሱ ኳየሩ ግን በለሊም ፕሮግራሙን ጨርሰ ወደቤት ተመለሰ።

ይህ ሁሉ ምንድር ነው ቢባል የሥራው ባለቤት ዋናው አግዚአብሔር ሲሆን ከርስቲያኖች ጸሎትን ልከ እንደ ሕይወት አስትንፋሳቸው አድርገው ይለማመዱ ስለነበርና አግዚአብሔር ለለሙ የሚቀናና የሕዝቡ አረኛ ስለሆነ የእርሱ መለኮታዊ ጣልቃ ገቢነት እጅግ ግልጽ ሆኖ ይታይ ነበረ።

እኔና ሁለቱ የቅርብ የጸሎት ጓደኞቼ ታደሰ ዮሐንስና ኤልያስ ሐንዲሶ በዝግጅት የጠበቅነዉ አስራት አልቀረምና መጣ። ለካስ አግዚአብሔር እስቀድሞ ያዘጋጀን የነበረዉ ለመከራው ጊዜ ነበርና በቅድሚያ የተፀለየው ጸሎት የመከራችንን ክብደት አንዳናይ አድርጎልናል። ትኩረታችን ጌታን አለከብሮ ማስፍ ላይ ብቻ አንዲሆን እደረገ። የመከራው አይነቱና ቁጥሩ በቃላት ለመግለጽ ያለቸግራል። ሆኖም ግን የአግዚአብሔር ጸጋ ከመጠን በላይ በዛልን። ጥቂቱን ለመግለጽ ያህል፦

ከእለታት አንድ ቀን የዋና አዉራጃዉ ካድሬ በጧቱ ወደ እኛ (ዱራሜ ከተማ ታስረን ወደ ነበርንበት) መጣና አለራታችን በምን ምክንያት እንደሆነ ጠየቀ። የሁሉም ወንጀል ስርቆት፣ ዝርፊያና የመሳሰሉት ነበር። እነዚህን ወንጀሎች ሁሉ እንደቀላል ቆጠረና ወደ እኔ ሲደርስ ይህስ ለምንድር ነዉ የታሰረዉ ብሎ ዘበኛዉን ሲጠየቅ «መፈከር አልልም ያለ ጴንጤ ነው» ብሎ ዘበኛዉ ሲመልስለት ካድሬው በእኔ ላይ ቁጣዉ ጋለ። ሁሉንም ወደ ማረሚያ ቤቱ ማረፊያ እንዲመለሱ አዘዘና አኔን ብቻ አራቁቴን በስደፍ እየገጨኝ ወደ ታወቀዉ መግረፊያ ከፍል ወሰደኝ። በግምት ቢያንስ ለሁለት ሰዓታት ያህል ደበደበኝ፤ እያንከባለለ ረገጠኝ፤ ኃይለኛ ጡንቻ ነበረዉና መልሶ መላልሶ ከአንዱ ግድግዳ ወደ ሌላ እየወረወረኝ በግድግዳዉ ላይ ያላትመኝ ነበር። በመጨረሻም እኔን ከመደብደቡ ብዛት የተነሳ የተደበደብኩ እኔ ሳለሁ እርሱን ኃይል ከዳዉና ደከመ። ስለዚህ ቆም ካለበት «መፈከር የማይል እፍህ አፈር ይብላ» ብሎ አፈር አጎረሰኝ።

ካድሬው ያስበዉ ነገር ለላልተላካስት ለአስር ቤቱ ዘበኞች በየቀኑ ጧትና ማታ አንዲገርፉኝ ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላለፈላቸው። ከዚያ በኋላ ያለዉ ጊዜ ለእኔ በእርግጥ እጅግ መራራ ነበር። አንዱ ዘበኛ እንድ ቀን ጀርባዬንና የአግሬን መዳፍ በጉማሬ አለንጋ ሲገርፈኝ ከሰዓት በኋላ የነበረዉን ስዓታት አሳለፈ። ምናልባትም ወደቁጥር ሊመነዘር ከ300-

400 የሚያህል ጉማሬ አለንጋ ጅራፍ በጀርባዬ ላይ እርፏል ለማለት ይቻላል። ከጀርባዬ የሚፈስዉን ደም ያዩ የእስር ቤት ታራሚዎች በሙሉ ሲጮሁ መስማቴ ከግርፋቴ ህመም የበለጠ ያሳቅቀኝ እንደነበር ዛሬም ከእዕምሮዬ የማይጠፋ ትዝታ ነዉ። የአግሬንም መዳፍ ብዙ ከገረፈ በኋላ እንደ ገና ዉኃ እያርከፈከፈ መግረፉን ይቀጥል ነበር። ከዚያ በኋላ ቢያንስ ለእንድ ሳምንት ያህል የተገረፍኩበት ጀርባ አላስተኛኝም ነበር። ስዉነቴ ለረዥም ጊዜ ተላ። ሆኖም ግን ከሁሉም የገረመኝ የአግዚአብሔር ፀጋ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ይበልጥ ያያሁት ያኔ ነበር።

እንባቢዎቼንም በጣም አደራ የምለዉ ጉዳይ ቢኖር የተቀበልኩትን መከራ ስመዘርዘር አይደለም ዓላማዬ። ነገር ግን ምናልባት ይህን መጽሐፍ ከሚያነቡት ለጥቂቶቹ ጌታ የሚናገራቸው ነገር ሊኖር ይችላል ብዬ ስላመንኩኝ ነዉ። ምክንያቱም እንዱ እኔን በመከራዉ ሰዓት ድፍረትና እምነት የሰጠኝ ነገር ቢኖር ሌሎች ለጌታ የከፈሉትን ዋጋ ማንበቤ፣ መስማቴና ማየቴ ነበርና። የጌታ ፀጋ ደግሞ ሁሉን የሚያስችል ነዉ። ፍቅሩ ደግሞ መከራችንን ሁሉ ያስረሳል። በወቅቱ የነፍስ ግድያ በጣም ቀላል ነበርና ይገርፈኝ የነበረዉ ካድሬ ጠብመንጃዉን ደጋግሞ በጎሮሮዬ ላይ በሚያነጣጥርበት ጊዜ እኔም ነፍሴን ለጌታ አደራ ሰጥቼ ነበር። በእስራቱ ወቅት የምተኛዉ ስዓት ጥቂት ነበር። ያለኝን ጊዜ በሙሉ አሳልፍ የነበረዉ በጸሎት ነበር። ከዚያ የተረፈዉን በመገረፍና በመደብደብ ነበር። ነገር ግን ጌታ ጊዜህ እልደረሰም ስላለኝ ብቻ ከእካላቴ እንዱም ከፍል አልጎደለም። ነፍሴም ያለጌታ ጊዜ ከሥጋዬ አልተለየችም። ያለፉትን 36 ዓመታት እግዚአብሔር ትርፍ ዓመታትን ዕድሜ ሰጥቶኝ በነፍስ ኖሬአለሁ ለማለት እችላለሁ። በምድር ላይ ያቆየኝንም ዓላማ በሚገባ እየተገነዘብኩ መጥቻስሁ። ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተማሪነት ዘመን

1970 ዓ.ም የአለራቴ ዓመት ነበር። በ1971 ዓ.ም ማትሪክ ፈተናን አልፌ በ1972 ዓ.ም ደግሞ ወደ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ አራት ኪሎ ሳይንስ ፋካልቲ የፊዝክስ ተማሪ በመሆን ትምህርቴን ቀጠልኩ። በዩንቨርስቲው ውስጥ የሚገኙ ከርስቲያን ተማሪዎች በተለያዩ አገልግሎቶች ሲሳተፉ፣ የእኔ ምርጫ ግን በፀሎት ቡድን ውስጥ ገብቼ ማገልገል ነበር። በዩንቨርስቲው በነበርኩባቸው 4 ዓመታት ውስጥ ሳስተባብርም ሆነ

አሳተፍ የነበረዉ በፀሎት ቡድን ዉስጥ ነበር። በአነዚያ ዓመታት ብዙ ታላላቅ በረከቶችን አግኝቻለሁ። ከኢትዮጵያ አራቱም አቅጣጫዎች ከመጡ ከርስቲያን ተማሪዎችና ከአኔ ጋር በፀሎት ቡድን ይሳተፉ ከነበሩ ወንድሞቼና አህቶቼ በኩል አግዚአብሔር ለሕይወቴ ዘመን ሁሉ የሚሆን አጅግ ብዙ ሰንቅ አለንቆኝ ነበር። በተለይም አብረዉኝ ያገለግሉ የነበሩ አሁን በነቀምት ዩኒቨርስቲ ሌከቸረር ተሰፋ በዳዳና፣ በአሁን ሰዓት በአንግሊዝ አገር አያገለገለ ያለ ወንድም ዘዉዴ ገብረ ሥላሴና አሁን በጀርመን አገር የምትኖር ዉልታ አብረን በጸሎት ጓድ ዉስጥ ሰናገለግል ነበር። ከአነርሱ ሕይወትና የጸሎት ትጋት አግዚአብሔር ብዙ ነገር አስተምሮኛል። አንዲሁም ትጋታቸዉ በኔ ላይ ዛሬም ድረስ ትልቅ ተጽዕኖ ፈጥሮብኛልና ሰለነርሱ ጌታ የተመሰገነ ይሁን።

ባሌ ሮቤ በመንግሥት ሥራ ዓለም

በ1975 ዓ.ም ትምህርቴን ጨርሼ ወደ መንግሥት ሥራ በ1976 ዓ.ም በህዳር ወር ተቀላቀልኩ። ለመንግስት ሥራ ባሌ አንደደረስኩ ሮቤ ቲቲአይ (Robe TTI) በፈዝዘለ አለተማሪነት ተመደብኩኝ። በአገሩ የነበሩ ጥቂት ከርስቲያኖች በወቅቱ የነበሩ የሶሻሊስት መንግሥት ባለሥልጣናት አላደዋቸው ነበርና በከፍሰ አገሩ ለመኖር ባለመቻላቸው ባሌን ለቅቀው ወደ ተለያዩ ከፍላተ ህገር ተበታትነዉ ነበር። በአርግጥ ከርስትናና ከርስቲያኖች በኢትዮጵያ ከሚጠሉባቸዉ ቦታዎች መካከል የመጀመሩያዉ ባሌ ነበር ለማለት ይቻላል። ነገር ግን ጌታ ትልቅ ዓላማ ስላለዉ አኔ ወደማልፈልግበት ከፍለ አገር ወሰደኝ። በተመደብኩበትም በሮቤ ከተማ የነበሩ የከርስቲያኖች ብዛታቸዉ አምብዛም ነበር። በዚያን ወቅት በጌታ አጅግ ትጉ ከነበሩ ወ/ሮ ጥሩነሽ አሻግሬ ጋር ከአራት የማንበልጥ የመንግስት ሰራተኞች (ማሬ፣ ዘለቀ ቢንጫሞ፣ ሙሉ ተስፋዬና አኔ) ብቻ በሮቤ ከተማ ዉስጥ ነበርን። በወቅቱም በከርስትና ስም መሰብሰብ በዚያን አገር አንደ ትልቅ ወንጀል ይቆጠር ነበር። ነገር ግን ከዘለቀ ቢንጫሞ ጋር ሆነን በሳምንት ሁለት ቀን በሰውር አየተገናኘን በያም መፀለይ ጀመርን። ቀስ በቀስ ደግሞም በከተማዉ ብቻቸዉን ከጌታ ጋር የነበሩትን ሰማቸዉን ከሳይ የጠሰኩትን ጥሩነሽ አሻግሬ የሚባሉ ታላቅ የፀሎት ሴት ነበሩና አርሳቸው ቤት በመሄድ በሰውር በመገናኘት መጸለይ ጀመርን። በብዙ መጨናነቅና ጥንቃቄ ተገናኝተን ሰለምንፀልይ ፀሎቱ ለኛ አጅግ ጣፋጭ ነበር። ቀስ በቀስ የአዳር ፀሎት ማካሄድ ጀመርን። በዚያ ሁሉ አጅግ በጣም ዝግ ባለ ድምጽ ነበር አንጸልይ የነበረዉ። ዝማሬ የሚታሰብም አልነበረም፤ በማንሳራጎር

ወይንም ድምጻችንን አጅግ በጣም ቀብረን ከመዘመር ያለፈ የጩሄት ዝማሬ አይታሰብም። ሁልጊዜ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር አግዚአብሔር አንዴት ባለ መልኩ ሸሽጐንና ሸፍኖን ያንን ከባድ ዘመን አንዳኖረን ነው።

በህብረት (በፌሎሽፕ) መልከ ተገናኝተን ሰናመልከ ነበርና ቀሰ በቀሰ የነፍሳት ቁጥር አየጨመረ መጣ። ኋላም የተለያዩ ወንጌላዉያን አብያተ ከርስቲያናት ማለትም ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ሕይወት፣ መሠረተ ከርስቶስና መካነ-ኢየሱስ ቤተከርስቲያናት ከ6 ዓመታት የፀሎት ጉዟችን በኋላ ተወለዱ። አንያንዳንዱ በየቤተ አምነቱ ማምለከ ጀመረ። በሕብረት ሰናመልከ ፍቅራችን አጅግ የላቀ ለለነበር ወደ አብያተከርስቲያናት መበታተናችን በሕብረቱ ዉስጥ ለነበርን አጅግ አሳዛኝ ነበረ። አልፎም ያቆሳሰለን ጉዳይ ነበር። ያም ከከፉት ሳይሆን አንዴት አንለያያለን? የሚል ጤናማና ዉሰጣዊ በሆነ በጠለቀ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ትስስር ነበረን። ነገር ግን ጌታ ለበጎና ለበለጠ እድገት ምክንያት ያደረገዉ መሆኑ ቆይቶ ነበር የገባን።

ከተሰያየን በኋላ ትዝ የሚለኝ ነገር ቢኖር እያንዳንዱ ቤተ እምነት አምልኮውን ሲጀምር ዋና መታወቂያዉ ፀሎት መሆኑ ነበር። እኔ በማገለግልባት በሮቤ ቃ/ሕ/ቤ/ከ ውስጥ ረቡዕና ቅዳሜ ሕዝቡ በአጠቃላይ በያም ፀሎት ይተጋ ነበር። በአሁድ አምልኮ በ2 ሰዓት ለሚጀምረው አምልኮ ልከ 12:00 ሰዓት ላይ የቤተ ከርስቲያኒቱ ምዕመን ግጥም ብሎ ሞልቶ ከአምልኮ በፊት ለሁለት ሰዓታት ያህል በታሳቅ መነቃቃት ይፀልይ ነበር። ከዚያ የተነሳ በየአሁድ አምልኮ ላይ ማንም አገልጋይ ወደ መድረከ ከወጣ ታላቅ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይለኮሰበት ነበር። ንግግር አንኳ በሚገባ የማይችል ሰው ኃይለኛ ሰባኪ ሆኖ ሲሰብክ ማየት የተለመደ ነበር። በፀሎት ዕለት፣ በአምልኮ ቀንና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥባቸው ቀናት አዳዲስ አማኞችን አጋንንት አየጮኸ ሲያነከባልል ወይንም ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አየተሞሉ ሲንከባለሉ ማስተናገድ የጥቂቶቻችን ተግባር ሆኖ ነበር። ከአምልኮ በኋላ ሰው በቀላሉ ተላቆ ወደ ቤት አይሄድም። ምክንያቱም በቃላት ሲገለጽ የማይቻል አጋፔ ፍቅር በቅዱሳን መካከል በግልፅ ይታይ ነበርና። የምዕመኑ እድገት በጣም ፈጣን ስለነበር በአጭር ጊዜ ውስጥ ከቤተከርስቲያኑ ምዕመን አብዛኛው በተሰያዩ አገልግሎቶች ይሳተፍ ጀመር። ብዙዎች ተነስተው ሲሰብኩ ሰናይ ብዙዎቻችን ነፍስ አለከማይቀርልን ድረስ በደስታ አንዋጥ ነበር። ምክንያቱም ትናንትና ጌታን የተቀበሉና በአጃችን የተጠመቁ ዛሬ ከአኛ ነባሮች ከምንባል በብዙ

እጥፍ በላቀ ሁኔታ ሲሰብኩ፣ ሲያስተምሩ፣ ሲፀልዩና ሲያስመልኩ ማየት ለኛ የድንቅ ድንቅ ነበርና።

በዱራሜና እካባቢዉ የነበረኝ እገልግሎት

በ1985 ዓ/ም መጀመሪያ ላይ ጌታ የባሌ ኑሮ፤ አገልግሎትና ሥራ ይበቃችኃል አለና ሳንፈልግ አኔንና ባለቤቴን ከሶስት ልጆቻችን (ድልየአብ፤ ድያያና ኢዮአብ) ጋር ወደ ደቡብ ከልል እንድንዛወር አደረገን። እሁን ካሉን አምስት ልጆች መካከል ሁለቱ (ሳሙልና ኢዮሰያስ) የተወለዱት ወደ ዱረሜ ከተዛወርን በኃላ ነዉ። በዚያን ወቅት ለካስ አግዚአብሔር ያየ ትልቅ ነገር ለላለዉ ነበር ወደ ተወሰድኩበት እካባቢ እንድንዛወር ያደረገን። የተወሰድኩበትና ያደግሁት ከላይ እንደገለጽኩ በዛሬ እስተዳደር በደቡብ ከልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ቀዲዳ ጋሜላ ወረደ በዱራሜ ከተማ ጥግ ባለችዉ በቀጀሌ ገበሬ ማህበር ዉስጥ ነው። አኔና ባለቤቴ ተዛውረን ከመጣን በኃላ በዱራሜ ከተማ ቤት ተከራይተን የመንግስት ሥራችንን መሥራት ጀመርን። ከዚህ ቀደም የሚያውቁኝ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ሰአገልግሎት ይጋብዙኝ ነበርና የተሰያዩ አብያተ- ክርስቲያናት በሚከፍቱ በተለያዩ ፕሮገራሞችና ኮንፍራንሶች ማገልገል ጀመርኩ።

ከወንድሞቼ ጋር የጸሎት ጉዞ

ትንሽ ወደ ኃላ መለስ ልበልና ስለ እበበ ላንገና የአኔ ተከታይ ታናሽ ወንድሜ ጥቂት ነገር ልበል። ይህ ወንድሜ በልጅነቱ ዘመን በባህርዩ በጣም አስቸጋሪ ልጅ ነበር። በተለይ በተከታታይ የተወለድን ለለነበር ሁሌ ይጣላኝ ነበር። አኔም እገልግሎት ጀምሬ በነበርኩበት ወቅት ከአገልግሎት ቦታ ሰመለስ ለኔ የመጀመሪያዉ መሰቀል አርሱ ነበር። ነገር ግን ቀሰ እያልኩ ኖአባቴ ወደ ነበረዉ ማሳ ወዳለዉ አንለት ዉስጥ ይዤው አየሄድኩ ስለጌታ ማንነት በሚገባ መስከርኩለት። እዚየዉ የጌታ ደቀመዝሙር አደረግሁት። በየቀኑም አብሬዉ አጸልይ ነበር፤ ስለጸሎትም አለተምረዉ ነበር። ከዚያ በኃላ ሕይወቱ ልከ አንደ ሐዋሪያዉ ጳዉሎስ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ።

ከ1970-1973 ዓ.ም ጥቂቶቻችን አየታደንን በምንታሰርበት ወቅት ታላቅ የፀሎት ንቅናቄ ተነስቶ ነበርና በነበረው መነቃቃት ግምባር ቀደም ከሆኑ ከጸሎት አገልጋዮች አርሱና ሦስቱ ጓደኞቹ (አየለ፤ አንድሪያስና ማቴዎስ የሚባሉ) በመንደራችን ዉስጥ የጸሎት እሳትን አቀጣጠሉ። አበበ ከዚያ

ቀደም ለእኔ የመከራ ምክንያት ነበረ። አሁን ይልቁን ከሚጸልዩልኝ መካከል የመጀመሪያዉ ሰዉ ሆነ። ከዚህም የተነሳ እበበና ጓደኞቹ በሶሻሊዝም ካድሬዎች ተለደዉ በቀበሌና በወረዳ እስር ቤቶች እንደ አኔዉ ታሰሩ። አዉነቱን ለመናገር በወቅቱ እኔ ያልነበረኝ ታላቅ የጸሎት ትጋት በእነርሱ ላይ ፈሰሶ ስለነበር በዚያች መንደር የነበሩ አጋንንት ከመጠን በላይ ይራወጡ ጀመር። ቆይቶም አልቀረም በዚያን አካባቢ ከፍተኛ መንፈሳዊ ንቅናቄ በዚያን ወቅት ተፈጥሮ ነበር።

በኃላም አበበ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጨርሶ በባሌ ምድር መምህር ሆኖ ለብዙ ዓመታት ሲሠራ ቢቆይም የጌታን ጥሪ በመቀበል የመንግስትን ሥራ ለቅቆ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በመማር የባሌ ሮቤ ቤ/ከ መጋቢ ሆኖ ለ3 ዓመታት አገለገለ። ከዚያም የቲኦሎጂ ድግሪውን በእዲስ እበባ ኢቲሲ ጨርሶ የጠዛ መጽ/ቅ/ት/ቤት ዳይሬክተር ሆኖ ለ6 ዓመታት ካገለገለ በኃላ ሁለተኛ ድግሪውን ለመማር/ለመቀበል ፊተና ለመፈተን አዲስ አበባ አየሄደ መንገድ ላይ እያለ አኔ ሚስዮናዊ አንድትሆን አፈልጋለሁና ከምትሄደበት አቅጣጫ ተመለስ የሚል የጌታን ድምጽ ሰማና ይሄድ ከነበረበት ጉዞ ተመለሰ። ለሚስዮን አገልግሎትም ለመዘጋጀት በዱራሜ በሚገኘዉ የሚስዮናውያን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ገቡቶ ከባለቤቱ ከአበበች ዳርስቦ ጋር ለሚስዮናዊነት ራሳቸዉን ካዘጋጁ በኃላ ወደ ደቡብ ሱዳን በመሄድ ላለፉት 6 ዓመታት አግዚአብሔር በሁለቱም ታላላቅ ሥራዎችን ሰርቶ የሚሸን ተልዕኮአቸውን እደራ ሲወጡ ከቆዩ በኃላ የአግልግሎት ተርማቸዉን ጨርሰዉ በዚህን ጊዜ በኬንያ ናይሮቢ መንፈሳዊ ትምህርት በመማር ላይ ይገኛሉ። በጣም ደስ የሚያሰኘኝ ነገር ቢኖር እበበ ፀሎት እንደሚወድ ሁሉ ባለቤቱም አበበች ደግሞ የበለጠውን ጸሎት ወዳጅ መሆኗ ነው። ከዚህም ከፀሎት ትጋታቸው የተነሳ የ6ቱንም ዓመታት የደቡብ ሱዳንን ሙቀት (አንዳንዴ አለከ 52°c የሚደርሰውን ሐሩር) የተቋቋሙት በጌታ ፀጋና በጸሎታቸው ትጋት ነው ለማለት አችላለሁ። እግዚአብሔር ለአኔ ከሰጠኝ የጸሎት ደቀመዛሙርት መካከልም አበበ የመጀመሪያው በመሆኑና አርሱንና ባለቤቱን አግዚአብሔር አጅግ ውጤታማ ሚስዮናዊ ቤተሰብ ስላደረጋቸው ነፍሴ ሁሌ በጌታ ሀሴት ታደርጋለች። ክብር ለጌታ ይሁን።

ሁለተኛው ወንድሜ የእበበ ታናሽ የሆነው ታምሩ ላንገና ይባላል። ከ1986 ዓ.ም በቀጀሌ ለፈነዳው ሪቫይቫል ግምባር ቀደም አርሱና ጥቂት ጓደኞቹ ናቸው። በ1976 ዓ.ም 4 ወጣቶች በጸሎት ሲደራጁ አንዱ እርሱ ነበር። እነርሱም ፀሎቱን በቀጠሉ ቁጥር ሰደቱ ከየአቅጣጫው

ቢጧጧፍባቸውም አግዚአብሔር አስገራሚ ጽናትን ሰጥቶአቸው ነበር። በሥጋቸው፣ በሰይጣንና በሰው በከፉ የተገዳደራቸውን ፈተና በመቋቋማቸው አግዚአብሔር አስገራሚ ውጤትን በማምጣቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሪቫይቫል ማዕከል እንድትሆን ምክንያት አድርጐ ተጠቅሞባቸው ነበር። ክዚያም ባሻገር ታምሩ በትምህርት ወደ ፊት ሰመግፋት ቢፈልግም እግዚአብሔር ወደ ሙሉ ጊዜ አገልጋይነት አቅጣጫውን ቀየረ። የቤተክርስቲያኒቱ ሙሉ ጊዜ አገልጋይ በመሆኑ በተለይም ወ/ሮ ተሰማ ሰተሞና አርሱን የቤተ ክርስቲያኒቱ ፀሎት አንደተቀጣጠለ እንዲቀጥል ጌታ ከተጠቀመባቸው መካከል ሁሰቱ መንትያ መላሪያዎችና መሪዎች ናቸው።

ታዲያ በዚያን ዘመን የእግዚአብሔር መንፈሰ የሰጠኝ ብቸኛ አገልግሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉሰጥ በፀሎት ላይ ሥሰበክና ማሰተማር ነበር። ሰለ ፀሎት እሰተምሬ ደግሞ በየቤተክርስቲያኒቱ በየዕሰቱ በፆም ፀሎት አየፀሰዩ የሚውሱ የተሰያዩ የፀሎት ቡድኖችን ማደራጀት ነበር። በዚያን ወቅት ምናልባትም ከ150-200 የሚደርሱ አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ደርሼ አገልግያለሁ ለማለት ይቻላል። የሚገርም ነገር ቢኖር በሰበከሁበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአያንዳንዱ በሳምንቱ ቀናት ውሰጥ የሚፀልይ የፀሎት ቡድን ማደራጀቴ ነበር። የፀሎት ቡድኖቹ ተደራጅተው መፀለይ በጀመሩበት አጥቢያዎች በሙሉ መንፈሳዊ መነቃቃት ተከሰቷል። ከአነዚያም ታሳቅ መነቃቃት ከተከሰተባቸው ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ ተወልጄ ያደግኩባት የራሴ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሆነችው የቀጀሌ ቃ/ሕ/ቤተክርስቲያን ናት። በዚህች ቤተክርስቲያን የተከሰተዉን ንቅናቄ ራሱን የቻለ ተሞክሮ አድርጌ በሚቀጥለዉ ከፍል አቅርባለሁ።

በየአጥቢያውና በየእካባቢዉ የተከሰተው መነቃቃት ብዙዎቹን ወደ አምባርቾ ተራራ ወጥተው አንዲጸልዩ አደረጋቸው። ከዚህ ነው የአምባርቾ ዓለም አቀፍ የጸሎትና የወንጌል አገልግሎት የሚባለው ዛሬ ኢትዮጵያ አቀፍና ብሎም ለአህጉርና ሰዓለም የሚሆን ራዕይ የተወለደዉ። ይህንንም ደግሞ ራሱን የቻለ የጸሎትና የወንጌል ንቅናቄ ተሞክሮ ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ ባለዉ ከፍል ቀርቧል። እኔም የዚህን ንቅናቄ መሥራችና ዳይሬከተር ሆኜ በአሁን ሰዓት በማገልገል ላይ አገኛለሁ። በዚህ የፀሎት ንቅናቄ እልፎ በተለያዩ ክልሎችና ከተሞች የጸሎት ንቅናቄ መፍጠሪያ ሰልጠናዎች አየተሰጡ በመሆኑ በአገሪቱ በጐ ተጽእኖ ፈጣሪ ምልክቶችና ከስተቶች አየታዩ ናቸውና ከብር ለጌታ ይሁን!!

የሚሽን ትምህርት ቤት

በሲንጋፖር በሚሽን የማሰተርስ ድግሪዬን ሰማር በሚሽን ላይ ጸሎት ስላሰዉ በጎ ተጽዕኖ ብዙ መጻሕፍትን አንብቤ ነበር። ደግሞም ዶ/ር ጆን ካይዘር የሚባሉ የቤታኒ አስኩል አፍ ሚሽን - ለንጋፖር ለሚባለዉ ኮሌጅ ዳይሬከተራችን ሰለ ጸሎትና ሚሽን ቁርኝት አበክረዉ ይናገሩ የነበረዉ ጉዳይ በልቤ ቀርቶ ነበር። እኔና ጓደኛዬ አየለ ዩቱራ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰን የምንጀምረዉን ት/ቤት በሚመለከት ጸሎትን በምን መልኩ የትምህርት ቤቱ ካርኩለም ዉሰጥ አንደምናስገባና በምንጀምረዉ ትምህርት ቤት ጸሎትን አንዴት አንደምናካሄድ አንመካከር ነበር። በኋላም ትምህርት ቤቱ በ1993 ዓ.ም በግንቦት ወር ተጀመረ። ትምህርት ቤቱ ሲጀምር የሚከተሉት የጸሎት ፕሮግራሞች ከትምህርቱ ጎን ተጀመሩ፡-

- ለኛ ሰኛ ከጥዋት ከ12፡00 አሰከ ቀኑ ዘ፡00 የፆም ጸሎት ለዓት አንዲሆን ተደረገ፤
- እያንዳንዱ ዶርም ያለ ተማሪ በየዶርሙ በሳምንት አንድ የተሰየ ቀን በፆም ጸሎት አንዲያሳልፍ ተደረገ፤
- በየቀኑ ከማለዳ ከ11፡00-12፡30፡00 ለዓት ድረሰ የጸሎት ጊዜ ሆነ፤
- በየምሽቱ ከ12፡00-1፡00 ድረሰም የጸሎት ጊዜ ሆነ፤
- በየወሩ መጨረሻ ሦለት ቀናትን (ቅዳሜ፤ አሁድና ሰኛ) በተከታታይ የጸሎት ጊዜ እንዲሆን ተደረገ፤
- በሳምንት አንድ ቀን አንዱ ተማሪ ለሌላዉ የሚጸልይበት ጊዜ ተፈጠረ፤

ታዲያ ከዚያ የተነሳ ተማሪዉ ከሁለት ዓመታት ትምህርት በኋላ ክተማራቸዉ ከ25 በላይ ኮርሶች ይልቅ በሚገባ ተምሬ ወጣሁ ይል የነበረዉ ሰለ ጸሎት ነበር። ዛሬም ያሉት የትምህርት ቤቱ አመራር አካላት በጣም ጸሎት የሚወዱ ናቸዉ። ያ የጸሎት ልምምድ እሰከ ዛሬ መቀጠሉ ሰለዚህ ትምህርት ቤት ነፍሴ ሁሰጊዜ ሐሴት ታደርጋለች። ተማሪዎቹ በየሰኛ በትምህርት ቤቱ የተለማማዱትን የፆም የጸሎት ልምምድ በጌዱበት የሚሽን ፊልድም አንደቀጠሉ በየደረሰኩበት ሳገኛቸዉ ከሚመሰከሩልኝ ምለከርነት ለመረዳት ችያለሁ። ከዚያም የተነሳ ሚሰዮናዉያኑ በየደረሱበት እጅግ በጣም ዉጤታሞች ናቸዉ። ለዚሁም ከብር ሁሉ ለጌታ ይሁን።

9. አምባርኞ ዓለም አቀፍ የጸሎትና የወንጌል ተልዕኮ ንቅናቄ (ኤ ኤይ ፕ ኤም) ዉልደትና እድገቱ

አኔ ተወልጀ ባደግሁባት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ዱራሜ በምትባል ከተማ ጥግ ያለውና በደቡብ ክልል ትልቁ (ረዥሙ) ተራራ በሚባለው (3.028 8ሜትር ወይም 9,934 ጫማ ከባህር ወለል በላይ ከፍታ ባለዉ) በአምባርኞ ተራራ ላይ ለብዙ መቶ ዓመታት አባስሬኞ የሚባል የጠንቋይ ቤተሰብ ይመለከ ነበር። አባስሬኞ የሚለዉ ስም የጠንቋዮቹ የቤተሰብ ስም (Family name) ነዉ እንጂ የአንድ ጠንቋይ ስም ብቻ አይደለም። አባት አባሰሬኞ ሲሞት ተከታይ ወይንም መንፈሱን ወራሽ አባስሬኞ አየተቀበለ ቢያንስ ከ500-700 ዓመታት በላይ በአምባርኞ ተራራ ላይ ተመልኳል።

የአምልኮ ሥርዓቱ በየዓመቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች መስዋዕት ይዘዉ አየዘፈኑ ወደ ተራራዉ አናት ላይ ይወጣሉ። የወቅቱ አባሰሬኞ ደግሞ በወንበሩ ላይ ተቀምጦ አምላኪዉን ሕዝብ ይጠባበቃል። ሕዝቡም ከስላሣ የተለያዩ የብሔረሰቡ አካባቢዎች ይመጣና በአንድ ላይ ተሰባስቦ በዘመኑ «ማፋታ» የሚባል ዘፈን አየዘፈነ፣ አባሰሬኞን እያሟገስ ሲቀርብ በወንበሩ ላይ የተቀመጠዉ ጠንቋዩ አባሰሬኞ አየዘለለ ይነሳና ሕዝቡን ይቀላቀላል። ከዚያም በኋላ ዘንዶ ወዳለበት የቃል ኪዳን ድንጋይ ወደሚባል ዋሻ በሕዝቡ ታጅቦ ይሄዳል። አባሰሬኞዉ በእግሩ ገመድ ታስሮ ዘንዶዉ ወዳለበት ወደ ድንጋዩ ዋሻ ይገባል። በዚያም ከዘንዶዉ ጋር ቃልኪዳን በማድረግ ከዋሻዉ ዉስጥ ትልቅ ኃይል አግኝቶ ይወጣል። ሕዝቡን ይባርካል፤ ሰርሱ የሚይጉበረዉንና አርሱን የሚያመልከዉን አንደሚያጠፋ በዛቻ ይናገራል። ይራገማልም። እርሱ የሕዝቡ (የከምባታ ሕዝብ) ፈጣሪ አምላክ እንደሆነ ይነግራቸዋል። ሕዝቡም ደግሞ አዎን ልክ ነዉ በማለት እዉነት እንደሆነ አድርጎ በመቀበል አምላካችን ነዉ ብሎ ያመልከዋል። ከዚያም በላይ ደግሞ ለሕዝቡ ዝናብ ሕይወቱ ነዉና ዝናብ ሰጪ አምላክ እርሱ እንደሆነ ይነግራቸዋል፤ ሕዝቡም ለዝናብ ተማጽኖት፣ በመጨረሻም የጥድ ዝንጣፊ ለእያንዳንዱ ሰዉ ተሰጥቶ ወደመጣበት ቀበሌ እየዘፈነ ይመለሳል። ለአባሰሬኞ ይዞ የመጣዉን መስዋዕትና ስጦታ ሕዝቡ በማስረከብ የልመና ዘፈን እየዘፈነ እንደመጣ ሁሉ የምስጋና ዘፈን አየዘፈነ ወደ መንደሩና ወደ ቤተሰቡ ይመለሳል። አንዲህ ሲል፡- «አባሰሬኞ መስዋዕታችንን ተቀብሏል። ዝናብንም አስጣለሁ ብሏል። የጥድ

ዝንጣፊም ልኮላችኋል» አያለ በጉጉት አየተጠባባቀ ወደ ነበረዉ ቤተሰብና መንደር ይመለሳል።

ከዚያም በላይ የከምባታ ብሔረሰብ ከአጠቃላይ ከኢትዮጵያ የተሰባሰበ ብሔረሰብ ነዉ ይባላል። አንዲያዉም ብዙ ጥናቶች አንደሚያመለክቱ ከሆነ ከ140-160 የሚደርሱ የተለያዩ ጎሳዎች የመጡ ዘሮች ስብስብ ነዉ። በመሆኑም ከየመጣበት የየራሱን አምልኮና የአምላኩን ስም አየጠራ በዘሩ መካከል አንዱን ቤተሰብ የአምልኮ መሪ በማድረግ ያነግሳል። መንፈሱ በዚያ ቤተሰብ ዉስጥ በሚሰየም ሰዉ ላይ ይወርድና በየዘሩ ጠንቋይ ይሆናል። ታዲያ አባሰሬኞ የአነዚህ ሁሉ የበላይ እለቃ የሆነ አምላክ ነበር ማለት ነዉ። በተጨማሪም በየቤተሰቡ ደግሞ ሁሉ ሰዉ ማለት ይቻላል ስም የወጣለት የሚመለክ መንፈስ አለ። ወንዱ ጃራ የሚባልና ሴቷ ደግሞ ወጣ የሚባል መንፈለ በእያንዳንዱ ግለሰብ (በተለይም በአባትና አናት) ላይ ራሱን ይገልጥባቸዋል። በመሆኑም በአያንዳንዱ ደረጃ ራሱን የሚገልጥ መንፈስ ቀይ፣ ነጭ፣ ገብስማ፣ ጥቁር ዶሮ፣ ኮርማና ሙኩት እምጡልኝ አለበለዚያ አናንተን፣ ልጆቻችሁን፣ ንብረታችሁንና ከብታችሁን አጨርሳለሁ አያለ ስለሚፎክር ሰዉ አርብቶና አልምቶ በመጠቀም ፈንታ ለሰይጣን አየገበረ መኖር በአካባቢው የተለመደ ነበረ።

ስደትና የከርስትና እድገት

ነገር ግን እግዚአብሔር ዘመናትን ቆጥሮ በ1920ዎቹ ላይ ከዉጪ አገር የኤስ አይ ኤም (SIM) ሚስዮናዉንን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ላከ። ከ1923 ዓ.ም ጀምሮ ተልከዉ በሁለቱም አካባቢ ወንጌልን ለማድረስና ለማስፋፋት ብዙ ጥረት አድረገዉ ነበር።ነገር ግን ጌታን ተቀብለዉ በአምነታቸዉ ጸንተዉ ነበር የሚባልላቸዉ አቶ ስብሮና አቶ ሽጉጤ ነበሩ። ከዚያ በኋላ በ1928ዓ.ም በተከሰተዉ የጣልያን ወረራ ምክንያት በደቡብ ኢትዮጵያ የነበሩ ሚስዮናዉያን ኢትዮጵያን ለመልቀቅ ተገደዱ።

የሚገርመዉ ነገር የስደትና የቤተ ክርስትያን አድገት እላት አብሮ አንድ ላይ ነደዱ። ሚስዮናዉያን ለስምንት ዓመታት በወላይታ አገልግለዉ 48 ሰዉ ብቻ አጥምቀዉ ነበር። ነገር ግን በከምባታና ሐድያ ሁለቱን ሠዎች ማለትም ስብሮንና ሹጉጤን ብቻ ነበር ሚስዮዉያኑ አጥምቀዉ አገር የለቀቁት ። በወቅቱ በአጠቃላይ በደቡብ ኢትዮጵያ ከ100 የማይበልጡ አማኞች አንደነበሩ ሬይሞንድ ዬቪስ ጠረጋ/የተራራዉ አሳት (Fire on the Mountain) በሚል በጻፉት መጽሐፋቸዉ በታሪክ አስቀምጠዋል።

ነገር ግን ሚሰዮናዉያኑ በቆዩበት ወቅት የዘሩት የአግዚአብሔር ቃል ዘርና የጸለዩት ጸሎት ጣልያን አዳዲሶቹን ምዕመናንን አያስደደ አያለም ትልቅ ፍሬ አንዲያፈራ አድርጓል። በጣልያኑ ወረራ ወቅት ጌታን የተቀበሉ አባጎሌ የሚባሉ አበት ታላቅ የወንጌል አርበኛ በመሆን የወንጌሉን አሳት አቀጣጠሉ። ወደ ወላይታም ከ5 ዓመታት በኋላ ሚሰዮናዉያን ሲመለሱ ከ15,000 ሠዎች በላይ፣ አንዲሁም ደግሞ በከምባታና ሐዲያ 10,000 በላይ አማኞች አንደነበሩ ይነገራል። ይህ በራሱ ታላቅና በታሪከ ዓይነተኛ ንቅናቄ ነበር ማለት ያቻላል። ምከንያቱም እነዚያ ያልተማሩ አባቶች ማንበብ ባይችሉም አንኳ የቀንና የሌሊት ጸሎታቸዉ ወደር አልነበረውም። አባባ ሚቆሬ ዶሌቦ አንጋፋ የአምነት አባት ሲናገሩ ያኔ ከርስትና በጀመረበት ወቅትና በኋላም የጸሎት ፕሮግራሞችን ለማካሄድና ለመካፈል አሰክ 8 ሰዓት ያህል ተጉዘን አንሄድ ነበር ብለው የነገሩኝ አሰካሁን ድረስ አልረሳሁትም። ዛሬ የ5 ደቂቃ ርቀት ባለዉ ቤተክርስቲያን የሚካሄደዉን የጸሎት ፕሮግራም አንኳ ለመካፈል ያለን ተነሳሽነት ምን ያህል ነዉ?

ወደ ታሪኩ ልመለሰና በ1930 ዓ.ም ላይ አቶ ኤደሞ የሚባል ሰዉ ወንጌልን በመቀበል የመጀመሪያዉ የከምባታ ብሔረሰብ አማኝ ሆነ። ታዲያ ከርስትና በአካባቢዉ ሲጀምር ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ ጠንቋዮችን የሚያመልከ ስለነበር የመጀመሪያዎቹ የአምነት አባቶች ከፍተኛ ለሆነ ስደት በመዳረጋቸዉ ከፍተኛ የሆነ መሰዋዕትነትን ከፍለዋል። ብዙዎች ንብረታቸዉን ተዘርፈዋል፤ ብዙዎች በእስር ቤት በሰብለዋል፤ ብዙዎች በዱላ ተደብድበዋል፤ በጠብመንጃ ሰደፍ ያለርህራሔ ተገጭተዋል፤ በጉማሬ አለንጋ በሰጭካኔ ተገርፈዋል። አንደነ ፈታሞና ቦቄ ያሉ በሆሳዕና ከተማ እየተደበደቡ ሕይወታቸዉ አልፋለች። አንደነ ፉዕኑሮና መንታሞ ያሉ ደግሞ በአሰላ ከተማ ባለዉ አሰር ቤት (አሰላ ያኔ የከምባታና ሐድያ አዉራጃን የሚያስተዳድር የጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ ነበረች) ለብዙ ዓመታት በሰብሰዉ ወደ ቤታቸዉ ሳይመለሱ አዚያዉ ሞተዉ አዚያዉ በአሰላ ከተማ ተቀብረዋል። ሌሎችም ስማቸዉን አዚህ ያልጠቀሰኩአቸዉ አባቶች ለዚህ ወንጌል ሕይወታቸዉን ሰውተዋል። አነፎቼ ያግሞ ለ10 ዓመታት ያህል ከታሰሩ በኋላ ተፈትተዉ ለብዙ ዓመታት ቤተክርስቲያንን ካገለገሉ በኋላ ወደ ጌታ ሄደዋል። አንደነ ባቦ ባቾሬ፣ ዋከቦ ባቾሬ፣ ስጋሮ፣ሻሜቦ፣ ዲንዳሞ፣ ሄራሞ፣ ሚቆሬ፤ አጤቦ፤ ወንታሞ ያሉና ሌሎች ስማቸዉን በዚህ ሰፍራ ያልጠቃሰኳቸዉ የእምነት አርበኛ የሆኑ አባቶች በአካባቢ፣ በወረዳ፣ በአዉራጃና በየከፍለ ሀገሩ ትልቅ ዋጋ ከፍለዋል። በወቅቱ ወጣቶች ቢሆኑም በትልቅ የወንጌል አሳት

ልባቸዉ የተቀጣጠለ አንደነ ያዕቆብ ባፋ፣ ሽፈራዉ አላኮ፣ ዮሐንስ መኪሶ፣ ተስፈ ጸዮን ዳለሎ የመሳሰሉ ሰንቅ አቀባዮችና የፈደል ትምህርትና የወንጌል አስተማሪዎች ነበሩ። ሌሎችም ለከርስትና ትልቅ ዋጋ የከፈሉ አባቶችን ሰም አዘረዝራለሁ ብል ገፆች አይበቁኝም።

ታዲያ ለዚህ ከርስትና መስፋፋትና ጥንካሬ ምከንያት የሆኑት የአገሬዉ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ አግዚአብሔር ለዚያ ዘመን ሆን ብሎ የላካቸዉ ሚስተር አስፓር፣ ጉስታቭ ካይዘር፣ ራልፍ ጀከብሴን፣ ሚስተር ዊቲሊ፣ ጆን ካማቦል፣ሚስተር ራስላፍ፣ በኋላም ዴቪድ ሜይ፣ ቴድ ካይዘርና ቤተሰቦቻቸዉ አንዲሁም ከአነርሱ ጋርና በኋላም የተላኩ የኤስ አይ ኤም ሚሰዮናዉያን እጅግ ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል። ከዚህም የተነሳ አካባቢዉ በወንጌል በጋይል ሊጥለቀለቅ ችሏል። በተለይም ጉስታቭ ካይዘርና ራልፍ ጀከብሰን ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በጠዛ ግቢ በመክፈት ብዙዎችን በማስተማርና ለቀሩት ለጎልማሶችና ለወጣቶች በየሳምንቱ ሁለት ቀናት ያግሞ ጠለቅ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይሰጡ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በአካባቢዉ መከፈት የከርስትና አምነት ጠንካራ አንዲሆን አድርገዋል። ደግሞም 17ቱን የስደት ዘመን ቤተክርስቲያን ሳትዘጋ በከምባታና ሐዲያ አካባቢ ብቻ አግዚአብሔር ምድሪቱን ጎብኝቶ ዛሬ ሕዝቡ 94% በላይ ከርስቲያን ሆኗል። በዚህን ወቅት ከኤ አይ ፕ ኤም ሚሰዮናዉያን ጋር በአንድ ላይ ከ300 በላይ ሚሰዮናዉያን ከአካባቢዉ ወጥተዉ በሌላ አካባቢ ወንጌልን አያሰራጩ ይገኛሉ። በአምባሪቾ አናትም ላይ አየተመለከ የነበሩ ተከታታይ አባለሬቾዎች 22 እንደነበሩ ይነገራል። ከአነዚህም የመጨረሻዉ ማለትም 22ኛዉ አባሰሬቾ ዛሬም (በ2006ዓ.ም) በሕይወት ያለ ሲሆን ከድል አድራጊ ወንጌል የተነሳ በአሁን ሰዓት አርሱም ጌታን ተቀብሏል። ከብር ለኢየሱሳ ይሁን።

የአምባርቾ ተራራ የጸሎት ንቅናቄ መወለድና አድገቱ

ስለመለረታዊ ሀሳቡ ይህን ያህል ካልኩ ወደ ተጀመረዉ ንቅናቄ ታሪከ ልመለስ። ለብዙ ዓመታት ብዙ ሰዎች ማለትም ከዉጪ የመጡ ሚሽነሪዎች፣ የአምነት አባቶቻቸን፣ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችና የተለያዩ ሰዎች ወደ አምባርቾ ተራራ አናት ላይ እንደ ጉብኝትም፣ ሆን ብለዉም ይሁን ለጸሎት ወደ ተራራው በመዉጣት ሲጸልዩ ቆይተዋል። ያንን ጸሎት አግዚአብሔር ሰምቷል። ነገር ግን ነገር ሁሉ በጊዜዉ ዉብ አድርጎ መሥራት ልማዱ የሆነ አምላከ የኢትዮጵያን

ሶሻሊዝም (ኮሙኒዝም) ሥርዓት ወድቆ ኢህአዴግ አገሩን በመሪነት ሊረከብ ተቃርቦ በነበረበት ጊዜ (1981 ጀምሮ ማለት ነዉ) ጥቂት ወጣቶች ወደ እምባርቾ ተራራ እናት ላይ ወጥተው መፀለይ ጀመሩ። በወቅቱ መጸለይ የጀመሩትም ወጣቶች ከ5 እንደማይበልጡም ይነገራል። ነገር ግን ይህ ጸሎት ቀስ በቀስ ንቅናቄ ወደመሆን ተቀየረ።

ትውልዴ በዚህ አከባቢ በመሆኑ ለብዙ ዓመታት በዚህ አከባቢ የፀሎት ንቅናቄ አንዲፈጠር በጌታ ፊት ለብዙ ዓመታት አምባ አፍሰሻለሁ። ደግሞም የፊዝከስ መምህር ሆኜ በባሌ እያስተማርኩ እያለ፣ ከባሌም ተዛዉሬ በዱራሜ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት በማስተምርበትም ወቅትና ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ራሴን ከሰጠሁም በኋላ ቢያንስ ወደ 200 የሚደርሱ አጥቢያዎችን ተዘዋውሬ ስለ ፀሎት ስልጠናና ስብከት በአምልኮዎች፣ በኮንፍራንሶች፣ በሴሜናሪች ላይ መስበኬን፣ ማስተማሬንና ማስልጠኔን አስታውሳለሁ። (ስለራሴ የጸሎት ልምምድና ዕድገት ራሱን የቻለ ምዕራፍ ላይ አስፍሬአለሁና ይመልከቱ)። አግዚአብሔርም በጎ ዓላማው ስለነበረ በእነዚህ ስልጠናዎች የፀሎት ሀሳብ የተቀበሉ ብዙዎች በተለይም ወጣቶች ወደ መንፈሳዊ መነቃቃት ውስጥ ገብተዋል። እግዚአብሔርም በተራራ ላይ እንዲጸልዩ ልባቸውን ያነሳሳቸው ወደ ተራራው ወጥተው መፀለይ ጀምረዋል። ይህም ደግሞ የጋራ የፀሎት ቀን ሆኖ በዓመት አንድ ጊዜ ለፀሎት መሰብሰብ የተጀመረዉ በ1990 ዓ.ም 500 በሚያህሉ ሰዎች ነበር። ዛሬ ከ15 ዓመታት በኋላ ከ150,000 የሚበልጥ ሕዝብ ወደ ተራራ ወጥቶ በመጸለይ ላይ ይገኛል። የእድገቱንም ሂደት በሰንጠረዥ መልክ ለማስቀመጥ አሞክራለሁ። ሰንጠረዡን በጥሞና ይመልከቱ።

ተ. ቁ	ዓመተ ምህረት	በየዓመቱ ይሰባሰብ የነበረዉ ሕዝብብዛትና እድገቱ	ምርመራ
1	1990	500	ቀደም ሲል ለ40 ዓመታት ያህል በግል/በቁንጽል ይደረግ የነበረዉ ጸሎት አድጎ በጋራ መሰባሰብ የጀመርነዉ በዚህን

			ዓመት ነበር
2	1991	5,000	
3	1992	10,000	
4	1993	20,000	
5	1994	25,000	
6	1995	30,000	
7	1996	35,000	
8	1997	45,000	
9	1998	50,000	
10	1999	60,000	
11	2000	70,000	
12	2001	80,000	
13	2002	90,000	
14	2003	100,000	
15	2004	200,000	በዚህ ዓመት ለመግመትም በጣም ያስቸግር ነበር፤ ግን ተሳታፊዉ በጋራ የገመተዉ ወደ 200,000 አንደሚደርስ ነበር
16	2005	150,000	በወቅቱ ሌላ ፕሮግራም ተደርቦ ነበር

በሁለተኛው ዓመት አሥር እጥፍ ማለትም ወደ 5,000 የሚያህሉ ሰዎች ተራራዉ ላይ ወጥተዉ ጸለዩ። ቁጥሩ በተጀመረ በ10 ዓመቱ ወደ 50,000 አደገ። ከአሥራ አራት ዓመታት በኋላ ማለትም በ2003 ዓ.ም ደግሞ በአጥፍ አድጎ 100,000 ሆነ። በዓመቱም ማለትም በ2004 ላይ አስከ 200,000 ያህል ሰው በአምባሮች ተራራ ላይ ወጥቶ ለአገሩችን ኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ለለለም ለመፀለይ ተሰብስቦ ነበር። ግምታችን መቶ ፐርሰንት ልክ ነዉ ባይባልም በየዓመቱ በግምት እንደወሰድነዉ ሪኮርድ ከላይ ከተመለከተዉ ሰንጠረዥ አጠቃላይ እንቅስቃሴዉን፣ አድገቱንና የጸሎት ጅማሬው እንዴት ወደ ንቅናቄነት እንደተለወጠ ለማየት እንችላለን።

ድሮ አባሰሬቾ አምላክ ነዉ፤ ዝናብ ሰጪ ነዉ፤ ፈጣሪያችን ነዉ ... በሚባልበት ዛሬ በተደጋጋሚ ኢየሱስ ጌታ ነዉ፣ ኢየሱስ ያድናል፣

ወንጌላችን ድል ያደርጋል አየተባለበት ይገኛል። ይህንን ሁሉ ላደረገ ለአምላካችን ለአግዚአብሔር አሁንም አሁንም ክብር ይሁንለት!

በአርግጥ ይህ ሁሉ ሲሆን ይህ ነው ተብለዉ የማይነገሩ ዉለጣዊና ዉጫዊ ተግዳሮቶች ተከሰተዋል። ይህም ብቻ ላይሆን በዚህ ተራራ ላይ ከተጀመረው የፀሎት አሳት የተነሳ በብዙ የአካባቢው ተራሮች ላይ ትላልቅ የፀሎት ንቅናቄዎች በአሁኑ ሰዓት ለመቀሰቀሰ ችለዋል። ምናልባት በአካባቢው ካሉት ተራሮች በትንሹ መቶዎቹ የጸሎት ተራሮች ሆነዋል ለማለት ይቻላል። ብዙዎችም ይህንን ራዕይ አየተቀበሉ በየአካባቢያቸዉ ባሉ ተራሮች ላይ የጸሎት አንቅሰቃሴ አየጀመሩ ናቸዉ። የዚህ መጽሐፍ አንባቢዎችም ራዕዩን በመቀበል አርሰዎም ከጓደኞችዎና ከቤተክርስቲያንዎ ጋር የተራራ ጸሎት አንቅሰቃሴ አንዲጀምሩ አመከራለሁ።

የኤ አይ ፕ ኤም (AIPM) የወንጌል ተልዕኮ ዉልደትና እድገቱ

አንቅሰቃሴው ወደ ተራራ ወጥቶ ፀልዮ በመውረድ ላይ ብቻ አልቀረም። በ1994 ዓ.ም ላይ አግዚአብሔር ከ15 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ 7 ለጋ ወጣቶች (ወንዶችና ሴቶች) ወደ ተራራዉ አናት ይወጣሉ። ለማቸዉም ድልየአብ ደሲታ፣ አመቤት ዮሐንስ፣ ተገኘ ሱማሞ፣ ተስፋነሽ ገነቶ፣ ሙሉነህ ጳዉሎስ፣ ለላማዊት አየለና ተገኘ ወርቅ ዮሐንስ የሚባሉ ነበሩ። በ1994ቱ የጸሎት ቀን የአምባርቾን ተራራ ወጥተዉ አንደተመለሱም በየወሩ አየተገናኙ መጸለይ ጀመሩ። በሚገናኙበት ጊዜ ሁሉ አንድ አንድ ብር ይሰበሰቡ ነበር። ከእነዚያ ልጆች አንዷ የመጀመሪያ ልጇ ድልየአብ ነበረችና አንድ ጥያቄ ጠየቅኋት። አየተሰበሰባቹሁ ገነዘብ አንደምትሰበሰቡ ለምቻለሁ። የሰበሰባችሁት ገንዘብ ለምን ጥቅም ይውላል አልኳት? አርሷም ለሰላሳ መጠጥና ዳቦ ገዝተን በመዉጣት ከተራረዉ ጸሎት በኋላ ለመጠቀም፣ ገንዘቡም ከተረፈልን ተራራዉ ደሰ ሰለሚል ከተራራዉ ጋር ፎቶግራፎችን ለመነሳት ነዉ ብላ መለሰችልኝ።

አኔም በድንገት ገንዘቡን ለመብልና ለመዝናናት ብቻ ከምታጠፉ ለምን ለወንጌል የተወሰነዉን ያህል ብር አትሰጡም አልኳት። አርሷም ከነዚህ ጓደኞችዋ ጋር ተማከራ ካሰባሰቡት ከ102 ብር 52ቱን ብር ሰጠችኝ። አኔም በሰዓቱ ይህንን ብር ምን ላደርግ ነዉ ብዬ በጣም ተጨነቅኩኝ። ወዲያዉ የጌታ መንፈሰ በዚህ ለዘመናት የጥንቆላ አርግማን አየተቀበረ ከኖረበት ከአምብርቾ ተራራ አናት ላይ ለዓለም ሁሉ በረከት የሚሆን

ወንጌል አንዲላከ አፈልጋለሁ። ለዚህም አንቅሰቃሴ አንተን በቀዳሚነት አፈልግሃለሁ ሲል ተናገረኝ። ነፍሴ በጣም ተጨነቀች። አምቢ ማለቱም አሺ ማለቱም ሁለቱም ጭንቅ ሆነብኝ። ታዲያ ከዚያ ሰዓት ጀምሮ አንቅልፍ ማጣት፣ የምግብ ፍላጎት አምቢ ማለት ተከሰተብኝ። ሆኖም ለባለቤቴና በወቅቱ በዚህ በተራራ ጸሎት በጣም ይንቀሳቀስ ለነበረ ተሰማ ዋለኖ ለሚባል ወንድም ራዕዩን አካፈልኩት። ባለቤቴና አኔ 100 ብር፣ ተሰማ ደግሞ የነበረዉን ኮት አዉልቆ በመሰጠት 50 ብር ተገምቶለት በመከፈል አኛም ልጆቹን ተቀላቀልን። ለጉባኤዉም ጌታ የተናገረኝን ራዕይ አካፈልኩና ሕዝቡ ራዕዩን አኛም ተቀብለናል በማለት በዕለቱ 739 ብር ተሰበሰበ። አነሆ የአምባርቾ ዓለም አቀፍ የጸሎትና የወንጌል ንቅናቄ የዛሬ 11 ዓመት ማለትም በ1995 ዓ.ም በዚህ መልክ ተወለደ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ የአጠቃላይ አንቅሰቃሴ ኃላፍነት ወደኔ ዞረና ልቤ በዚህ ንቅናቄ ላይ በቁርጠኝነት አተኮረ። ሽከሙም ከጊዜ ወደ ጊዜ አየጠነከረብኝ መጣ። በዕለቱ ከሚቴ አዋቀርን። አኔ ፣ ከብሩ ሾሞሮ፣ ዳዊት ሐደሮ፣ በላቸዉ በጅጎ፣ ተሰማ ዋለኖ፣ ረታ ወዕሜና ካላ ሆነን አንቅሰቃሴዉን ቀጠልን። ረታና ካሳ በርቀት ለለሚኖሩ በሀላብ አብረዉን ቢሆኑም በአካል በብዛት ለመገኘት አልቻሉም ነበር። ዳሩ ግን የቀረነው አምሰታችን አብረን አየጸለይንና አየተወያየን የኮሚቴዉን ሥራና አንቅሰቃሴ በማጠናከር ቀጠልንበት።

ለአንድ ዓመት የጸሎትና የዝግጅት ጊዜ ሆነና ባመቱ ደግሞ 6,700ብር ተሰበሰበ። ራዕዩ በመጣ በ2ኛው ዓመት ማለትም በመጋቢት 1 ቀን 1996 ዓ.ም ለንቡቴ ሻላ ወደ የምትባል ለወንጌል 100% ዝግ ወደ ነበረችው ከተማ የመጀመሪያውን የኤ አይ ፕ ኤም ሚሰዮናዊ አድርገን ታምሩ ላንገናን ላክን። አሰካሁን ያለዉ አጠቃላይ የሚሰዮናዉኑ ብዛትና አንቅሰቃሴ ምን አንደሚመስል የሚከተለዉን ለንጠረዥ ይመልከቱ

ተ.ቁ	ዓመተ ምህረት (ዓ.ም)	የተላኩሚሰዮናዉያን ብዛት	አጠቃላይ ሚሰዮናዉን ብዛት	ምርመራ
1	1996	1	1	
2	1997	2	3	
3	1998	1	4	
4	1999	3	7	
5	2000	15	22	

6	2001	17	39	
7	2002	18	57	
8	2003	45	101	
9	2004	50	151	
10	2005	42	193	
11	2006	60	253	
12	የቢሮ አስተባባሪዎች	12	265	

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ እንዳየነዉ ከሆነ አለከ ለባት ዓመታት አጠቃላይ የተላኩ ሚስዮናዉያን ብዛት ከ56 እንዳላለፉ አይተናል፡ ነገር ግን ካለፉት 3 ዓመታት ወዲህ ነዉ ከፍተኛ የሆነ የሚስዮናዉያን ንቅናቄ ለማየት የቻልነዉ፡፡ ስለዚህ በ1996 ዓ.ም አንድ ሚስናዮናዊ በመላክ የተጀመረው የወንጌላውያን ብዛት በሕዳር 2006 ዓ.ም 220 ደርሷል፡፡ ጌታ የተመሰገነ ይሁን፡፡ እነዚህንም በአጠቃላይ በአገሪቱ ወንጌል ባልደረሰባቸው አካባቢዎች በሙሉ ወንጌል ለመሥራት ፊላጎት ካላቸው አብያተክርስቲያናት ጋር በአጋርነት ልከናቸው ሄደው የወንጌል ተልዕኮን ሥራ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በላይ የአላላከ አካሄዱን በሚመለከት ደግሞ አስቲራቴጅካዊ በሆኑ አካባቢዎችና በታዎች፣ ወንጌል ባልደረሰባቸዉ ብሔረሰቦችና ሥፍራዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ጌታ በሚሰጠን አስትራቴጂ አማካኝነት እየላከን አንገኛለን፡፡

በመዝ 118:23 ላይ «...ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች ለዓይናችንም ድንቅ ናት» የሚለዉ ቃል በዚህ አገልግሎት አዉነት ሆኗል፡፡ ስንጀምር የአገልግሎቱን ስም «የአምባርቾ ዓለም አቀፍ የጸሎትና የወንጌል አገልግሎት» ብለን ጀመርን፡፡ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ «አጋፔ ዓለም አቀፍ የጸሎትና የወንጌል አገልግሎት የሚል ስያሜ አግኝቶ በሕጋዊነት ተመዝግቦ አየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ለወደፊቱም ደግሞ አግዚአብሔር በአገር አቀፍ ብቻ ላይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በዚህ አገልግሎት አማካይነት ታላላቅ የሆኑ በጎ ተጽእኖዎችን ያመጣልናል ብለን እናምናለን፡፡

10. በቀጄሌ ቤተ ክርስቲያን የተከሰተዉ የፀሎት ንቅናቄ

በ1976 ዓ.ም በህዳር ወር በሮቤ ቲ.ቲ አይ ማስተማር ከጀመርኩ በኋላ ወላጆቼንና ቤተዘመዶቼን ለመጠየቅ ወደ ተወለድኩበት አካባቢ በየዓመቱ ስመላለስ አንድ ነገር ተገነዘብኩ፡፡ ያደግኩባት የቀጄሌ

ቃ/ሕ/ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ መንፈሳዊ ጉስቁልናና ጨለማ ተውጣ አየሁ፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ ጭቅጭቅና መከፋፈል ሰፍኖ ነበር፡፡ በእሁድ እምልኮ ሰው በተኮሳተረ ፊት ገብቶ መውጣት፣ ሕይወት አልባ ስብከትና ዝማሬ ለሥርዓቱ ብቻ ተደርጐ ሕዝቡን ማስናበት የተለመደ ነገር ሆኖ ነበር፡፡ ይህን ባየሁ ሠዓት ሁሉ ያሳደገችኝ ቤ/ክ በሕይወት እያለች ሞታ ማየቴ ልቤን ከመጠን በላይ ለበረው፡፡ በወቅቱ የሶሻሊዝም ተጽእኖም ስለነበረ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ቤተ ክርስትያናት ባይዘጉም ጠንካራ እማኞች አየተነዱ ይታሠሩ ነበር፡፡ ክርስቲያኑ አሰራትን ስለሚፈራ መንፈሳዊነቱን ለሥርዓቱ ብቻ ይዞ መኖር ይፈልግ ስለነበር ቤተክርስትያን በያለችበት በሕይወት እያለች ሞታ ነበር፡፡ የቀጄሌም ቤተክርስቲያን የነበረችዉ በገበሬ ማህበረሰብ ውስጥ ስለነበረ አብዛኛው ገበሬ በመሬቱ ትምባሆ፣ ጫትና ጌሾ ተከሎ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚህ ሽያጭ ይገኝ የነበረ ገቢ ብዙ ነበርና፡፡ ደግሞ ክርስቲያን ሆነዉ የሚያጨሱና አልኮል የሚጠጡ ቁጥራቸዉ ብዙ ነበሩ፡፡ ከዚያ የተነሳ መንፈሳዊና ህብረተሰባዊ ጉስቁልናም ገደብ የለሽ ነበር፡፡

በ1976 ዓ.ም በከረምት ቤተሰብን ለመጠየቅ በሄድኩበት አጋጣሚ ከዚህች ቤተ ክርስቲያን የጌታ መንፈስ ወደ ልቤ ያመጣቸዉን 4 ወጣቶችን መለመልኩና በየእሮቡ በፆምና ጸሎት አንዲተጉ ቃል አስገባኋቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ጩፋሞ ገአኖሮ፣ ታምሩ ላንገና፣ አየለ ኤርሱሞና ታደሰ ኦርጂኖ የሚባሉ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ አንዱ ጩፋሞ ገአኖሮ የሚባለው ወደ ጌታ ሄዷል፡፡ አየለ ኤርሱሞ የሚባለው በመንግሥት ሥራ ተሰማርቶ በእሁን ሰዓት አላባ በምትባል ልዩ ወረዳ ዉስጥ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ ሁለቱ ታምሩ ላንገናና ታደሠ ኦርጂኖ የሚባሉ ደግሞ በዚያን ወቅት ለሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ተለይተው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ታደሰ በእጥቢያዉ፣ ታምሩ ደግሞ በሚስዮናዊነት ያገልግላሉ፡፡

እነዚህ አራቱ ወጣቶች መጸለይ እንደ ጀመሩ ተሰማ ለተሞ፣ አዲሴ ኦርጋዶና አህት አበራሽ አሼቦ የሚባሉ በፀሎት ቡድኑ ላይ ተጨመሩና ቁጥራቸዉ ወደ ሰባት አደገ፡፡ የእግዚአብሔር ሙሉ ቁጥር ሆነ ማለት ነዉ፡፡ እነዚህ ወገኖች መጸለይ አንደጀመሩ ብዙ ሰልፍ ተነሳባቸው፡፡ ሰልፉ ከውስጥና ከውጪ ነበር፡፡ ያልተለመደ የጸሎት እንቅስቃሴ ስነበር ውጊያውን ከከፈቱት የመጀመሪያዎቹ የቤ/ክ መሪዎች ነበሩ፡፡ ሆኖም ግን ለእነዚህ ወጣቶች እግዚአብሔር ታላቅ ጽናትንን ጥበብን ሰጣቸው፡፡ ምክንያቱም ያልተለመደ እንቅስቃሴ ነበርና፡፡ መሪዎች ከከፉ ዓላማ

በመነሳት ሳይሆን ያልተለመደ ልምምድ መጥቶ ቤተክርስትያንን እንዳይጎዳ በማለት ነበር። በተቀበሉት አደራና በተገለጠላቸዉ አዉነት እየበረቱ ሄዱ። በፀለዩ ልክ እግዚአብሔር ከጊዜ ወደ ጊዜ የፀሎትን ፍቅር እየጨመረላቸው ሄደ። በቤተክርስቲያኑ ግልጽ የሆነ ለውጥ ቶሎ ባይታይም እንኳ የእነርሱ ሕይወትና አገልግሎት ግን በእጅጉ እየተለወጠ ሄደ። በተለያዩ ጊዚያት የተለያዩ የወንጌል እንቅጋዮች እየመጡ ስለ ፀሎት አስፈላጊነት በቤተክርስቲያኑ ይሰብኩም ያስተምሩም ነበር። ከእነዚህም አንደ ምሳሌነት የሚጠቀስ ወ/ዊ ክፍሌ ወ/ሀና የሚባል ክእዲስ እበባ ኮልፌ እየመጣ በከምባታ ዉስጥ ባሉ ቤተክርስቲያናት በወቅቱ (በ1980ዎቹ መጀመሪያ እካባቢ) እየዞረ የሚያገለግል ወንጌላዊ ነበር። እኔም ደግሞ በተለያዩ ጊዚያት ከባሌ እየተመላለስኩ በቤተ ክርስቲያኑ ስለ ጸሎት በተደጋጋሚ ማስተማሬና መስበኬ ትዝ ይለኛል። ከዚያ የተነሳ በዚያች በቀጀሌ ቤ/ክ/ በቋሚነት የሚፀልይ ቡድን እባላት ብዛት በየጊዜ እየጨመረ ሄዶ በዘጠኝ ዓመታት ውስጥ የቡድኑ የጸሎት እባላት ቁጥር ወደ 90 ደርሶ ነበር።

ፀሎቱ ከተጀመረ ልክ በ10ኛው ዓመት በ1986 ጳጉሜ ላይ የጸሎት ቡድኑ ኮንፍራንስ እዘጋጀና የኮንፍራንሱ ስባኪዎች ወንድም ምህረቱ ተስፋዬና እኔ ሆንን። ሁለታችንም በዱራሜ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እስተማሪዎች ስለነበርን በተለይ በ1985 እስከ 1987 ዓ.ም ባስዉ ጊዜ ሁለታችንም በእካባቢዉ እግዚአብሔር ሪቫይቫል እንዲያመጣ አብረን እንጸልይም እየዞርን እንሰብከም ነበር። እንዲሁም ብዙ ቦታ ላይ እየተጋበዝን በኮንፍራንሶች ላይ አብረን አገልግለናል። እርሱ በ1986 ጳጉሜ ወር የቀጀሌ ኮንፍራንስ ላይ ሁለት ቀናት (ሐሙስና ዓርብ) አገልግሎ ለሌላ ፕሮግራም ወደ ሻሸመኔ ሲመለስ የቀሩትን ሁለቱን (ቅዳሜንና የእሁድ) ቀናት ሙሉ በሙሉ ስባኪ እኔ ነበርኩ። ነገር ግን ሰኞ የጀመረው የፆም ጸሎቱ ፕሮግራም ያለቀዉ ሐሙስ ዕለት በ10 ሰዓት ላይ ነበር። በሐሙስ ዕለት መጨረሻ ላይ በጸሎት የሰነበተዉ ሕዝብ የማታ ኮንፍራንሱ ከመጀመሩ እስቀድሞ ቡናና ሻይ ካለ በኋላ እንዲት እናት እንዲጸልዩ ይጋበዛሉ። ሴተየዋም እየጸሰዩ እያለ የ10 ዓመት ፀሎት መልስ በዚያን ሰዓት ላይ በድንገት መጣ። በቅጽበት ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። በጸሎቱ ለዓት የመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ እኚህ አናት ሲሆኑ፤ ልክ እላቸዉ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ 6 ወጣቶች ደግሞ በዚያዉ ሰዓት ተሞሉ። ማታ በኮንፍራንሱ ስዓት እገር ቀዉጢ ሆነ። በቤተክርስቲያኒቱ በ32 ዓመታት ታሪክ ዉስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንድ ወጣት በመገለጥ መልዕክት ሲያመጣ ነገሩ በጣም ግልጽና

እዉነተኛ ነበር። የበለጠ ሕዝቡ እንደገና ጌታን በማመስገን በምሰጋናና በአምልኮ መንፈስ ተሞላ። በእብዛኛው የቤተክርስቲያን ምዕመን ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን ተቀበለ።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለመቀበል የመጀመሪያዎቹ አሥሩንም ዓመት በየላምንቱ ሳያቋርጡ ይፀልዩ የነበሩ መሆናቸዉ እጅግ ያስደነቀን ጉዳይ ነበር። ከእነዚህ እብዛኛዎቹ ትምህርት ምንም ያልቀመሱና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላትና ስስዶከተሪኑ እምብዛም የማያውቁ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ። እኔ እድገቴም ልምምዴም በጣም ወግ እጥባቂ ከነበረች ከቃ/ሕ/ቤ/ከ ስለነበር በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በሙላትም ማገልገል በጣም ደስ ቢለኝም እንቅስቃሴውን በጥንቃቄ እከታተል ነበር። ነገር ግን በዚያን ጊዜ እየስበኩ እያለሁ ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ስላየሁ፤ የማየዉ ነገር ለራሴ ግራ ይገባኝ ነበር። ነገሩ ግራ ቢገባኝም ፍጹም ከእግዚአብሔር እንደነበር ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ግልጽ ነበር።

በዚያ ላምንት መጨረሻ ማለትም ጳጉሜ 5/1986 ዓ.ም ላይ ከቤተ ክርስቲያኒቱ እብዛኞቹ ሠዎች ወደ እስገራሚ መንፈሳዊ ተሃድሶና መነቃቃት ውስጥ ገቡ። እግዚአብሔር ይባርካቸውና በወቅቱ የነበሩ መሪዎች እየተከሰተ ያለው ነገር ግራ ቢገባቸውም ያላደጉኝ ስለሆኑና ለረዥም ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል ላስተምር ያዉቁኝ ስለነበረ ደስታ ቤተ ክርስቲያንን አፍራሽ ሥራ እይሰራም የሚል እምነት ነበራቸውና ጉዳዩን በእግዚአብሔርና በእኔ ላይ ጥለው ዝም አሉ። እኔም ከዚያ በኋላ የፀጋ ሥጦታ አጠቃቀምን በሚመለከት ከነኛ ቆሮ 14 በሰፈው ትምህርት እስተማርኩኝ። ሁሉም አዲስ ባገኘው ልምምድ የተነሳ ሥርዓተ አልበኝነት ለማሳየት ቢቃጣውም ለቃሉ ተገዢ በመሆኑ እንዳች የሀሰት ትምህርት ተከታይና እስተማሪ ከዚህች ቤተክርስቲያን እስከ ዛሬ ድረስ እልተነሳም። ከብር ሁሉ ለጌታ ይሁን። የቀጀሌ ቤ/ክ ፀሎትና በረከቶችና በማህበረሰቡ ላይ ያመጡአቸዉን በጐ ተጽእኖዎች እንዲሁም ደግሞ ከዚህ ፀሎት የተነሳ በመጣው ሪቫይቫል የተከሰቱትን ከስተቶች መንፈሳዊና ማህበረሰባዊ በረከቶች እጅግ ብዙ ናቸው። ቢሆኑም ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥሎ ለማየት እንሞክራለን።

አጠቃላይ የቤተክርስቲያን ምዕመን ፀሎት ወዳጅ መሆን

የመጣው የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል ሁሉንም የቤተክርስቲያን ምዕመናን በበጐ ጐኑ እነሳለ። ጸሎትን በሚመለከት ለመጸለይ ቀርቶ ለመስማትም

እንኳ የማይወዱ ለዎች ወደ ጸሎት ቦታ መሮጥ ጀመሩ። የእያንዳንዱ እማኝ ቤት የፀሎት ቤት ሆኖ እስከሚቀየር ድረስ ታላቅ የፀሎት ንቅናቄ አጥቢያይቱ በነበረችበት ቀበሌና መንደር ሳይ ተቀጣጠለ። መነቃቃቱም ቀጣይነት እንዲኖረው ሲባል ሪቫይቫሉ ከፈነዳ በኋላ በሳምንት ሁለት ቀናትን ማለትም ማክሰኞና ሐሙስ ማለዳ 10:00 ሰዓት ፈቃደኛ የሆኑ ሠዎች ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን መጥተው መጸሰይ እንዲችሉ ጌታ አሳሰበኝ። የሠዎቹን ፈቃደኝነት ስጠይቅ አብዛኛዉ ሕዝብ ተስማማ። ክሦስት መቶ ሰዉ በላይ በመጀመሪያዉ እለት መምጣቱን አስታዉሳለሁ። ደግሞም ሕዝቡ ከእቡለ ሌሊት በኋላ በ7:00 ሠዓትና በ8:00 ሠዓት ላይ አየመጣ ቤተክርስቲያን ሞልቶ መጸሰይ ጀመረ። ታዲያ ከሌሊቱ በ7:00 ሠዓት መጥቶ የተንበረከከ ሕዝብ ምንም ሳይደክመዉ መንበርከኪያ በሌሰዉ ወለል ላይ እስከ 12:00 ድረስ እየፀለየ ቆይቶ ወደ ቤቱ ይመለስ ነበር። ደግሞም ቤተክርስቲያኒቱ የገጠር ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ መጠን ሕዝቡ በእንስት በቡና ውስጥ_እንዲሁም በእህልና በጫካ ውስጥ እየገባ መጸለይ የተለመደ ተግባሩ ሆነ።

ይህም ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ቀን ቤተ ክርስቲያን በፆምና በፀሎት እየፀለዩ በሚውሉ ወጣቶችና አዛውንቶች የተጣበበች ሆነች። በእያንዳንዱ ቀን የሚጸልይ ቡድን ተደራጅቶ ለእያንዳንዱ ቡድን ደግሞ ታላፊነትን የሚቀበሉ 3 መሪዎች ተመደቡለት።

ከዚህ የተነሳ የፀሎቱ ሪቫይቫል ላለፉት 20 ዓመታት እስከ ዛሬ (1986-2006 ዓ.ም) ድረስ እንደቀጠለ ይገኛል። በእነዚህ ዓመታት ታዲያ ውጣ ውረድ የለም ማለት አይደለም። የጸሎት ቡድኖች መሪዎች የነበሩና ሌሎች በጸሎቱ ይሳተፉ የነበሩ በሥራ፣ በትዳር፣ በትምህርትና በሌሎች ምክንያቶች ቦታ በመቀየራቸው እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ሙቀት በነበረበት ዘመን የተነኩ ሰዎች ያ ሙቀት በእንዳንዶቹ ላይ እንደነበረ አልቀጠለም። እንዲሁም ቤተክርስቲያኒቱ በብዙ እዲስ ትውልድ መተከቷና ብዙዎች በእገልግሎት ምክንያት ተንቀሳቃሽ በመሆናቸው (እንደኔ ዓይነቶቹ) ነባሩ ሁኔታ እንደነበረ አለ ባይባልም ዛሬ ቁጥሩ እነስተኛ ያይደለ ህዝብ በየዕለቱ ይጸልያል። ምክያቱም ቤተክርስቲያቱ የሚጸልይ ቡድን እላትና። በቅዳሜና አሁድ የፀሎት ቡድኖች አይኖሩም። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን በተለያዩ ፕሮግራሞች በእነዚህ ሁለት ቀናት ውስጥ ስለምትያዝ ነዉ።

ብዙ ነፍሳት መዳንና ሁለንተናዊ ለውጥ

በቀበሌዉ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚያጨሱና ጫት የሚተክሉ እንዲሁም አልኮል የሚጠጡ ብዙዎች እንደነበሩ ከላይ ለመጥቀስ ሞክሪያለሁ። ይህም ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያኒቱ ባላመኑ ለዎች የተከበበች ነበረች። ነገር ግን ጸሎቱ ካመጣው ሪቫይቫል በኋላ 100% ምድሪቱ ከጫት ተከል ነፃ ወጥታ ነበር ማለት ይቻላል። ጫት እየተከሉ በየዓመቱ በእስር ሺሆች የሚቆጠር ብር ያገኙ የነበሩ ሁሉ ወይ ራሳቸው እየነቀሉ አሊያም የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን፣ ወጣቶችን፣ ኳየርንና የፀሎትን ቡድኖች እየጠሩ ያስነቅሉ ነበር። ከቤተ ክርስቲያኒቱ ከልል ከጫት ገቢ የሚያገኝ በሙሉ ኢየሱስ የገቢዬ ምንጭ ነው ብሎ እጁን፣ ኪሱንና ልቡን ለጌታ ሰጠ። ያም ብቻ ሳይሆን ያላመኑ ሰዎች በእንዴ ብቻ 250 የሚሆኑቱ ጌታን ተቀብለው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቷ በአባልነት ተጨመሩ። በዚህች ቤተክርስቲያን ከዚያ ቀደም በየዓመቱ ከ10 ወይም ከ20 ሰው በላይ ጥምቀት ወስዶ አያዉቅም ነበር። ያን ዓመት ግን 158 ሰዎች በአንድ ጊዜ ጥምቀትን ተቀበሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ህንፃ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ሶስት ጊዜ ፈርሶ እንዲሰፋ ተደርጓል። ለ40 ዓመታት ኖራ ከ500 በላይ አባላት ያልነበራት ቤተክርስቲያን ዛሬ ከ2,000 በላይ አባላት አሏት። ክብር ለኢየሱስ ይሁን!!

አንዲሁም ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ቤተክርስትያኒቱ የሥነ ምግባር ችግር የሚታይባቸዉን አባላት፡- ለምሳሌ ጫትና ትምባሆ በመትከል ገንዘብ ለማግኘት የሚፈልጉትንና ተመላላይ ድርጊቶችን በማድረግ ተመከረዉ የማይመለሱትን ከቤተ ክርስቲያን አባልነት እንደምትሰርዝ ድንጋጌ እወጣች፤ እቋምም ወሰደች። ከዚህም ጥብቅ እቋም የተነሳ ብዙዎች ራሳቸዉ ገብቷቸዉ፤ ለሎቹም ተመከረዉ በንስሃ ተመለሱ። እምቢ ያሉትም ከአባልነት በመሰረዛቸዉ ቆይተዉ በንስሃ የተመለሱ አሉ።

የአገልጋዮች መብዛት

ከቤተ ክርስትያኒቱ ሪቫይቫሉ ከመጣ በኋላ ሰው ሁሉ በመንፈሳዊነት የበሰሰና ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የእግዚአብሔርን ቃል ወዳድ ሆነ። ትንንሽ ሕፃናት ተነስተው የሚለብኩት ለብክት፣ የሚያዩት ራዕይ፣ ይናገሩ የነበረው የትንቢት መልእክት በእፍ ላይ እጅ የሚያስጭን ሆነ። ወዲያው ባልተጠበቀ ሁኔታ ከዚህች ቤተክርስትያን እግዚአብሔር ታላላቅ ሰባኪዎች እንዲወጡ አደረገ። እንዲሁ ታላላቅ ሚስዮናውያን ጭምር። በአሁን ሠዓት ከዚህች የገጠር ቤተክርስቲያን ከእኔው ጋር 9

ሚሰዮናውያን ቤተሰቦች ወጥተው በሚሰዮናዊነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአጥቢያይቱ ደግሞ ከ10 የሚበልጡ ሙሉ ጊዜ እገልጋዮች እሏት፡፡ ይህ ሁሉ ጸሎትና በጸሎቱ ምክንያት እግዚአብሔር ያመጣዉ መንፈሳዊ ተሃድሶና ለዉጥ ነዉ፡፡

በምዕመናንና ሕይወትና በእካባቢው የተከሰቱ ድንቃድንቅ ከለተቶች

- በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ መነቃቃቱ ሳይመጣ በፊት በዲግሪ የተመረቀ ሰው ከሁለት አለከ አምስት የማይበልጥ ነበር፡፡ ይህ ፀሎት ከተጀመረ በኋላ ግን ቢሚያሰገርም ሁኔታ የብዙ ወጣቶች አእምሮ ተከፈተ፡፡ ከተለያየ ቤተሰብ ውሰጥ የማትሪክ ፈተናና የዩንቨርስቲ የመግቢያ ፈተና አያለፉ ብዙዎች ወደ ዩንቨርስቲና ኮሌጅ መግባት ቻሉ፡፡ መነቃቃቱ ከመምጣቱ በፊት ደመወዝ ያላቸው ሰዎች ብዛት ከ7 ለው አይበልጥም ነበር፡፡ በአሁን ሠዓት ግን ከ100 በላይ ደርሷል፡፡ አሰገራሚው ነገር በአሁን ለዓት ከጥቂቶች በቀር በአያንዳንዱ ቤተሰብ ውሰጥ በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ያልገባ ወይም ሥራ የሌለው ወጣት የለም ለማለት ይቻላል፡፡ በጸሎት ምክንያት የሚመጣ የአግዚአብሔር መንፈስ አአምሮን የመከፈት ኃይሉ ምን ያህል አንደሆነ በግልጽ ለማየት ችለናል፡፡

- ቤተክርስቲያኒቱ ያለችው በገበሬ ህብረተሰብ መካከል በመሆኑ በእያንዳንዱ ቤት ያለው ከብት የሚሰጥ ወተት በብዙ ጨመረ፡፡ የአበሻ ከብት በዲቃላ ከብት ተተካ፡፡ ገበሬው ያለው መሬት በጣም ትንሽ ቢሆንም ሕዝቡ የሚያገኘው ምርት እየጨመረ ሲሄድ ታይቷል፡፡

- ከዚህ ቀደም ለዎች በተለያየ አቅጣጫ እንዱ ከሌላው ይሰርቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመነቃቃቱ የተነሳ በሌብነት ልምምድ ያሉ አንዳንዶቹ በድንተኛ በሽታ ላይ በመውደቃቸው የሞት መቅሰፍት ሳይመጣባቸው በፍጥነት ኃጢአታቸውን በአደባባይ ይናዘዙ ጀመር፡፡ ያንን ይለሙ የነበሩ ሌሎቹ የቀሩት ሌቦች ደግሞ ቁጭ ብለው ሲሰሙ ከነዚህ ያመለጠ መቅሰፍት በእኛ ላይ እንዳይመጣብን በማለት ንሰሃ እየገቡ ወደ ጌታ ይመለሱ ነበር፡፡ ደግሞም ከዚህ ቀደም ብዙ ዓይነት ምድሪቱን ያሰቸግሩ የነበሩ፣ ቤት ለርሳሪዎች፣ ከማላ ላይ አህል የሚለርቁና ወደ ሰው ቤት ገብተው

የሌላውን ንብረት የሚወለዱ አንዲሁም ጫካ ውሰጥ ተደብቀው መንገደኛውን የሚዘርፉ ሁሉ በንሰሃ ወደ ጌታ ተመልሰዉ የቤተክርሰያን አባላትና እገልጋዮች ሆነዉ ተለዉጠዋል፡፡ ከሁሉም በላይ በቤተክርሰቲያን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ ሁሉ የአግዚአብሔር ሉአላዊነት እየተገለጠ ፈሪሃ አግዚአብሔር በሰው ሁሉ ላይ ወረደ፡፡ ከዚህ የተነሳ ሌባ ከነአካቴው ጠፍቶ በአሁን ሠዓት ምድሪቱ አፎይ ብላለች፡፡

- ሌላው ደግሞ እካባቢው በተንኮለኛ የጅብ መንጋ የተሞላ ነበር፡፡ ነገር ግን ሕዝቡ ትንንሽ ልጆች ሳይቀር ከሌሊቱ 7 ሰዓት ጀምሮ ለጸሎት ፕሮግራም ሲመላለሰ ባለፉት 20 ዓመታት ውሰጥ አንድ ቀን ሰንኳ አንድም ሰው ጅብ ተተናኩሎት አያውቅም፡፡ የእግዚአብሔር መለከታዊ በጎ ተጽዕኖ ከጸሎት የተነሳ ሰውን፣ አንሰሳን፣ እውሬንና ግዑዟን መሬት ሳይቀር እንደለወጠ የአይን ምሰክሮች ነን፡፡ ሰለዚህ ፀሎት ሲኖር እውሬ ለማዳ ይሆናል፤ ፀሎት ሲቀር ግን ለማዳው አውሬ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

- ቤተክርሰትያኒቱ ላለችበት ሕብረተሰብ የሚያሰፈልጉ ግልጋሎቶች እንዲገቡ ለዚያ ብቻ የሚጸልይ የተለየ የጸሎት ቡድን ተቋቁሞ ነበር፡፡ ታዲያከዘያ ጸሎት የተነሳ የዉኃ ቧምቧ መዘርጋት፤ የኤልከተሪክ መዘርጋት፤ ዘመናዊ ትምህርት ቤት መሰራት፣ የመሳለሉ ሁሉ ባልተጠበቀ ጊዜና ሁኔታ ለሕብረተሰቡ እገልግሎት አንዲሉጡ ተደርገዋል፡፡

ii. በሰንበቴ ሻላ ቤተክርሰቲያን ፀሎት ያለከተለዉ አለገራሚ ተአምራት

ሚሽነሪ ታምሩ ላናገና በቀጀሌ ቃለሕይወት ቤተክርሰቲያን ለተነሳዉ መንፈሳዊ መነቃቃት ግምባር ቀደም ከነበሩት ወንድሞች መካከል እንዱ መሆኑን ከላይ ጠቅሻለሁ፡፡ ታድያ አርሱ ባደገበት አጥቢያ ወንጌላዊ ሆኖ ሲያገለግል በልቡ ውሰጥ ይቀጣጠል የነበረውና ጌታ በልቡ ዉሰጥ ያሰቀመጠዉ

ትልቅ ሸክም የወንጌል ተልዕኮና የወንጌል ሥርጭት ነበር፡፡ አርሱም ለዚህ ጉዳይ ሁልጊዜ በዚህ አቅጣጫ ይፀልይ እንደነበር ከአርሱ ጋር አብረዉ ይጸልዩ የነበሩ ጓደኞቹ መስከረዉልኛል፡፡ አርሱም ነግሮኛል፡፡ ለለሆነም

በ1996 ዓ.ም የመጀመሪያው የአምባርቾ ዓለም አቀፍ የጸሎትና የወንጌል አገልግሎት (AIPM) ሚሰዮናዊ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ወንጌልን ለማድረስ የመጨረሻ እስቸጋሪ ከሚባሉ ሥፍራዎች ምናልባት ግምባር ቀደም ናት ወደምትባል ወደ ሰንበቴ ሻላ ተላከ።

ሲሄድም እጅግ ታላቅ ዋጋ የሚያሰከፍለው ተግዳሮት እንደሚያጋጥመዉ ጌታ በራዕይ ተናግሮት ነበር። በዚያ ከተማ ውስጥ ያሉ ሰዎችን እውሬ እየበላና እየፈጀ መሆኑን፣ የዚህን ከተማ ሕዝብ እግዚአብሔር በወንጌል የሚደርሰዉን ሰው እየፈለገ መሆኑን እንደገና በራዕይ አሳየው። ያንንም ራዕይ ካየ በኋላ ብዙዎች ወደዚያች ከተማ ከሄድክ ወዲያው ይገድሉሃል እያሉ እንዳይሄድ ቢለምኑትም ለመሄድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ማረጋገጫና ምሪት ሰላገኘ ወደ ሰንበቴ ሻላ ሚያዝያ 3 ቀን 1996 ዓ.ም ገባ። እንደገባም የነበሩትን ጥቂት ወገኖቹን ይዞ እንዲሁም ከርሱ በኋላ ወደዚያ ሚሰዮናዉያን ሆነዉ ያገለግሉ ዘንድ የተላኩ ከበደና ጌታቸዉ የቀንና የሌሊት ሥራቸዉ መጸለይ ሆነ። የደረሰው የመከራ እይነት ቁጥር የሌለዉ ቢሆንም እልህ አስጨራሽ ጸሎታቸዉ የተነሳ ጌታ የሰራቸዉ አሰገራሚ ታማራቶች ብዙ ናቸዉ። ነገር ግን በዚያች ምድር ጌታ የሰራቸዉን ታላላቅ ተአምራቶች ታምሩና ሁለቱም ጓደኞቹ እንዲሁም የሰንበቴ ሻላ ቤተ ከርሰቲያን ምዕመናን የመሰከሩልኝን ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ገጾች ለማስቀመጥ አወዳለሁ፦

- ወደዚያ ከገባ በኋላ አንደ እርሱ በፀሎት የሚተጉ ራሳቸውን ለወንጌልና ለአግዚአብሔር ፈጽመው የሰጡ ሁለት ሚሰዮናውያን ከበደ ሄልሰቦና ጌታቸው ማቴዎስ ከታምሩ ጋር አብረውት እንዲያገለግሉ ኤ.አይ.ፒ.ኤም (AIPM) መደባቸው። ከዕለታት አንድ ቀን ተከራይተው የነበሩበትን ቤት ከሌሊቱ 8፡00 ሠዓት ላይ የወንጌል ተቃዋሚዎች አራት ሊትር ቤንዚን እርከፍከፈው አሳት ለቀቁበት። ነገር ግን ሌሊቱን ጫት እየቃሙ ያረፈዱ የሰንበቴ ሻላ ነዋሪ ሰዎች በጣሪያው ላይ አየነደደ የሚወርደውን አሳት አዩና ተደናግጠው በመሄድ አሳቱን አጠፉ።
- ሌላ ጊዜ ደግሞ የነበሩበትን ቤተከርሰቲያን ሚሰዮናውያንና ምዕመናኑን ለመግደል ተዘጋጅተው የመጡ ሰዎች በድንገት ያልታወቀ የመብራት ባውዛ አመንጭዳቸው ላይ በርቶባቸው በመለኮታዊ አሳዳጅ እየተሰደዱ ነፍሳቸውን ለማዳነን በሸሽት እካባቢውን ለቅቀው ጠፉ።

- በሌላውም ቀን ደግሞ በቤ ከርሰቲያኑ ላይ ቦንብ ሊያፈነዱ ያሰቡ ሠዎች ቦምብ ወደ ጣሪያ ላይ ወርውረው ቦምቡ ተንከባልሎ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ በመፈንዳቱ ቤተከርሰቲያኒቱም፣ በውሰጡ የነበሩ ሚሰዮናውያኑና አማኞቹም ለዕለቱ ጠላት ካቀናጀው አደጋ አግዚአብሔር ታድጓቸዋል።
- እንድ ቀን ደግሞ ሚሰዮናውያኑን ለመግደል ወደ ቤተከርሰቲያኑ መሣሪያ ታጥቀው ገዳዮች በገቡ ዕለት ሚሰዮናውያኑ አካባቢውን ለቅቀው በመውጣታቸው እግዚአብሔር በዚያ መልከ ታደጋቸው።
- በሌላው ቀን ደግሞ ገዳዮች ተገዝተው መጥተው ከርሰቲያኖችና ሚሰዮናውያን በነበሩበትና ገና ተሠርቶ ባላለቀው ቤት ላይ የጥይት እሩምታ ለቀቁባቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ግድግዳውን ጥሶ የሚገባውን ጥይት በሙሉ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲዞር ስላደረገ በዕለቱ በቤተከርሰቲያን ዉስጥ ከነበሩ መካከል አንድም ሰው እንዳይቆሰል እድርጎ እግዚአብሔር ታድጓቸዋል።
- ሌላው እሰገራሚ ነገር ደግሞ በዚያ ከተማ የሰይጣን ትልቁ ጥረት ቤተከርሰቲያን መሥራት ቀርቶ ከርሰቲያን እንዳይኖር ነበረ። ነገር ግን ከእማኞቹ መካከል ጌታቸዉ ጌንላና ቤተሰቡ 35x50 ሜትር የሆነ መሬት ለቤተከርሰቲያን ሰጠና ከዱራሜ (ከAIPM) ዋና ቢሮ እንጨት፣ ምስማርና ቆርቆሮ በአንድ ሌሊት በማሰገባት ቤተ ከርሰቲያኑ በ14 ሠዓታት ዕድሜ ብቻ ተሠርቶ እለቀ። ያ ለጠላት ትልቅ ንዴትን በመፍጠሩ ከላይ የተከሰቱ ታላላቅ ተግዳሮቶች እንዲከሰቱ ጠላት ግፊት ያደርግ ጀመረ። ሆኖም ግን እያንዳንዱ ተግዳሮት በእግዚአብሔር መለኮታዊ ተአምራት ሊከሸፍ ችሏል።
- ለቤተከርሰቲያን መሥሪያ መሬቱን በነፃ የሰጡት ጌታቸውና ቤተሰቡ መሬትን ለቤተ ከርሰቲያን በመሰጠታቸው የደረሰባቸው የመከራ ዓይነት እጅግ ብዙ ቢሆንም ግን ጌታ የሠራው ተአምራት ደግሞ እጅግ እሰገራሚ ነበር። ለዚህ ቤተሰብ ጌታ ከሠራቸው ታላላቅ ድንቆች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦ በሰድሰት ጥማድ መሬታቸው የዘሩት ቦቆሎ ምናልባትም መቶ የሚያህሉ ሰዎች በእንድ ሌሊት ገብተው ሰብብረው ወሰዱ፤ የጌታቸው ባለቤት ወ/ሮ ወርቁ በቃርሚያው ላይ "ሃሌሉያ የእኛ ቦቆሎ ቢወሰድም ለዘለዓለም የማይወሰድ ሀብታችን የሆነው ኢየሱስ ከእኛ ጋር አለ እያለች ትዘምር ነበር።" ለማንኛውም ብለው ዘራፊዎች ሲወሰዱ የቀረውን ቃርሚያ ለቅመው ሲወቁ አርባ ኩንታል ሆነላቸው። ይህ ለእገሩ

ሕዝብ በሙሉ ጉድ የሚያሰኝ ትንግርትና ተአምራት ሆነ። ለማስረጃም ኩንታሎቹን እኔ ራሴ በዓይኔ አይቻለሁ።

- ቀጥሎ ባለው ዓመት ገና ለጋ የነበረውን የጌታቸውን ቦቆሎ ቆርጠውና ረጋግጠው ሄዱ። ነገር ግን እግዚአብሔር አስገራሚ ነገር አደረገ። ተረግጦ የነበረው ቦቆሎ በተጋደመበት ፍሬ አፈራ በሁለተኛውም ዓመት እንዲሁ አርባ ኩንታል መገኘቱ ሁለተኛ ጉድ የሚያሰብል ጉዳይ ሆነ።
- ቀጥሎ ደግሞ በማላ ንብረት አልቻልነውም ብለው ያለውን ከብት ሦስት የወተት አዲስ የወለዱ ላሞችንና (ከጥጆቻቸው ነጥለው) 3 በሬዎችን ዘርፈውባቸው ከከልል ውጪ አወጡ። በአገሩ ታሪክ ከብት ከጠፋ ወይም ከተዘረፈ ፈጽሞ ተመልሶ አይታወቅም። ነገር ግን የጌታቸውና የቤተሰቡ ከብት ከጠፋ ከ7 ቀናት በኋላ 6ቱም ወደ ቤት ሲመለስ ያመነውም ያላመነውም ሕዝብ በትልቅ ደስታ ከተማውን አናወጠ። አንዱ ያላመነ ለው "የጴንጤ ኢየሱስ ጀግና ነው" በማለት ወደ ቤቱ ገብቶ ጠመንጃውን በመውሰድ ወደ ላይ ጥይቱን አንጣጣ ይባላል። ለአገሩ ይህ ሌላዉ አስገራሚ ታሪክ ሆነ።
- ድሮ ከከተማ ወጣ ብላ ተተከላ በነበረች ቤተክርስቲያን ፕሮግራሞችን ማድረግ አጅግ በጣም ከባድ ነበር። ምክንያቱም የድንጋይ አሩምታና በተለያየ ጊዜ ይከሰት የነበረዉ የግድያ ሙከራ ነበር። ዛሬ ግን በከተማው መሃል ለሚገኙ ቀንደኛ ተቃዋሚዎች መንግስት ፀጥታን በሚመለከት አንድ ችግር ቢከሰት ተጠያቂ አንሆናለን ብላችሁ ፈርሙ ብሎ በማሰፈረሙ ዛሬ በከተማዉ መሃል ባሉ የአማኞች ቤቶች የላምንቱንም ሰባቱን ቀናት የምሽት ፕሮግራሞች በብዙ ነፃነት ይካሄዳል። ይዘመራል፣ ይጸለያልም። ከተቃዋሚዎች ዘንድ የሚወረወር አንድም ድንጋይ የለም። አንዲሁም አንድም የዛቻ ድምጽ የለም።
- የዛሬ 8 ዓመት አንድ ሚለዮናዊ ገብቶ አምልኮ ይጀምራል። ዛሬ ግን ያቺ የሰንበቴ ሻላ ቤተክርስቲያን ከAIPM ጋር በመተባበር አንድ ሚሽነሪ ወደ ሌላ አካባቢ ልካ የምሥራቹን ወንጌል እያዳረሰች ትገኛለች።
- ዋነኛዉ በከተማው የነበረ አሳዳጅ "ጴንጤ ይህን ከተማ ይለቃል አለበለዚያ እኔ አለቃለሁ" ሲል ፎክሮ ነበር። ከዚህ የተነሳ ስዉየዉ የለደቱን ዓይነት መልኩን አያቀያየረ ያጧጧፍ ነበር። ለሦስት ዓመታት ያህል ጠንቋዩ ታግሎ ታግሎ ካቃተው በኋላ ተስፋ ቆርጦ

ዛሬ ራሱ ከተማውን በመልቀቅ ወደ ሌላ ከተማ ገብቷል። ያም ብቻ ሳይሆን ከሳይ አንደተገለጸዉ ሁሉ በከተማው የቀሩ ቀንደኛ አሳዳጆች አንድ ረብሻ በከተማው ቢፈጠር ተጠያቂዎች ነን የሚል ፈርማ መንግሥት አስፈርሟቸው ዛሬ አይናቸው ፈጦ እያየ ቤተክርስትያን አማኝ ቁጥሩ አየበዛ ነዉ።

- ገና በዚያ ከተማ ወንጌል አንደጀመረ ኢየሱስ የሚባል ስም ያለገደብ የተስደበበት ከተማ ነው። አንዲህ እያሉ ይሳደቡ ነበር፦ ኢየሱስ ሰው ነዉ፦ ይበላል፤ ይጠጣል፤ ይሸናል፤ ... አየተባለ ብዙ ይለደብ ነበረ። ኢየሱስ ዛሬ አንበሳና ሆኖ ንጉሥ ሆኖ በከተማው መካከል እየተሰበከ ይገኛል። አዎን ለነገሩ ኢየሱስ ሞቶ የተቀበረ መስሎ ነበር። ዳሩ ግን በትንሳኤው ስይጣንን ጉድ አድርጎታል። የተአምራቶች ሁሉ ባለቤት የሆነው አግዚአብሔር ከዘለለም አስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን!!